# ወደ ኢየሱስ ተመልከቱ

አሜን። ጆርጅ፡ ቤኪና፡ እህት አንግረን፡ ስለዚህ ግሩም መዝሙር፡ እናመሰግናለን! “ኢየሱስ ሲመጣ ሁሉም ይለወጣል፡” የሚለው በእውነትም ትክክል ነው። እርሱ ጨለማውን አሰወግዶ፡ ብርሃንን ይፈነጥቃል፡ ለዚህም አመስጋኞች ነን። አሁን፡ ቤኪ እዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ ፒያኖ ስትጫወት የመጀመሪያዋ ነው፡ ስለዚህ **ኢየሱስ ሲመጣ** የሚለው መዝሙር፡ እጅግ ተስማሚ ነው።

2 ስለዚህ ዛሬ ማታ፡ እንደገና እዚህ በመገኘታችን ደስ ብሎናል፡ እንዲሁም ዛሬ ጠዋት... ስላደረጋችሁት መልካም ተሳትፎ እጅግ እናመሰግናለን። አሁንም ዛሬ ማታ፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ፡ ልናገርበት የፈለግሁት አንድ ትንሽ ርዕስ፡ አለኝ፥ ነገር ግን ከዚያ በፊት፡ የምናገራቸው አንዳንድ ማስታወቂያዎችና፡ ነገሮች አሉኝ።

3 ድምጼን ትንሽ ዘጋ አድርጎኛል። ከመጠን-በላይ ከመናገር የተነሳ ይመስለኛል። ረጅም ሰዓት ሰብኬያለሁ። ነገር ግን እነዚህን፡ የአንድ ወይም የሁለት ሰዓት፡ ካሴቶች ስቀርጽ፡ ወደዚህም ስመለስ፡ ይሄን የምቀርጸው ለመላው ዓለም ስለሆነ ነው። ስለዚህ ዛሬ ጠዋት በትዕግስት አብራችሁን ስለነበራችሁ እናመሰግናለን።

4 አሁንም እዚሁ ላነሳቸው የምፈልጋቸው ጥቂት ነገሮች አሉ። ይኸውም፡ ማለት፡ በመጀመሪያ ደረጃ፡ ቤተክርስቲያንን መ—መጠየቅ የምፈልገው ነገር አለ፡ አንድ ያ—ያደረግሁትን ነገር፡ ዛሬ ማታ፡ መለወጥ እችል እንደሆነ መ—መጠየቅ እፈልጋለሁ። እኛ...

5 የአዲስ ዓመት የለውጥ ውሳኔዎችን አላደርግም። ከዚያም... ነገ ወደ ቤታችን መሄድ ስላለብን፡ ለአዲስ ዓመት እዚህ አንገኛም፡ ወደ... ነገር ግን እናሰባችኋለን። በአዲስ ዓመት ዋዜማም፡ እዚህ ስብሰባ ይኖራል ብዬ አምናለሁ። አዎን፡ ልክ ነው፡ በ—በአዲስ ዓመት ማታ ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት፡ የሌሊት አገልግሎት ይኖራል። መቆየት እንፈልግ ነበር፡ ነገር ግን ልጆቹን ትምህርት ቤት ለ—ለማድረስ በጊዜ መመለስ አንችልም። ባለቤቴም ልብሶቻቸውን ማጠብ አለባት፥ ሁኔታው እንዴት እንደሆነ ታውቃላችሁ።

6 ስለዚህ በገና በዓል ወቅት ላደረጋችሁልን መልካም ነገሮች እያንዳንዳችሁን ላመሰግን እወዳለሁ። ደግሞም እናንተ ሴቶች እዚያ ሄዳችሁ ለእኛ ምግብና፡ የተለያዩ ነገሮችን፡ እቤታችን ውስጥ በማስቀመጣችሁ፡ እዚያ ስንደርስ፡ እዚያ... ምግቡ አስቀድሞ ተበስሎ ለመበላት ዝግጁ ሆኖ ጠብቆናል። ለዚህ በእርግጥ አመሰግናችኋለሁ። እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ።

7 ቤተክርስቲያንም፡ ከፈለግሁ እዚህ ሄጄ፡ ለ—ለሱፍ የሚሆን ልብስ እንድገዛ ለሰጠችኝ፡ ትንሽ ቲኬት አመሰግናለሁ። በየዓመቱ አንድ የሱፍ ልብስ ይሰጡኛል። ደግሞም አንዳንድ ደግ ጓደኞቼ የሱፍ ልብስ ገዝተውልኛል።

ስለዚህ እንደ እኔ አሳብ፡ ምንም ችግር የሌለው ከሆነ፡ እንደ ሸሚዞች፡ የውስጥ ልብሶችና፡ የመሳሰሉት ሌሎች ነገሮች ስለሚያስፈልጉኝ፡ በቤተክርስቲያን ችግር የሌለው ከሆነ ገንዘቡን ለነዚያ ነገሮች ማዋል እፈልጋለሁ። አሁን ባለው ሁኔታ፡ ከሱፍ ልብሱ ይልቅ... በበለጠ እነዚያ ነገሮች ያስፈልጉኛል።

8 አሁንም፡ ቅድም የዘመረልን ይህ ወጣት፡ ወንድም ጆርጅ ስሚዝ፡ እዚያ ቱክሰን ካለው፡ ከእነርሱ ቤተክርስቲያን ከኒው ቴስታመንት ባፕቲስት ቤተክርስቲያን ነው የመጣው፡ እኛም ወደዚያ ስንሄድ ቆይተናል። አባቱ ሚስዮናዊ ነው። ታች በኦልድ ሜክሲኮ ውስጥ ወደ ሰባት የሚጠጉ ቤተክርስቲያኖች ያሉት ይመስለኛል። በእርግጥም እዚያ ግሩም የሆኑ ሰዎች አሉ። አባቱና እናቱ፡ እንዲሁም ሁሉም፡ ግሩም ሰዎች ናቸው። ጆርጅም በጣም ግሩም ወጣት ነው። ከመቀመጡ በፊት በሕይወቱ ውስጥ ስላለው ስለ ክርስቶስ አዳኝ ጸጋ፡ የምስክርነት ቃል ስላልሰጠን ብቻ አዝኜ ነበር።

9 አሁንም፡ መ—መልእክቶቹን በተመለከተ፡ በቅርብ ጊዜ እዚህ ቃል እንደገባሁት፡ መልእክቶቹን፡ ወደ ስብሰባዎቹ ከመሄዴ በፊት፡ መጀመሪያ እዚህ መጥቼ እንደምቀርጻቸውና ከዚያም እንደምወጣ ነበር። ያም የሆነው ካሴቶቹን ለሰዎች ለማድረስ በማሰብ ነበር። ስለዚህ እዚህ መጥቼ መልእክቱን እቀርጻለሁ፡ ቀጥሎም ወጥቼ እሰብከዋለሁ። ይህ ደግሞ ለሰዎች፡ ለ—ለካሴት አዘጋጆቹ፡ ካሴቱን አዘጋጅተው ስንሄድ አብረውን እንዲወስዱት እድል ይሰጣቸዋል። አሁን በታላቅ የወንጌል አገልግሎት ጉዞ ላይ ለመውጣት እየተዘጋጀሁ ስለሆነ፡ ከአሁን በኋላ ያንን ማ—ማድረግ አልችልም፡ እያችሁ፡ ስለዚህ ካሴቶቹን የሚወስደው ሰው እኛ እያገለገልን ባለንበት ሂደት ውስጥ ማግኘት ይኖርበታል።

10 ደግሞም፡ እንደማስበው ከሆነ፡ በዚህ ሳምንት ስለ ካሴቶቹ ስብሰባ የላቸውም እንዴ? ወይም፡ በዚህ ሳምንት ስለ ካሴቶቹ የሚሆን፡ ሌላ ነገር አላቸው። ለማንኛውም፡ ወንድም ሶዝማን እዚህ ያለ ይመስለኛል፡ እርሱም ወንድም ማጓየርን ይወክላል። እዚህ ይኑር አይኑር አላውቅም። ወንድም ፍሬድ እዚህ ያለ ይመስለኛል። አንድ ሰው እዚህ እንዳለ ነግሮኛል። እርሱም... ስለ ካሴቶቹ በዚህ ሳምንት፡ ምናልባት ነገ ማታ፡ ወይም በሌላ ጊዜ፡ ስብሰባ የሚያደርጉ ይመስለኛል። ባለፈው ምሽት እዚያ ክፍል ውስጥ፡ ስለዚሁ ጉዳይ ሲናወራ ነበር። ስለ ጉዳዩ ተነጋግረው ማስተካከያ የሚያደርጉበት ጊዜው፡ አሁን የደረሰ ይመስለኛል።

11 ስለዚህ፡ ከአሁን በኋላ፡ እዚህ ተበርናክል ውስጥ ያልነካኋቸውን መልእክቶች፡ ምናልባት በስብሰባዎቹ ላይ ብቻ እናገራለሁ።

12 አሁንም፡ ለዚያ የወንድም ብሌየር ምስክርነት ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ። ያ ትንሽ ልጅ የነበራቸው ወንድምና እህት ብሌየር፡ ዛሬ ማታ እዚሁ ተቀምጠዋል፡ እዚሁ ከፊታችን ተቀምጠዋል። ወንድም ብሌየርም፡ እጅግ ተረብሾ፡ እያለቀሰ፡ በነበረበት ጊዜ... ጌታ የነገረኝን አስታውሳለሁ። ትንሹ ልጁም መኪና-ተገልብጦበት፡ ፊቱ ላይ **እንደዚህ** ክፉኛ ተጎድቶ ነበር፡ ሁኔታውም በጣም ከባድ ነበር። ዳሩ ግን ሰ—ሰጸልይ፡ ትንሹን ልጅ ደህና ሆኖ አየሁት። ወንድም ብሌየርም፡ እርግጥ ነው፡ ጠየቀኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ **ይህ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነውን፡" አለኝ?

እኔም፡ “ወንድም ብሌየር፡ ብሌየር፡ ይህ **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነው” አልኩት።

13 ወንድም ብሌየርም ዛሬ ማታ እዚህ ይገኛል። ወንድም ብሌየርም ከእኛ ጋር በመሆኑ በእርግጥም አመስጋኞች ነን። እርሱም ትንሽ በ—በጭንቀት ችግር ሲሰቃይ ቆይቷል። በእኔ እንዳያምን፡ ሰይጣን፡ በቅርብ ጊዜ ክፉኛ መትቶት ነበር። ሰይጣንም ያንን ሲያደርግ፡ ጌታ ወዲያው መጥቶ ገለጠለት፥ ጊዜው ከመድረሱ በፊት፡ ሊያስወግደውም ስለዚሁ ጉዳይ ነገረው። ወንድም ብሌየርም ግሩም ሰው ነው። እንድታስታውሱትም እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ እንዳለበት በሁለት ሃሳብ እያመነታ ነው። ወዴት መዞር እንዳለበት አያውቅም። ደግሞም እምናለሁ፡ ወንድም ብሌየር፡ እግዚአብሔር… አንተ ታላቅ የክርስቶስ አገልጋይ ነህ፡ መብራቶቹም እየደበዘዙ ስለሆነ፡ እርሱም አንተ የምትሰራለት ብዙ ስራ አለው። ዛሬ ጠዋት እዚህ ነበርክ? ኧ-ህ። መልካም፡ ይህ በጣም ጥሩ ነው።

14 አ—አሁንም፡ ቀጥሎ የማያችሁ፡ ለትንሽ ጊዜ፡ በጸደይ ወራት አካባቢ ሊሆን ይችላል፡ ብዬ አስባለሁ። በዚያን ጊዜም፡ በ—በኖርዌይ፡ እንዲሁም በስካንዲኔቪያን ሀገራት መሆን በነበረብኝ ጊዜ፡ እዚህ ጀፈርስንቪል ውስጥ፡ ስብሰባዎቹን እንደምናካሂድ ወይም እንደማናካሂድ እናውቅ ይሆናል። አሁንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍላችንን ከመውሰዳችን በፊት…

15 ምክንያቱም፡ የምናደርገው የጸሎት መሰመር ስላለን፡ ብዙዎችም በክፍሎቹ ውስጥ፡ በግድግዳዎቹ ዙሪያ፡ እንዲሁም በመሳሰሉት ቦታዎች፡ ቆመዋል፡ ይሄም ለእናንተ፡ በጣም ከባድ እንደሆነ፡ አውቃለሁ። እኔም፡ ራሴ፡ ብዙ ጊዜ ቆሜያለሁ። ቅድም፡ ባለቤቴን ይዤ ስመጣ፡ ሳልፍ፡ በሮች አካባቢ የቆሙትን ሰዎች አስተውያለሁ። እኔም፡ “ወንጌል አሁንም በዓለም ላይ ካሉ ነገሮች ሁሉ ይበልጥ ማራኪ አይደለም ብሎ የሚናገር ማነው” ብዬ አሰብኩ? በእርግጥም ማራኪ ነው። እርሱ፡ ፍላጎት ያላቸውን ይሰባል። ፍላጎት የሌላቸው ግን፡ በእርግጥ፡ አይሳቡም። ለእነርሱ፡ አይሆንም። ነገር ግን፡ ኢየሱስ፡ “እኔ እ፡” “ከምድር ከፍ ከፍ ያልኩ እንደሆነ፡ ሁሉንም ወደእኔ እሰባለሁ፡” ብሏል። ይህም ምንኛ እውነት ነው!

16 ወደዚህ ስመጣ፡ የምናገረው በጣም ብዙ ነገር ስላለ፡ እዚህ የምናገረውን ነገር ለትንሽ ጊዜ፡ አጠር አድርጌ ማስታወሻ መያዝ ይኖርብኛል። ወይም… የሚነገር በጣም ብዙ ነገር ስላለ፡ ልትናገሩ ያሰባችሁትን ነገር ትረሱታላችሁ።

17 አሁንም፡ የወንድም አንግረን አባት፡ ዛሬ ጠዋት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደተጠመቁ ተረድቻለሁ። እህት አንግረንና ቤተሰቧ እዚህ ካሉ፡ ይህ ለብዙ ዓመታት የዘወትር ጸሎታቸው ስለነበር፡ ለእነርሱ ትልቅ ነገር እንደሚሆን እርግጠኛ ነኝ። ወንድም አንግረንም፡ የትም ይሁን ባለህበት ሰፍራ፡ ወንድሜ፡ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክህ።

18 ያም ትክክል ካልሆነ፡ በፍርድ ቀን እግዚአብሔር እንድጠየቅበት ያድርገኝ። አያችሁ? ትክክል እንደሆነ አውቃለሁ። ለ—ለዚህም እኔው ጥፋቱን እወስዳለሁ። ይህ ፈጽሞ ትክክል ነው፡ ምክንያቱም እውነት ነውና።

እናንተም፡ “የሚያመጣው ለውጥ አለን” ትሉ ይሆናል?

19 ለጳውሎስ አምጥቷል። እንዴት እንደተጠመቁ ጠየቋቸው። እነርሱም ኢየሱስን ባጠመቀው ሰው፡ በዮሐንስ አስቀድመው እንደተጠመቁ ተናገሩ። ጳውሎስም መጥተው በ“ኢየሱስ ክርስቶስ” ስም፡ በድጋሚ፡ እንደገና መጠመቅ እንዳለባቸው ተናገረ። በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ አንድም ሰው በ “አብ፡ ወልድና፡ መንፈስ ቅዱስ” ስም ከቶ ተጠምቆ አያውቅም።

20 በላኦ-... ላኦ-ኒቂያ በሮም ላኦ ኒቂያ በሚገኘው የላኦ ኒቂያ ጉባኤ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን እስከተደራጀችበት ጊዜ ድረስ፡ ሰዎች-ከቶ በዚህ ሁኔታ፡ ተጠምቀው-አያውቁም። ማዕረጎቹን በመጠቀም፡ የመጀመሪያው ሰው የተጠመቀውም በዚያ ነበር።

21 ስሞኑን አንድ ሰው እንዲህ አለኝ። እኔም፡ “መልካም፡ ከሆነ... ‘ጌታ ኢየሱስ፡’ ያ የእርሱ ስም ነው” አልኩት። እርሱም... “መልካም፡” እኔም እንዲህ አልኩ፡ “አንድ ሰው ወደ አንተ ቢመጣ... ”

እርሱም፡ “ምንም ለውጥ የሚያመጣ አይመስለኝም” አለ።

22 በገዛ ትምህርቱ ያዝኩት። እኔም፡ “አንድ ሰው ወደ አንተ መጥቶ፡ ‘በሻሮን ጽጌረዳ በሸለቆው አበባና፡ በንጋት ኮከብ ስም፡ ተጠምቄያለሁ’ ቢልህ፡ ለዚያ ‘አሜን’ ትላለህን” አልኩት?

እርሱም፡ “አልልም፡ ወዳጄ” አለኝ።

እኔም፡ “እንዴት ታደርጋለህ... እንደገና ታጠምቀዋለህን” አልኩት?

“አዎ፡ ጌታዬ፡” አለ።

እኔም፡ “እንዴት ታጠምቀዋለህ” አልኩት?

እርሱም፡ “በ ‘አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ’ ስም አጠምቀዋለሁ” አለ።

23 እኔም፡ “እኔም የማጠምቀው በዚህ መንገድ ነው፡ አዎ፡ በአብ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም” አልኩት። እንዲህም አልኩት፡ “አሁን፡ ‘የሻሮን ጽጌረዳ፡ የሸለቆው አበባና፡ የንጋት ኮከብ’ ስም አይደለም” አልኩት።

እርሱም፡ “ልክ ነው። ማዕረግ ነው” አለ።

24 እኔም እንዲህ አልኩት፡ “‘አብ፡ ወልድና፡ መንፈስ ቅዱስም’ እንደዚሁ ነው። አሁን እኔ በአብ፡ በወልድና፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቀዋለሁ፥ የአብ፡ የወልድና፡ የመንፈስ ቅዱስ ስም ደግሞ ‘ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ’ ነው። በትክክል። ስለዚህ እላለሁ... ” ብታምኑም፡ ባታምኑም፡ እርሱም አስተዋለው።

25 እርሱም የቺካጎው፡ ወንድም ጆሴፍ ማትስን-ቦዝ ነበር፡ በዚህ ጉዳይ፡ ወደ እርሱ ዘልቄ ለመግባት ከገጠሙኝ ሰዎች ሁሉ በጣም ከባዱ ሰው እርሱ ነበር። እናም አሁን ከእርሱ ጋር አፍሪካ ሰደርስ እንደገና እንዲጠመቁ የተዘጋጁ፡ በግምት ወደ ሦስት ወይም አራት ሺህ የሚጠጉ፡ የአገሬው ተወላጆችን ማጥመቅ ይኖርብኛል።

26 እንግዲህ፡ ስለወንጌሉ ብርሃን ምስጋናችን ብዙ ነው። ስለዚህ አሁንም፡ ኢየሱስ፡ በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ፡ “እኔም፡ የምሰማውን፡ ያንን እናገራለሁ” ብሏል። አሁንም ልናገር ነው... በቀጣዮቹ አሰር፡ ወይም አስራ አምስት፡ ደቂቃዎች፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከማንበቤ በፊት፡ እጅግ አጭር ክፍል

ይሆናል፡ ከዚያም የጸሎት መስመር ይኖረናል። በአገልግሎቴ ውስጥ፡ አንድ ነገር መናገር ወ—ወደሚገባኝ ደረጃ ላይ... ደርሻለሁ። እኔም...

27 ኢየሱስ ተናግሮታል። እርሱ የሰማውን ነገር፡ የተናገረው ያንን ነበር። እርሱም፡ “ወዳጆቼ ብዬ ጠርቻችኋለሁ፡ ወዳጅም ለወዳጆቹ ሁሉንም ነገር ይናገራል” ብሏል።

28 ጳውሎስ፡ በሐዋርያት ሥራ 20፥27 ላይ፡ “የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ለእናንተ ከመንገር ወደ ኋላ አላልሁም” ብሏል። አያችሁ?

29 ዛሬ ማታ፡ እኔም ከጥንታዊው ታላቅ ቅዱስ ጋር አብሬ፡ ያንኑ ነገር ልናገር። ባለኝ እውቀት መጠን፡ ወደ ኋላ አላልሁም... የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ለእናንተ ነገርኳችሁ እንጂ፡ ወደ ኋላ አላልሁም።

30 ሰሞኑን አንድ ሰው ከካሴቶቼ፡ አንዱን እያጫወተ ነበር። አንድን ሰው ስላስቆጣው ብቻ፡ በመስኮት በኩል ተኮሱባቸው፡ አንዲት ሴትም ቆሰለች።

31 ስለዚህ ምናልባት አንድ ቀን ምስክርነቴን አትም ይሆናል። ነገር ግን ያ ጊዜ ሲመጣ... እኔ ለመሄድ ዝግጁ ነኝ። ጊዜዬ እስኪደርስ ድረስ፡ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ሊጎዳኝ የሚችል ምንም ነገር የለም። አያችሁ?

32 አሁንም፡ መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት በዚያው ሁኔታ፡ በዚያው ወንጌል እናምናለን። ኢላማው የተስተካከለ ነው። እ—እንዲሁም ጠመንጃው በትክክል ዜሮ ላይ ከተስተካከለና፡ አቅጣጫውም ከተጠበቀ፥ የመጀመሪያውን ጊዜ ኢላማውን ከመታው፡ ሁለተኛውንም ጊዜ ይመታዋል፡ ሁልጊዜም ይመታዋል።

33 አንድ ዛፍ፡ ወይም አንድ ግንድ፡ ወይን፡ ቅርንጫፍ ቢያወጣ፡ ያም ቅርንጫፍ የተወሰነ ፍሬ ቢያፈራ፥ በሚቀጥለው ጊዜ ያ—ያ ወይን ቅርንጫፍ ሲያወጣ፡ ያንኑ ዓይነት ፍሬ ያፈራል።

34 እንግዲህ ኢየሱስ የወይኑ ግንድ ከሆነ፡ እኛ ደግሞ ቅርንጫፎቹ ከሆንን፥ ያም ወይን ያወጣው የመጀመሪያው ቅርንጫፍ፡ ቤተክርስቲያን፡ በጀርባዋ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ተጽፏል። ያም የመጀመሪያው ቅርንጫፍ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠመቀ። በምድር ላይ ሳለ ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር በመካከላቸው የሚያደርገው ሕያው አምላክ፡ በመካከላቸው ነበረ። ስለዚህም፡ ሰዎች ያልተማሩና ተራ ቢሆኑም እንኳ፡ ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩ አስተዋሉ፥ ምክንያቱም የእርሱ ሕይወት፡ በእነርሱ በኩል ይኖር ነበርና።

35 እንዳልኩትም፡ የ—የቤቶቨን መንፈስ በውስጤ ቢኖር ኖሮ፡ መዝሙሮችን እጽፍ ነበር። ቤቶ-... እኔም... ቤቶቨን በውስጤ ቢኖር ኖሮ፡ እኔም ቤቶቨን እሆን ነበር። አያችሁ?

36 ሼክስፒር በውስጤ ቢኖር ኖሮ፡ ሼክስፒር እሆን ነበር። ሼክስፒር በ—በውስጤ ቢኖር ኖሮ፡ ግጥሞችን፡ ተ—ተ—ተውኔቶችን፡ እንዲሁም ሌሎችንም ነገሮች እጽፍ ነበር።

37 ክርስቶስም በውስጤ ቢኖር፡ የክርስቶስን ስራ ትሰራላችሁ። ልክ ነው። እንደዚህ መሆን አለበት። ክርስቶስ ምንድን ነው? ቃሉ። እርሱም፡ “በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ ቢኖር፡ የምትፈልጉትን ሁሉ ለምኑ፥ ይሆንላችኋል” ብሏል። ምክንያቱም፡ ቃሉ እዚያ አለ፡ የሚያስፈልገው ብርሃን ብቻ ነው፥ ብርሃኑም ህያው ያደርገዋል።

38 ስለዚህ አሁን፡ እስካሁን ድረስ ያልተናገርኩትን አንድ ነገር፡ አሁን ለእናንተ ልነግራችሁ ነው። ይኸውም፡ ይህ ነው፡ እጅግ ለረጅም ጊዜ በጉጉት ስንጠብቀው የነበረው ነገር (ቢያንስ ለብዙ ዓመታት፡ ለአራት ወይም አምስት ዓመታት፡ ምናልባትም ከዚያ በላይ)፡ ይህም ሦስተኛው ስህበት ነው፡ አሁን ተረጋግጧል፡ ምን እንደሆነም ሁላችሁም እንደምታውቁ እርግጠኛ ነኝ።

39 አሁን አስታውሱ፡ ይህን ፈጽሞ ማስመሰል አይቻልም፡ ምክንያቱም አይቻልም፡ አያችሁ፡ ሊሆን አይችልም። አሁን፡ በገሃድ አለ፡ እንዲሁም... ስለዚህ ነገር ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኛል፡ በቅርቡ... አሁን በዚህ ሰዓት የሆነው፡ በመካከላችሁ መኖሩ እንዲታወቅ ብቻ ይህ አሁን ሆነ፡ አያችሁ፡ ነገር ግን ያ ካውንስል ማጣበብ እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ በታላቅ መንገድ ጥቅም ላይ አይውልም፡ ያ ሲሆን፡ ያ ሲከሰት፡ ጴንጤቆስጤዎችና፡ የመሳሰሉት፡ የሚደረገውን ማንኛውንም ነገር ከሞላ ጎደል ማስመሰል ይችላሉ፡ ነገር ግን ያ ጊዜ ሲመጣ፡ መጣበቡ ሲመጣ፡ በጊዜያዊነት ስታዩት የነበረውን ነገር፡ ያኔ በኃይሉ ሙላት ሲገለጥ ታዩታላችሁ። አያችሁ? አያችሁ? አያችሁ? አያችሁ?

40 አሁን የወንጌላዊነት አገልግሎቴን መቀጠል አለብኝ። መጀመሪያ፡ እንደታዘዝኩት፡ መቀጠል አለብኝ። ስለዚህ ቃሉ አላችሁ፡ ምን መጠበቅ እንዳለባችሁና፡ እንዴት መቆም እንዳለባችሁ ታውቃላችሁ። በወንጌላዊነት አገልግሎቴ መቀጠል አለብኝ። ወዳጆቼ ሆይ፡ ጸጥ በሉ፡ እንዲሁም፡ ወደፊት መጓዛችሁን ቀጥሉ፡ ምክንያቱም ሰዓቱ በፍጥነት እየቀረበ ነው፡ አያችሁ፡ አንድ ነገር የሚደረግበት ጊዜ ደርሷል።

41 አሁን፡ በእኔ ዘንድ አንዳንድ ያልተለመዱ ነገሮች ሲሆኑ ታዩ ይሆናል። ኃጢአት የሆነ ነገር ማለቴ አይደለም፥ ያንን ማለቴ አይደለም። ነገር ግን፡ ከመደበኛው አካሄድ ለየት ያለ ነገር፡ ማለቴ ነው። ምክንያቱም፡ አሁን በአገልግሎት፡ ከደረስኩበት ቦታ፡ ያንን ስፍራ እየተመለከትኩና የምጠቀምበትን ጊዜ እየጠበቅኩ፡ ወደዚህ ወደ ኋላ እየተመለስኩ ነው። ነገር ግን፡ ጥቅም ላይ ይውላል።

42 ይህንንም ሁሉም ሰው ያውቀዋል፡ ምክንያቱም፡ አንደኛው እንደተረጋገጠ ሁሉ፡ ሁለተኛውም ተረጋግጧል። እናንተ መንፈሳውያን የሆናችሁ፡ በጥልቀት ብታስቡበት ታያላችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለው፡ "ጥበብ ላለው ይኸው።" ሦስተኛውም በትክክል ተረጋግጧል። አያችሁ? የት እንዳለ እናውቃለን። ስለዚህ፡ ሦስተኛው ስህበት እዚህ አለ።

43 እጅግ የተቀደሰ፡ ስለሆነ፡ ስለ እርሱ ብዙ መናገር የለብኝም። በመጀመሪያ እንደነገረኝ፡ "ስለዚህ፡ ነገር ምንም አትናገር፡" ብሎኛል። ከዓመታት በፊት፡ ያንን ታስታውሳላችሁ? ስለ ራሱ ራሱ ይናገራል። አያችሁ? ነገር ግን እ... ሌሎቹን ለማብራራት ሞክሬ፡ ስህተት ሠርቻለሁ። ነገሩ የሚሆነው እንዲህ ነው፡ ይህም፡ በግምቴ... ጌታ ይህንን ነገረኝ አላልኩም። ከዚህ ለመሄድ የመነጠቅን እምነት የሚያስጀምር፡ ይህ ነገር ይሆናል። አያችሁ? አያችሁ? ይህ ደግሞ...

44 ለጥቂት ጊዜ ጸጥ ማለት ይኖርብኛል። አሁን አስታውሱ፡ ይህንን ካሴት የምትሰሙ ሁሉ፡ በአገልግሎቴ ላይ ወዲያውኑ እንዲህ ያለ ለውጥ ታዩ ትችላላችሁ፡ ወደ ላይ መውጣት ሳይሆን፥ ወደ ኋላ፥ ወደ ኋላ መመለስ። አሁን ልክ በዘመኑ ላይ ደርሰናል፡ ከዚህ በላይ መሄድ፡ አይችልም። ይህኛው ነገር

**እዚህ** ጋር ተከሰቶ እስኪደርስብን ድረስ፡ ትንሽ መጠበቅ አለብን፡ ከዚያም ጊዜው ይመጣል። ነገር ግን፡ በሚገባ ጸንቷል።

45 በዚህች አገር ላይ፡ አረማዊት ሮም ወደ ጳጳሳዊት ሮም በተቀየረች ጊዜ፡ ከእርሷ በፊት የነበረው አውሬ ይጠቀምበት የነበረውን ሥልጣን ሁሉ፡ ይህች አገር የምትተገብርበት ጊዜ ይመጣል፡ አያችሁ፡ ይህች አገር ያንን ታደርጋለች።

46 ራእይ 13 ይህንን በግልጽ ያስረዳል። “በጉ ከምድር ወጣ። ሌላኛው አውሬ ከውሃ ወጣ፡” ይህም የህዝብ ብዛትና ጭንቅንቅ ነው። ይህ በግ የወጣው ህዝብ በሌለበት ስፍራ ነው። በግ ሐይማኖትን ይወክላል። የእግዚአብሔር በግ... እንዲሁም፡ አስታውሱ፡ እንደ በግ ተናገረ። በግ ነበረ።

47 ከዚያም፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እርሱ-... ሥልጣን ተቀበለ፡ እንደ ዘንዶም ተናገረ፡ ዘንዶው ከ—ከእርሱ በፊት የነበረውን ሥልጣን ሁሉ፡ በሥራ ላይ አዋለ። **ዘንዶው** ሁልጊዜም “ሮም፡” ነው። ስለዚህ ታዲያ አታዩትምን? የሮም የሐይማኖት ተቋም፡ “ምልክት፡” የፕሮቴስታንት የሐይማኖት ተቋም፥ “ለአውሬው ምስል፡” ይህም ልክ እንደ ህብረት፡ ፕሮቴስታንቶችን ሁሉ የሚያስገድድ ሥልጣን ማድረግ ነው። በዚህ የቤተ ክርስቲያናት ካውንስል ውስጥ መሆን ይኖርባችኋል፡ አለበለዚያ ህብረት ማድረግ አትችሉም። ወ—ወይንም...

48 አሁንም፡ በ—በተግባር አሁን እንደዚያው ሆኗል። የህብረት ካርድ ወይም የተወሰነ መታወቂያ ከሌላችሁ በስተቀር ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄዳችሁ መስበክ አትችሉም። አሁንም፡ እንደ እኛ ባሉ ሰዎች ላይ፡ ከዚህ ሁሉ ሙሉ በሙሉ፡ ልንገለል ነው፡ ይህ ፈጽሞ ትክክል ነው፡ ምክንያቱም ይህንን ማድረግ አይችሉምና።

49 ነገሩ እየከረረ ነው። ከዚያም ያ ጊዜ ሲመጣ፡ እንዲሁም ጫናው እናንተን አስወጥቶ እስከሚገፋበት ደረጃ ሲደርስ፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ልነግራችሁ ያዘጋጀሁትን ተመልከቱ። ያኔ ሦስተኛውን ስህበትን ተመልከቱ፡ አያችሁ፡ እርሱም ሙሉ በሙሉ ለጠፉት ይሆናል፡ ነገር ግን ለ—ለሙሽሪትና ለቤተ ክርስቲያኒቱ ይሆናል።

50 አሁን ከሚመስለን በላይ በጣም ቀርበናል። መቼ እንደሆነ አላውቅም፡ ዳሩ ግን እጅግ፡ እጅግ በጣም ቀርቧል። ሌላ ሰው የሚወጣበትን መድረክ እየገነባሁ ሊሆን ይችላል። ከዚያ ጊዜ በፊት እወሰድ ይሆናል። አላውቅም። ያም ጊዜ በዚህ በሚመጣው ሳምንት ሊሆን ይችላል፡ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ... ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመጣበት። በዚህ በሚቀጥለው ሳምንት ሊመጣ ይችላል። ምናልባትም ዛሬ ማታ ይመጣ ይሆናል። መቼ እንደሚመጣ አላውቅም። ያንን አይነግረንም።

51 ነገር ግን፡ እጅግ በጣም ስለቀረብን፡ በእርጅና ምክንያት እንደማልሞት አምናለሁ። ሆኖም፡ በሃምሳ-አራት ዓመቴ፡ እርሱ እስኪመጣ ድረስ፡ በእርጅና አልሞትም። አያችሁ? ካልተተኮሰብኝና፡ ካልተገደልኩ፡ ወይም በሌላ ነገር፡ በሆነ መንገድ ካልተገደልኩ በቀር፡ እርሱ እስኪመጣ ድረስ፡ እንዲሁ በእርጅና አልሞትም። ይህንንም አምናለሁ።

52 ይህንንም መናገር እፈልጋለሁ። ከዚህ በፊት ተናግሬው አላውቅም። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፡ ከሠላሳ ዓመታት በፊት እንደተናገረው፥ ማለቴ፡

በ1933፡ እዚያ ወንዝ ላይ ከሠላሳ-ሦስት ዓመታት በፊት፡ እንደተናገረው፥ የተናገረው ሁሉ በትክክል ሆኗል። ላላደርገው እችላለሁ፡ ነገር ግን ይህ መልእክት ኢየሱስ ክርስቶስን ለዓለም ያስተዋውቃል። ምክንያቱም፡ “መጥምቁ ዮሐንስ ለመጀመሪያው መምጣት መንገድ ጠራጊ ሆኖ እንደተላከ ሁሉ፡ ይህ መልእክትም ለሁለተኛው መምጣት መንገድ ጠራጊ ይሆናል።” ዮሐንስም፡ “የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እነሆ” ብሏል። አያችሁ? ስለዚህ፡ በሁሉም አቅጣጫ፡ ትይዩ ሆኗል። እንደሚሆንም አውቃለሁ፡ መልእክቱም ይቀጥላል።

53 አሁን፡ በመንገዳችን ላይ አንዳንድ ታላላቅ ነገሮች ሲከሰቱ ቆይተዋል። ዛሬ ጠዋት እዚህ ክፍል ውስጥ ሰዎችን ሳነጋግር ነበር። ኦ—ኦትሪ የሚባል፡ አንድ ወጣት፡ ምናልባትም ዛሬ ማታ እዚሁ ይገኛል ብዬ እሰባለሁ። የመጣው ከሳን አንቶኒዮ፡ ቴክሳስ ነው። የመጣውም ከካሊፎርኒያ ተነስተን፡ ወደ ዳላስ ስንሄድ... ወደ ተበርናክላቸው፥ ለአንድ ምሽት ብቻ፡ ኈራ ማለት እንችል እንደሆነ ሊጠይቀኝ ነው። ያንን ማድረግ እንችል እንደሆነ፡ በሚቀጥሉት አንድ ወይም ሁለት ቀናት ውስጥ፡ እያጣሩት ነው። እርሱም ይነግረኝ የነበረው... ከዚያ የመጀመሪያ አገልግሎት ወዲህ ወደ ሳን አንቶኒዮ ሄጄ አላውቅም።

54 አሁን፡ የመጀመሪያው አገልግሎት፡ ወደ ሳን አንቶኒዮ በመጣሁበት ጊዜ ነበር። እዚያ የነበርኩት፡ ከወንድም ኩትና ከ—ከዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ጋር፡ ይመስለኛል። አገልግሎቱን ያደረግንበትን አዳራሽ ረስቼዋለሁ። የመጀመሪያው ወይም የሁለተኛው ምሽት ነበር፡ የመጀመሪያው ምሽት ይመስለኛል፡ ወደ መድረክ እየተራመድኩ ሳለ፡ በህንጻው ውስጥ በጣም ወደ ኋላ፡ አንድ ሰው ተነስቶ፡ ልክ እንደ መትረየስ ጥይት እንደሚተኮስ፡ በ—በልሳን ተናገረ። እርሱም እንደተቀመጠ ወዲያው፡ አንድ ወይም ሁለት እፍታ እንኳን ሳይቆይ፡ በመድረኩ ላይ አንድ ሰው ተነስቶ ትርጉሙን ሰጠ።

55 እኔም በተናገረው ነገር፡ ቆም አልኩ። ለሰውየውም፡ “**ይህንን** ሰው ታውቀዋለህን” አልኩት?

እርሱም፡ “አላውቀውም፡ ጌታዬ” አለ። እርሱም አለ...

እኔም፡ “እንዴት ወደዚህ መጣህ” አልኩት?

56 እርሱም፡ “የምሠራላቸው ሰዎች፡ እዚህ... ዛሬ ማታ እዚህ ነበሩ፡ እነርሱ ናቸው ያመጡኝ” አለ። እርሱ... የከብት እረኛ ነበር።

እኔም፡ “**አንተ** ምንደው የምትሰራው” አልኩት? እርሱም... “ታውቀዋለህን? ”

57 እርሱም፡ “አላውቀውም፡ ወዳጄ። ፈጽሞ አይቼው አላውቅም” አለ።

58 እኔም፡ “አንተስ ምን ትሠራለህ” አልኩት? እርሱም በከተማው ውስጥ... ነጋዴ ነበር።

59 የተናገሩትም ነ—ነገር በ... አሁን፡ በተሻለ ሁኔታ ከመረዳቴ በፊት፡ ሁልጊዜ፡ ልሳን መናገርን በተመለከተ ትንሽ ተጠራጣሪ ነበርኩ፥ አብዛኛው ስጋዊ ነው ብዬ አስብ ነበር፡ ሊሆንም ይችላል። ዳሩ ግን ይህ በተነገረ ጊዜ፡ ያ ትርጓሜ አሥራ አንድ ዓመታት በፊት፡ እዚያ ወንዝ ላይ የጌታ መልአክ ከተናገረው ጋር ፍጹም አንድ ዓይነት ነበር፡ “መጥምቁ ዮሐንስ ለመጀመሪያው

የክርስቶስ መምጣት መንገድ ጠራጊ ሆኖ እንደተላከ፡ አንተም ለሁለተኛው መምጣት መንገድ ጠራጊ ሆነህ ተልከሃል″ የሚል ነበር። አያችሁ?

60 ይኼውና፡ ያ መልአክ፡ በሚገባ የጸናው ያ ብርሃን። በቤተ ክርስቲያን፡ በቃሉ፡ በሳይንስ፡ እንዲሁም በሁሉም ነገር፡ ጸንቷል። ያ ብርሃን፡ በአደባባይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታይ፡ ልክ እኔ በነበርኩበት ቦታ ላይ ቆሞ ነበር፥ ከሰዓት በኋላ በግምት በሁለት ሰዓት ገደማ፡ ልክ እዚያው ከድልድዩ ግርጌ፡ እዚህ ታች የስፕሪንግ ጎዳና መጨረሻ ላይ፡ በውኃው ውስጥ ነበር። አሁንም፡ ያ ከሆነ ብዙ፡ ብዙ ዓመታት አልፈዋል። የተናገረውም ነገር ሁሉ፡ አንዲትም ነጥብ ሳትጓደል በትክክል ተፈጽሟል።

61 ይህ ወንድም፡ ዛሬ ጠዋት ሲነግረኝ ነበር። እዚህ ከቤተ ክርስቲያናችን አንዲት ልጅ አግብቷል፡ የእህት ኖይሰን ልጅ። እኔም አላውቅም፡ ወጣቱ... ወንድም ኑትሪ፡ እዚህ አለህን? አላውቅም። ከሳን አንቶኒዮ ነበር። እዚህ ይኑር አይኑር አላውቅም። ዛሬ ጠዋት እዚህ ነበር። እየነገረኝ ነበር። በዚያ ስብሰባ ጊዜ፡ አያቱ ይመስለኛል፡ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ የሚጥል በሽታ ነበረበት፡ ወደዚያም መጥቶ ነበር።

62 ያ የመጀመሪያው፡ የአገልግሎቱ ጅማሬ ነበር፡ ይኸውም እርሱ፡ በመንፈስ ምስጢርን ማወቅ የሚሆነው፡ እጃቸውን በእኔ እጅ ላይ ሲያደርጉ እንደሆነና፡ የሚነገረውም ነገር ልክ የተባለው እንደሚሆን በተናገረ ጊዜ ነበር። ለእናንተም ነግሬአችሁ ነበር፡ ዛሬ ምሽትም ብዙዎች ምስክሮች ናቸው፡ የልባቸውን ምስጢር እንኳ ሳይቀር እስከማወቅ እንደሚሆን ነግሬአችኋለሁ። ያ ከመሆኑ በፊት፡ ታስታውሳላችሁን? ከአምስት ወይም ስድስት ዓመታት በኋላ፡ ያ ተፈጸመ፥ እዚያ ካናዳ ውስጥ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ያ ተፈጸመ። ከዚያም፡ “ቅንነትህን ከጠበቅህ፡ ይህ እየቀጠለ ይሄዳል″ አለኝ። አሁንም ሦስተኛው ነገር ተከሰቷል፡ አያችሁ፡ ያለማቋረጥ ወደፊት እየገፋ ነው።

63 እርሱም አባቱ በጸሎት መሰመር ውስጥ መጥቶ፡ ስለዚሁ የሚጥል በሽታና፡ የመሳሰሉት እንደተነገረው፡ ጸሎትም እንደተጸለየለት ተናገረ። ያም ከሆነ አስራ ስድስት ዓመታት አልፈዋል፡ አስራ ስድስት ወይም አስራ ሰባት ዓመታት አካባቢ አልፈዋል፡ ብዬ እሰባለሁ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም በሽታው አንዴም እንኳን ጥሎት እንደማያውቅ ይናገራል። አሁን ዕድሜው ሰማንያ-አምስት ዓመት ገደማ ሆኖታል፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም አንዴም እንኳን አልጣለውም። ይህ ምንድን ነው? “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።″

64 ማርጂ ሞርጋን ህንጻው ውስጥ አለች? የካንሰር በሽታ በልቷት የነበረችው ሴት፡ እህት ማርጂ ሞርጋን፥ ነርሷ። ስንቶቻችሁ እህት ሞርጋንን ታስታውሳላችሁ? እዚህ ብትኖርም፡ ወደ ውስጥ መግባት አትችልም። የነርስነት ስራዋን ትሰራ ነበር። አያችሁ፡ እንደ ሉዊስቪል የካንሰር ታማሚዎች መዝገብ፡ ይህች ሴት ከሞተች አስራ ስድስት፡ አስራ ሰባት ዓመታት አልፏታል፡ በሉዊስቪል የካንሰር መዝገብ ላይ እንደሞተች ተደርጋ ተመዝግባ ነበር።

65 ጠበቃው፡ ጂም ቶም ሮበርትሰን፡ ክርስቲያኑ ጠበቃ፡ ስለዚሁ ነገር ሲሰማ፡ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ፡ ወደ ባፕቲስት ሆስፒታል ሄደ፡ ምክንያቱም አባቱ በባፕቲስት ሆስፒታል፡ የቦርድ አባል ነበር። ጉዳዩንም መረመሩት፡

ሴትዮዋም ከዓመታት በፊት፡ እንደሞተች ተቆጥሮ ነበር። እርሷ ግን እዚሁ ጀፈርሰንቪል ውስጥ፡ ሆስፒታል ውስጥ በነርስነት እያገለገለች ትገኛለች። ልክ እዚህ ስትቆም፡ ሰዎች ደግፈው ይዘዋት በነበረበት ጊዜ፡ በራሷ አእምሮ እንኳን አልነበረችም። ነገር ግን **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነበር፡ እርሷም አሁን በሕይወት አለች። ሉዊስቪል ውስጥ፡ የነርስነት ስራዋን ቀጥላለች።

66 እዚሁ ታች የሺምፍ ከረሜላ መደብር ያለ፡ አንድ ሰው አለ። ዛሬ ማታ ሚስተር ሺምፍ እዚህ አለ? እዚህ ካለ፡ እርሱ ቢናገር ደስ ይለኛል። ሶኒ ሺምፍ፡ እጅግ ጤናማ ሰው ነው። ብዙ ጊዜ እኔ በፊት...

67 ይህንን መናገር ባልወድም፡ እውነቱ ግን ይህ ነው። ሳምንቱን ሙሉ ሰስራ አባቴ አስር ሳንቲም ይሰጠኝ ነበር፡ ከተማ መጥቼም እዚህ ከቦርድ አባላት፡ አንዱ በሆኑት በወንድም ማይክ ኢገን ቤት አካባቢ ብስክሌቴን አቆም ነበር። ከጂሚ ፑል ጋር፡ ልጁ ዛሬ ማታ እዚህ ያለ ይመስለኛል፡ እኔና ጂም፡ እንዲሁም አርነሰት ፊሽር፡ ወደ ከተማ ወርደን፡ በአምስት ሳንቲም ፊልም ለማየት እንገባ ነበር፡ የቀድሞዎቹንም ድምጽ አልባ ፊልሞች እናይ ነበር። ትንንሽ ልጆች ነበርን፡ ደስም ይለን ነበር፡ የሰምንት፡ የአስር ዓመት ልጆች አካባቢ ነበርን። ያ ዊሊያም ኤስ ሃርት የሚባል ሰው ነበር። ብዙዎቻቹ አታስታውሱትም፡ የድሮ ተዋናይ ነበር። ድምጽ አልባ ፊልም ነበር፥ እኔ ደግሞ ማንበብ አልችልም ነበር። የሚሆነውን ዝም ብዬ አይ ብቻ ነበር። ሁሉንም ነገር በጽሁፍ ያስነብብ ነበር፡ እኔ ግን ማንበብ አልችልም ነበር፡ ነገር ግን ምን እያደረገ እንደሆነ እከታተል ነበር።

68 ተጨማሪ አምስት ሳንቲምም ይኖረኝ ነበር። በአንድ ሳንቲም አይስክሬም ይገዛ እንደነበር ሰንቶቻችሁ ታስታውሳላችሁ? መልካም። ሦስት አይስክሬሞች፡ እንዲሁም በሁለት-ሳንቲም ደግሞ ሬድ ሆትስ የሚባሉ ከረሜላዎችን መግዛት እችል ነበር። አይስክሬሞቹን ይዤ ማቆየት ስለማልችል፡ ወዲያውኑ እበላቸው ነበር። በሁለት-ሳንቲም የምገዛው ሬድ ሆትስ ከረሜላ፡ ግማሽ ፓውንድ ገደማ ይመዝን ነበር። ይህንንም ሺምፍስ ያመርቱት ነበር። እኔም ወደዚያው ገብቼ፡ ፈታ ብዬ ተቀምጬ ዊሊያም ኤስ ሃርትን አየው ነበር።

69 ይህም ወጣት፡ ከእኔ በዕድሜ ትንሽ ከፍ የሚለው፡ በበሽታ ተመትቶ፡ አምስት ታዋቂ የሉዊስቪል ስፔሻሊስት ሐኪሞች ተሰፋ የቆረጡበት ሆኖ፡ ክብደቱም አርባ-አምስት ፓውንድ ገደማ ብቻ ደርሶ፡ እየሞተ ነበር። ሚሰስ ሞርጋን እርሱን ታስታምመው ነበር። እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ነበር! በጣም ብዙ ህመሞች ነበሩበት፥ ሳምባው ከጥቅም ውጪ ሆኖ ነበር፡ ጉሮሮውም ተበላሽቶ ነበር። ትንንሽ ክንዶቹ **ይህን** ያህል የሚያክሉ ነበሩ፡ በተኛበት፡ እየሞተ ነበር።

70 ሚሰስ ሞርጋንም ይህንን ስራ እንድትሰራ ተቀጥራ ነበር። ስለዚህም ለእርሱ፡ “እኔም በአንድ ወቅት የካንሰር ታማሚ ነበርኩ፡” በማለት ታሪኳን ልትነግረው ጀመረች።

71 እርሱም፡ “ማን አልሽ፡ ቢሊ ብራንሃምን? እንዴ፡” እንዲህ አለ፡ “እጅግ ብዙ የሬድ ሆትስ ከረሜላዎችንና የአይስክሬም ኮኖችን እኮ ሸጬለታለሁ።” በመቀጠል እንዲህ አለ፡ “መጥቶ ይጸልይልኝ ይሆን? ” እኔም ለጁኒ ሺምፍ ለመጸለይ ወደዚያው ሄድኩ።

72 አሁንም ልታናግሩት ከፈለጋችሁ፡ እዚሁ ታች ባለው የሺምፍ ከረሜላ መደብር ውስጥ ነው፡ ወረድ ብሎ፡ ከለርዝ ቲያትር አጠገብ፡ ወይም ሁለተኛው በር ላይ ነው። የሺምፍ ከረሜላ፡ እዚህ ያላችሁት ሁላችሁም የት እንዳለ ታውቃላችሁ። ማይ፡ በጀፈርሰንቪል ውስጥ ከተቋቋሙት እጅግ አንጋፋ መደብሮች አንዱ ነው።

73 እዚያ ተኝቶ፡ እየሞተ ሳለ፡ አምስት ስፔሻሊስት ሐኪሞች በሕይወት ለመኖር የሰዓታት ጊዜ ብቻ ሰጥተውት ነበር። **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** "አትሞትም፥ ነገር ግን በመደብሩ ባንኮኒ ላይ፡ ሬድ ሆትስ ትሸጥልኛለህ፡" የሚል ነበር። ለረጅም...

74 እርሱ እንደተፈወሰ አውቄ ነበር፡ ነገር ግን ያንን ከረሳሁት ረጅም ጊዜ አልፎ ነበር። እኔና ባለቤቴ፡ በገና በዓል ጊዜ እዚህ ሰንመጣ ጥቂት ከረሜላዎችን ለመግዛት ወደ ታች ወረድን። ስለ ሺምፍስ፡ እንዴት እንዳሰብን፡ አላውቅም። ምክንያቱም፡ አብዛኛውን ጊዜ፡ እዚህ አካባቢ ወዳሉት ፋርማሲዎች ጎራ ብለን እንገዛ ነበር፡ ሆኖም በሺምፍስ ፊት ለፊት ቆምን።

75 ወደ ውስጥ ሰገባ፡ እህቱ አይታኝ፡ "እንዴ፡ ወንድም ብራንሃም፡" አለች። እርሷም፡ "ጁኒን ታስታውሰዋለህን" አለች?

76 "አዎ፡" አልኩ። እዚያም፡ እጅግ ግዙፍ፡ ጠንካራና፡ ጤናማ-የሚመስል ሰው ቆሞ ነበር።

77 ወደ ባንኮኒው ተጠጋሁና፡ ተመለከትኩት፡ **እንደዚህ** ወደ ታች አቀረቀርኩ። "ከእነዚያ ሬድ ሆትስ አንድ ፓውንድ እወስዳለሁ፡" አልኩት።

78 እርሱም፡ "እሺ፡ ጌታዬ" አለ። ስለዚህ፡ እህቱም ባለቤቴን እያስተናገደች ነበር። ስለዚህም፡ ከረሜላዎቹን፡ አወጣቸው።

79 ራሴን እንዳቀረቀርኩ፡ "ከብዙ ጊዜ በፊት፡ እዚሁ ፊልም ቤት ውስጥ፡ እበላቸው ነበር"፥ አልኩት።

እርሱም፡ "አዎ፡" እንዲህ አለ፡ "ብዙ ልጆች ይህንን ይገዛሉ" አለ። እኔም፡ "አሁንም ይገዛሉ" አልኩት።

እርሱም፡ "ያንን ፎርሙላ አዘጋጅቶ የሰራው፡ አባቴ ነው" አለኝ። "በጣም ነው የምወዳቸው፡" አልኩት።

80 አሁን፡ ሁሉንም አዘጋጅቶ በእጄ ከሰጠኝ በኋላ፡ "ሌላ የሚያስፈልግህ ነገር አለ፡" አለኝ?

"አላውቅም፡" ብዬ፡ ቀና አልኩ። ኦህ፡ ማይ! እርሱም፡ "ወንድም ብራንሃም" አለ!

81 እኔም፡ "ከአምስት ዓመታት ገደማ በፊት፡ '**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡**' ብዬ የነገርኩህ፡ ሬድ ሆትስ ይኸው፡" አልኩት።

82 እርሱም፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ሙሉ በሙሉ ተፈውሼያለሁ፡ አንዲትም የቀረች የሕመም ምልክት የለችም። በአንደኛው ጆሮዬ የመሰማት ችግር ትንሽ አለብኝ" አለ። አሁን በሃምሳዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ ይመስለኛል። እርሱም፡ "በአንደኛው ጆሮዬ የመሰማት ችግር ትንሽ አለብኝ፡ ምክንያቱም እዚያ

በነበርኩበት ጊዜ እጅግ ብዙ አንቲባዮቲክስ ሰጥተውኝ ስለነበር ነው” አለ። የኢየሱስ ክርስቶስ ድንቅ ጸጋ!

83 አሁንም ሌላ ነገር ለመናገር ብዙ ጊዜ የለኝም፡ ነገር ግን ይ—ይ—ይህንን መግለጫ መስጠት እፈልጋለሁ።

84 ስንቶቻችሁ ስለ ሽኮኮዎቹ ታስታውሳላችሁ? መልካም። ያ በሕይወቴ፡ ፈጽሞ ልረዳው ያልቻልኩት፡ ግራ የ—የሚያጋባ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነበር።

85 ግራ ያጋባኝ ሌላም ነገር ነበር፡ ይኸውም እግዚአብሔር ማንኛውንም ነገር ማድረግ ከሚያውቅበት መንገድ የተሻለውን መንገድ ሙሴ ለእግዚአብሔር ሊነግረው በቻለ ጊዜ ነው፡ ይኸውም ሙሴ፡ “ሕዝቡ፡ ‘አምላካችሁ ሊያወጣችሁ ቻለ እንጂ፡ ሊጠብቃችሁ አልቻለም’ ይላሉ” ባለ ጊዜ፡ ሙሴ በክፍተቱ ራሱን አሳልፎ በሰጠ ጊዜ ነበር። ከዚያም ቆየት ብዬ፡ በሙሴ ውስጥ ሆኖ፡ ለህዝቡ የቆመው፡ ክርስቶስ እንደነበረ ደረስኩበት። አያችሁ?

86 ስለዚህ በእርሱ ላይ ፈጽሞ ሰብኬበት በማላውቀው፡ በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ “ይህን ተራራ፡ ‘ተነቀል’ ብትሉት” የሚል ነው። ታሪኩንም ስለምታውቁት፡ ያንን አልፈዋለሁ። አሁን፡ ያ ወደ ምን እያመራ እንደነበረ ቅንጣት ታክል አላውቅም ነበር። ያ ሲከሰት፡ ወይም እዚያው ከተፈጸመ በኋላ ወዲያውኑ በቦታው የነበሩት፡ ወንድም ውድና ወንድም ፍሬድ፡ እንዲሁም ከእነርሱ ጋር የነበሩት፡ እዚህ ሕንጻ ውስጥ ያሉ ይመስለኛል።

87 እዚያ ታች ከኬንታኪ የመጡት ወንድም ሮድኒና፡ ወንድም ቻርሊ፡ የእህት ውድ ወንድምና ከእነርሱ ጋር የነበሩት ይህ ነገር እዚያው ኬንታኪ ውስጥ ሲፈጸም በቦታው ነበሩ፡ ይህም የተከሰተበት ሁለተኛው ጊዜ ነበር። በቀላሉ ያልነበሩትን ነገሮች በመናገር ብቻ፡ ወደ መኖር ማምጣት ነው። አያችሁ? ሁልጊዜ፡ በመናገር፡ መጽሐፍ ቅዱስን በማጽናትና፡ በማበረታታት ነበር።

88 ለሦስተኛ ጊዜ የሆነው በሃቲ ራይት ላይ ነበር። ሃቲ ዛሬ ማታ እዚህ አለችን? የኢዲዝ... ስንቶቻችሁ ናችሁ ሃቲ ራይትን የምታውቁት? ያ ሲሆን እኔና ወንድም ውድ እዚያ ተቀምጠን ነበር፡ መንፈስ ቅዱስም፡ “የምትፈልገውን ስጣት” ባለ ጊዜ፡ እነዚያ ሽኮኮዎች እንዴት ወደ መኖር እንደመጡ፡ እየተነጋገርን ነበር።

89 እኔም፡ “ዋናው ነገር፡ እርሱ ይሖዋ-ይሬ መሆኑ፡ ነው። አብርሃም አውራ በግ ባስፈለገው ጊዜ፡ እግዚአብሔር ያንን በግ አዘጋጀለት። ሽኮኮዎቹንም አዘጋጀ። በጉን ተናግሮ እንዳስገኘው ሁሉ፡ ሽኮኮንም ተናግሮ ሊያስገኝ ይችላል፡ ምክንያቱም እርሱ ፈጣሪ ነውና። አብርሃም ፈጽሞ ያንን አልጠየቀም። ዝም ብሎ ሊያደርገው በመንገዱ ይሄድ ነበር፡ ይህ ግን ይሖዋ-ይሬ እዚያ እንደነበረ የሚያሳይ ነበር” አልኩ።

90 ያንን በተናገርኩ ጊዜ፡ አንዲት ትሁት ምስኪን ሴት... ይህ ነገር ሲከሰት ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ሦስተኛው ሰህበት፡ በሰው ልጅ ላይ ሲሆን፡ በአንዲት ምስኪን፡ ትሁት ሴት ላይ ነበር።

91 እርሷም፡ ለኑሮዋ፡ ከትንሽ እርሻዋ የምታገኘው፡ በዓመት ወደ ሁለት መቶ ዶላር ገደማ ብቻ ነበር። ባሏ የሞተባት ሲሆን፥ የማይታዘዙ ሁለት ልጆች ነበሯት። መጥታም ከዚያ ላይ፡ ሀያ ዶላር፡ ለዚህ ተበርናክል ግንባታ ሰጠች።

ሚዳ ደግሞ በዚያ ጧት ለሸቀጣ ሸቀጥ መግዣ፡ ሀያ ዶላር ሰጥታኝ ነበር፡ ወደዚያ ሰወርድም፡ ገንዘቡን ልመልስላት አስቤ ነበር፡ ስለዚህም እሷ መክፈል አይጠበቅባትም ነበር። ነገር ግን ልትቀበለኝ አልቻለችም። በዚያን ጊዜም...

92 እሷም ወደኋላ በጥግ ተቀምጣ ነበር፡ እኔም እንዲህ ባልኩ ጊዜ፡ "እኔ የማውቀው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ይህም፡ እሱ አሁንም ይሖዋ-ይሬ መሆኑ ነው።"

93 ያኔ ምስኪኗ ሃቲም ትክክለኛውን ቃል ተናገረች። እርሷም፡ "ይህ ከእውነት በቀር ሌላ ምንም አይደለም" አለች።

94 ያንንም ስትናገር፡ እዚህ ያለው ወንድም ባንክስ ውድ በዚያ ከነበሩት አንዱ ነው፡ ክፍሉ የሚፈራረስ ይመስል ነበር። መንፈስ ቅዱስም፡ ስለ ሽኮኮዎቹ የተናገረው ያው ድምጽ፡ "የምትጠይቀውን ነገር ስጣት፡" አለ።

95 እኔም፡ "እህት ሀቲ፡ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ምስክር ሆኜ እላለሁ፡ ይሄው ነው በቃ። አሁን፡ በአእምሮሽ ውስጥ አንዳች ጥርጣሬ ከሌለ፡ የምትፈልጊውን ነገር ጠይቂ፡ ያም በእቅፍሽ ላይ ካልተቀመጠ፡ እኔ ሀሰተኛ ነቢይ ነኝ" አልኳት።

96 እሷም፡ "ወንድም ብራንሃም" አለች። ሁሉም ሰው ያለቅስ ነበር። "ምን ልጠይቅ፡" አለች?

97 እኔም፡ "አንቺ ድሃ ነሽ፡ ያለገንዘብም፡ እዚያ ማዶ ባለው ኮረብታ ላይ ነው የምትኖሪው፥ ስለዚህ ጉዳይ ልትጠይቂ ትችያለሽ። ለዓመታት፡ የጸለይንላት እዚህ የተቀመጠች፡ ኢዲት የምትባል አካለ ስንኩል፡ ምስኪን እህት አለችሽ፥ ለእርሷ መፈወስ ልትጠይቂ ትችያለሽ።" እንዲህ አልኩ፡ "አባትሽና እናትሽ አርጅተዋል ደግሞም አቅም አንሷቸዋል፥ ስለ እነርሱ ልትጠይቂ ትችያለሽ። የምትጠይቂውን ማንኛውንም ነገር፡ እህት ሀቲ፡ አሁኑኑ፡ መሆኑን ወይም አለመሆኑን አሁን ተመልከቺ" አልኳት። እንዲህም አልኩ፡ "እርሱ አሁን ነግሮኛል፡ ያው ድምጽ፡ 'የምትጠይቀውን ነገር ስጣት' ብሎኛል፡" አልኳት።

98 እሷም ዙሪያዋን ተመልክታ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ምን ልበል፡" አለች?

99 እኔም፡ "ፍላጎትሽ የሆነውን ነገር ተናገሪ። ከሁሉ የሚበልጠውን ታላቁን ፍላጎትሽን አስቢና፡ ተናገሪው" አልኳት።

100 ወንዶች ልጆቿም ሳይቀር እያሾፉና እየሳቁ ነበር። እሷም፡ "ያለኝ ከሁሉ የሚበልጠው ታላቅ ፍላጎቴ የሁለቱ ልጆቼ መዳን ነው" አለች።

101 እኔም፡ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ሰጥቼሻለሁ" አልኳት፡ እነርሱም ወዲያውኑ ጌታን ተቀበሉ።

102 እነርሱም በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ በጌታ እራት፡ እነዚያ ትናንሽ ልጆች ከሰዎች ጋር እዚያ ተቀምጠው እግር በማጠብና፡ በመሳሰሉት ነገሮች ታማኞች ሆነው ቆይተዋል። ሁላችንም ለዚህ ምስክሮች ነን።

103 እሷ እውነተኛ ምርጫ አድርጋ ነበር። እናቷ መሞቷ አይቀርም፡ እሷም ብትሆን፡ ሁሉም መሞታቸው አይቀርም። ነገር ግን የጠየቀችው ነገር የዘላለም ነው፡ ይኸውም የልጆቿ መዳን ነው። ያም ይህ ነገር ሲሆን ለሦስተኛ ጊዜው ነበር።

104 ለአራተኛ ጊዜ የሆነው፡ ለመጨረሻ ጊዜ እዚህ በነበርኩበት ጊዜ እንዳብራራሁት፡ ያ ማዕበል እያስገመገመ በነበረበት ተራራ ላይ ነበር።

ስንቶቻችሁ ስምታችሁታል? ኦህ፡ ሁላችሁም። መልካም። ማዕበሉ እያስገመገመ በነበረበት ስፍራ። እዚህ ስቆም እግዚአብሔር ፈራጄ ነው፡ ከተራራው እየወረድን ሳለ...

105 ዴቪድ ውድ፡ እዚህ የሆነ ቦታ ያለ፡ ይመስለኛል፡ ሳንድዊች ሰርቶልኝ ነበር፡ እሱም በጣም የሚገርም ነበር! ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ ለአባቱ ከሰራሁት ጋር ብድሩን እየመለሰልኝ የነበረ ይመስለኛል። ቦሎኛ፥ ስ—ስጋ እንዲሁም ሁሉንም ነገር በአንድ ላይ ቀላቅሎበት ነበር። እኔም ሸሚዜ ውስጥ ከተትኩት፡ ዝናብም ዘነበበት፡ ልክ እንደ አንድ ትልቅ የተቦካ ሊጥ ሆኖ አገኘሁት።

106 ከተራራውም እየወረድኩ ነበር። ማዕበሉ በጣም ኃይለኛ ስለነበር፡ ከፊቴ ያለውን እጄን እንኳ፡ በጭንቅ ነበር ማየት የምችለው። እኔም የማውቀው፡ አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ነፋሱ እጅግ ስለሚያሽከረክር፡ አቅጣጫችሁን ትስታላችሁ።

አሁንም ለዚህ፡ እዚህ ምስክሮች አሉ።

107 ከእነርሱም አንዱ ከታማኝ ዲያቆኖቻችን አንዱ የሆነው፡ ወንድም ዊለር ነው። እዚህ ነህ እንዴ፡ ወንድም ዊለር? የት ነው ያለው? አዎ፡ እዚህ አለ፡ ወንድም ዊለር።

108 ከኒው አልባኒ የመጣው የሜቶዲስት ሰባኪ፡ ወንድም ማን። ወንድም ማን፡ ዛሬ ማታ፡ እዚህ አለ እንዴ? እዚህ ይኑር አይኑር አላውቅም።

109 ወንድም ባንክስ ውድ። እዚህ ነህ፡ ወንድም ባንክስ? እርሱ ድምጽ መቅረጫ ክፍል ውስጥ ነው። መልካም። ዴ—ዴቪድ ውድ።

110 ወንድም ኢቫንስም በዚያ የነበረ፡ ይመስለኛል። ልክ ነው፡ ወንድም ኢቫንስ? ግድግዳውን ተደግፎ የቆመው፡ ወንድም ኢቫንስ፡ በዚያ ነበር።

111 ከዚያ ሁለት ቀናት በፊት፡ "ኃይለኛ የበረዶ ማዕበል ምድሪቱን እየጠራረጋት ነው፡" በማለት ለቀናት እንዴት ሲያስተላልፉ እንደነበር።

112 ወንድም ቶም ሲምፕሰንም ዛሬ ማታ እዚህ ይገኛል። ከካናዳ በሚወርድበት ጊዜ፡ ማለፍ ስለማይችል ያንን ቦታ ትቶት እንዲያልፍ ጠይቀውት ነበር፡ "የበረዶ ማዕበል እየመጣ ነበርና።" ወንድም ቶም፡ እዚህ ነህ? የት ነው ያለኸው? ይኸው፡ እዚህ ተቀምጧል።

ከዚያም ደመናዎቹ መጡ። እኔም፡ "ወንድሞች... "

113 ሁሉም ተጣድፈው ወጡ። እዚያ ኋላ ከነበሩት መቶ ምናምን ሰዎች ውስጥ፡ ማንም አልነበረም፡ ከትንሹ ቡድናችንና ከከብት አረኛው፡ ከፈረሰኛው በቀር እዚያ ኋላ ማንም አልነበረም። እኛ ግን እዚያ ልንቆይ ነበር።

114 ለእህት ኢቫንስ ደውዬ፡ ለባለቤቴ እንድትደውልና፡ "መውጣት ካልቻልኩ፡ ለቢዝነስ መን የቁርስ ፕሮግራም የሚያካሂድ ሌላ ሰው እንዲፈልጉ" ለቶኒ እንድትነግረው አደረግሁ።

115 በ—በዚያች ቀንም ተራራው ላይ ሳለን፡ እንዲህ አልኩ፡ "አሁን የመጀመሪያው፡ ትንሽ ዝናብ ሲጀምር፡ ወይም ማንኛውም ነገር ሲፈጠር፡ ወደ ካምፑ ተመለሱ።" እንዲህም አልኩ፡ "እነዚያ የበረዶ ማዕበሎች ሲመጡ... በአስር ወይም በአስራ አምስት ደቂቃ ውስጥ ከፊታችሁ ያለውን እጃችሁን

ማየት አትችሉም፡ በተራራውም ላይ፡ በትንሽ ጊዜ ውስጥ ሃያ ጫማ የሚያህል በረዶ ይከምራል” አልኩ።

116 ሰዎች እዚያ ኋላ ቀርተው እንዴት እንደሚጠፉና፡ የመሳሰሉትን ነገሮች፡ በጋዜጣ ላይ የምታነቡት፡ በዚህ ምክንያት ነው። ዳሩ ግን እኛ እንዴት መውጣት እንዳለብን እናውቅ ነበር፡ እነርሱም የት እንደነበርን ያውቁ ነበር፡ ስለዚህም እዚያ እንድንቆይ እንደተመራን ተሰማን።

117 ስለዚህ በተራራው ላይ፡ ያ የበረዶ ማዕበል ሲጀምር፡ ወደ ታች መውረድ ጀመርኩ። ከጀመርኩበት ስፍራም ግማሽ ማይል ያህል ብቻ ርቄ ነበር፡ የእግዚአብሔርም ድምጽ፡ “ተመለስና ወደ ኋላ ሂድ” አለ።

118 ዴቪድ የሰጠኝን ያንን ሳንድዊች በልቼ ለተወሰነ ጊዜ ከቆየሁ በኋላ፡ እርሱ እንደነገረኝ ተመለስኩ፡ ወደዚያም ተመልሼ በመውጣት ተቀመጥኩ።

119 በዚያም ተቀምጬ ሳለሁ፡ ያም ነፋስ እያሽከረከረና እየነፈሰ፡ የዛፎቹም ጫፎች በጣም ወደ ታች ጎንበስ እያሉ፡ በረዶውና ውርጩም በዚያ ሁኔታ እየበረረ ሳለ፡ አንድ ድምጽ፡ “እኔ የፍጥረት አምላክ ነኝ” አለ።

120 ቀና ብዬ ተመለከትኩ፡ እኔም፡ “ያ ከየት ነበር? ምናልባት፡ ነፋሱ ይሆናል” ብዬ አሰብኩ።

121 እርሱም፡ “ሰማያትንና ምድርን ፈጠርሁ። በባህር ላይ ያሉትን ኃይለኛ ነፋሳት ጸጥ አሰኘሁ” አለ፡ መናገሩንም ቀጠለ።

እኔም ዘልዬ ተነሳሁና ባርኔጣዬን አወለቅሁ።

122 እርሱም፡ “ማዕበሉን ተናገረው፡ እርሱም ጸጥ ይላል። የምትናገረው ማንኛውም ነገር፡ ያው ይሆናል” አለ።

123 እኔም፡ “ማዕበል ሆይ፡ ጸጥ በል። ፀሐይ ሆይም፡ ከዚህ እስክንወጣ ድረስ፡ ለአራት ቀናት በተለመደው ሁኔታ አብሪ፡” አልኩ።

124 ያንንም ተናግሬ እንዳበቃሁ፡ ውርጩ፡ በረዶውና ሁሉም ነገር ቆመ። በአንድ ወይም በሁለት ደቂቃ ውስጥም፡ ሞቃታማዋ ፀሐይ በጀርባዬ ላይ ታበራ ነበር። ነፋሳቱ **እንደዚህ** ሲነፍሱ፡ ከሰሜን ሲመለሱ፡ ወደ ታች ሲወርዱ… ማለቴ ከምስራቅ፡ ከምስራቅ ሲመጡ አየሁ። ከምዕራብ ይመጣ ነበር፡ ነፋሳቱም አቅጣጫቸውን ቀየሩና **ወደዚህ** ተመለሱ። ደመናዎቹም፡ ልክ እንደ ሚስጥራዊ ነገር፡ ወደ አየር ተነሱ፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥም ፀሐይዋ ታበራ ነበር።

125 ከዚያም ጌታ ኢየሱስ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እዚያ ታች ስላለችው ባለቤቴ፡ እንደምታውቁት፡ ወደዚያ ስለወጣሁበት ጉዳይ ተናገረኝ። ትዳር ከያዝን ሃያ-ሁለት ዓመታት አልፈዋል፡ ሆኖም በአኒቨርሰሪ ቀን ከቶ እቤት ውዬ አላውቅም። በመጀመሪያው በአኒቨርሰሪ፡ በመጀመሪያው፡ በሠርጋችን ዕለት፡ ምን መሰላችሁ፡ ለአደን ይዣት ሄድኩ። ምክንያቱም፡ የአደን ጉዞ ለማድረግም ሆ—ሆ—ሆነ የጫጉላ ሽርሽር ለማድረግ፡ አቅም ስላልነበረኝ፡ እንደምንም እ—አጣምሬ፡ አደረግሁት። ስለዚህም፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ እያደንኩ ቆይቻለሁ። እርሷን በያዝኩበት ሁኔታም የጸጸት ስሜት ተሰማኝ።

አሁን፡ ይህ ሲሆን ለአራተኛ ጊዜው ነበር።

126 አሁን እዚህ ል—ልናገረው የምፈልገው ነገር አለ፡ እውነቱንም በትክክል መናገር አለብኝ። ከዓሰራ ሰድሰት ዓመታት ገደማ በፊት ከወንድም ጆን ሻሪት ጋር ካሊፎርኒያ ውስጥ ነበርኩ፡ ሰብሰባም እያካሄድኩ ነበር። እኔና ሚዳ፡ እንዲሁም ወንድም ሻሪትና እህት ሻሪት፡ ሌሎቹም፡ በአንድ ሆቴል ውስጥ አርፈን ነበር። ፖል መሊኪያን የተባለ፡ እዚህ ታበርናክል ውስጥ ብዙ ጊዜ የቆመ አንድ ሰው ነበር፥ እርሱም ሀብታም አርመናዊ ነው። ባለቤቱም በሚኖሩበት በፍሬሰኖ፡ ካሊፎርኒያ፡ ልጅ ወልዳ ነበር፥ እርሱም ባለቤቱን ይዞ፡ ወደ ታች መጣና፡ ሆቴል ውስጥ ደውሎልኝ፡ እንዲህ አለ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ባለቤቴን ላመጣት እችላለሁን" አለኝ?

እኔም፡ "አዎ፡ ትችላለህ" አልኩት። በሚቀጥለው ቀን፡ ወደ ካታሊና ልሄድ ነበር።

127 ስለዚህ ባለቤቱን አመጣ፡ ትንሿም እመቤት በጣም ታማ ነበር! እሷም ስትታይ... እኔም፡ "እህት መሊኪያን፡ እጅሽን በእጄ ላይ አድርጊው" አልኩ፡ "ጌታ ይነግረን እንደሆነ እናያለን፡" አልኩ። እጆቿንም በላዬ ላይ እንዳደረገች ወዲያው፡ "ኦህ፡ የእግር ደም ሰር መታፈን ነው፡" አልኩ።

እሷም፡ "ምንም ዓይነት ምልክቶች ያሉብኝ አይመስለኝም" አለች።

128 እኔም፡ "ተመልከቺ" አልኳት። በሁለት ቀናት ውስጥም፡ ለዚያ የእግር ደም ሥር መታፈን ህክምና ያደርጉላት ነበር።

129 ልክ እዚህ እንዳለው እንደ ጂሚ ቱል ልጅ፡ ትንሿ ሕፃን ልጁ። በቀደም የልብ ድካም እንዳጋጠመው አሰበው፡ ይዘውት መጥተው ነበር፡ ነገር ግን የአሰም ህመም ነበር። እኔም እጄን በላዩ ላይ አደረግሁ። እኔም፡ "ለተወሰኑ ቀናት ተመልከቱት፥ ኩፍኝ ይዞታል። እየወጣ ነው። ትኩሳቱም የዚያ ነው" አልኩ። ትላንት ማታ አግኝቼው ነበር። ሰውነቱ ላይ ሁሉ፡ ኩፍኝ፡ እንዳወጣበት ነገረኝ። አያችሁ?

130 አሁን፡ ሰለዚያ እጅ ሰለማድረግ፡ ከእህት መሊኪያን ጋር እያወራሁ ነበር። እሷም፡ "ያንን መመልከት የሚያሰገርም ነገር ነው፡ ወንድም ብራንሃም፡" አለች። እሷም፡ "ያ በሁሉም እጅ ላይ ይሠራልን" አለች?

131 እኔም፡ "መልካም፡ በሽተኛው ላይ አንዳች ችግር ካለ ነው" አልኩ። እኔም፡ "እንግዲህ እዚህ፡ እጄን አሰቀምጣለሁ" አልኩ፡ ከእናንተም ብዙዎቻችሁ ቆማችሁ ተመልክታችኋል፡ እርሱም አንዳች ነገር አላሳየም። እኔም እንዲህ አልኩ፡ "እነሆ፡ ባለቤቴ ምንም ችግር የለባትም፡ እጇን ብታደርግ... "

132 "ውዴ፡ ተመልከቺ፡ እጅሽን በእጄ ላይ አድርጊው።" ባለቤቴም፡ እዚያ ተቀምጣ ነበር። እጇንም በእጄ ላይ አደረገች። እንዳደረገችም ወዲያው፡ "በግራ ኦቫሪሽ ላይ እጢ አለብሽ። በእርግጥም የማህፀን ህመም አለብሽ፡" አልኳት።

እሷም፡ "ምንም የተለየ ነገር አይሰማኝም" አለች።

133 እኔም፡ "ነገር ግን አለብሽ" አልኳት። ቤኪ የሁለት ዓመት ልጅ ነበረች። ቀደም ሲል፡ የተጫወተችልን ልጄ፡ በዚያን ጊዜ የሁለት ዓመት ልጅ ነበረች።

134 ከሁለት ዓመታት በኋላም፡ ሳራ ተወለደች፡ ያም ሲሆን... የተወለደችው በቀዶ ጥገና ነበር። እኔም እዚያ ኮሪዶን ያ—ያለውን፡ ሀኪማችንን ዶክተር

ዲልማንን፡ እ፡ "በቀዶ ጥገና ስትከፍታት፡ ያንን የግራ ኦቫሪዋን ተመልከተው" ብዬ ጠየቅሁት፡ እርሱም ተመለከተው።

እርሱም፡ "እኔ እንዳየሁት፡ ምንም ችግር የለም" አለ። እጄን ሳደርግ፡ አሁንም እዚያው ነበረ።

135 ከአራት ዓመታት በኋላም ጆሴፍ ተወለደ። ሀኪሙንም እንደገና እንዲመለከት ጠየቅሁት። "እኔ እንዳየሁት፡ ምንም ችግር የለም" አለ። እጄን ሳደርግ፥ አሁንም እዚያው ነበረ። ስለዚህ ስለ ጉዳዩ ረሳነው።

136 አሁንም ይህ መናገር ያለብኝ ነገር ነው። ይህን መናገር አልወድም፡ ነገር ግን እውነቱን መግለጽ አለብኝ፡ አያችሁ፡ እናንተም የምትፈልጉት ያንን ነው። ምንም ይሁን ምን፡ ሁልጊዜ እውነትን ተናገሩ።

ዓመታት አልፈዋል፡ እኛም ይህን ከቶ አላስተዋልነውም ነበር።

137 ይህንንም የምናገረው፡ እርሷ እዚያ ስለተቀመጠች አይደለም፡ እርሷ በሌለችበትም ጊዜ ይህንኑ ስለምናገር ነው። ያንንም ታውቃላችሁ። በዓለም ላይ ከባለቤቴ የምትበልጥ የተሻለች ሚስት ልትኖር ትችላለች ብዬ አላምንም፡ ሁልጊዜም እንደዚያው ሆና እንደምትቀጥል ተስፋ አደርጋለሁ። እኔም ታማኝ ባል መሆን እፈልጋለሁ፡ በዚህ ህንፃ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ወጣት፡ ሲያገባ፡ ልክ እንደ ባለቤቴ ያለች ሚስት እንዲያገኝ ተስፋ አደርጋለሁ። በዚህ ሁኔታ ለምን ያህል ጊዜ እንደምንኖር አላውቅም፡ ነገር ግን በምድር ላይ ባለን ቀሪ ዘመን ሁሉ እንዲህ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። አብረንም በጣም ደስተኞች ሆነን ቆይተናል። እንዳገባት የነገረኝ እግዚአብሔር ነበር።

138 በተመሳሳይ ጊዜም፡ እርሷ ሳታውቅ፡ እኔ ላላገባት እሞክር ነበር፥ ያም ስላልወደድኳት አይደለም፡ ዳሩ ግን ላስተዳድራት እችላለሁ ብዬ ስላላሰብኩ ነበር። እሷም ግሩም ሴት ነበረች፡ እኔም ለዚያ የተገባሁ አልነበርኩም።

139 ለመጸለይም ወጣች፡ መጽሐፍ ቅዱሱንም ከፈተች። ሳስበው... እሷም፡ "ጌታ ሆይ፡ ከዚህ በፊት ይህንን አድርጌ አላውቅም፡ ነገር ግን የሚረዳኝን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስጠኝ። እርሱን መርሳት ካለብኝ፡ መርሳት አለብኝ" አለች። መጽሐፍ ቅዱሱንም ስትከፍት...

140 ወደ አንዲት ትንሽ ጎጆ ወጥታም ጸለየች። መጽሐፍ ቅዱሱንም ስትከፍት፡ "ሚልክያስ 4። እነሆ፡ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ... " ያ—ያም የሆነው ከሃያ ምናምን ዓመታት በፊት ነበር፡ ስለዚህ ዘመን አገልግሎትም ምንም አታውቅም ነበር። እኔም... አልችልም ነበር...

141 እዚያ ወንዙ ዳር ተኝቼ ነበር። አንድ ማታም፡ ከእንቅልፌ አ—አነቃኝ፡ እዚያ በሩ አጠገብ ሲቆም ሰማሁት። እርሱም፡ "ሂድና ውሰዳት፡ ሠርጋችሁም በሚመጣው ጥቅምት ሃያ-ሦስት ይሆናል፡" አለኝ። ያደረግሁትም ፈጽሞ ያንኑ ነበር። በደስታም ኖረናል። በእግዚአብሔር ጸጋ፡ አንዲትም ክፉ ቃል ተለዋውጠን አናውቅም። እሷም እጅግ ተወዳጅ ነበረች።

142 አንድ ቀንም ወደ ቤት ገባሁ። በአገልግሎት በመሄዴም፥ እነዚህን ልጆች ብቻዋን ማሳደግ ግድ ሆኖባት ነበር። ብዙ ሴቶች ይህንን አይታገሱም፥ ያንንም ታውቃላችሁ፡ ሁኔታው ይከብዳቸው ነበር። ከዚያም ወደ ቤት ስገባ፡ አንድ ነገር ወይም ሌላ ነገር ተናገረች። እዚያ ኋላ ጆሴፍ አለን፡ እርሱም... በእርግጥም

ሙሉ ወንድ ልጅ ነው! ልክ እንደ እኔም፡ በእናቱ ራስ ላይ ለወጣው ሽበት እርሱም የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል። ስለዚህ በእርግጥም ሙሉ ወንድ ልጅ ነበር፡ በጣም መጥፎ ነገርም አድርጎ ነበር። እኔም እንዲህ አልኳትና... እሷም፡ “ቢል፡ ግረፈው” አለችኝ።

እኔም፡ “በቃ ልቤ አልጨከነም” አልኳት። አያችሁ?

143 እሷም፡ “አዎ፡ አንተም ችግሩን መቋቋም ቢኖርብህ ኖሮ፡” ብላ በሩን ፊቴ ላይ በኃይል ዘጋችብኝ።

144 “መልካም፡” እኔም፡ “ምንም አይደለም። ምስኪኗ ያንን አስባ አይደለም” ብዬ አሰብኩ።

145 መኪናዬን ለማጠብም ወደ ውጭ ወጣሁ። እዚያም ሰወጣ፡ መንፈስ ቅዱስ ያንን አልወደደውም፥ እርሱም፡ “ሄደህ ንገራት” አለኝ፡ ሁለተኛ ዜና መዋዕል፡ 22ኛ ምዕራፍ ይመስለኛል። አልነገርኳትም። መጀመሪያ ላይ፡ በህሊናዬ ያሰብኩት፡ ብቻ መሰሎኝ ነበር። ማጠቤን ብቻ ቀጠልኩ። እንደገና፡ “ይህንን እንድታነብ ሄደህ ንገራት” አለኝ።

146 ገብቼም መጽሐፍ ቅዱስን አመጣሁ፡ አነበብኩትም። ያም የሆነው ሙ-... ወይም ነቢዪቱ፡ ማርያም፡ ኢትዮጵያዊት ሴት በማግባቱ ምክንያት፡ በወንድሟ በሙሴ ላይ፡ ባሾፈችበት ክፍል ነበር፡ እግዚአብሔርም ያንን አልወደደውም። እርሱም፡ “ይ—ይህን ከ—ከምታደርግ፡ አባቷ ፊቷ ላይ ቢተፋባት ይሻል ነበር” አለ።

147 ስለዚህ፡ ማርያም ሰውነቷ ላይ ሁሉ፡ ለምፅ ወጣባት። አሮንም መጣ፡ ለእህቱ ነገራት፡ እንዲህም አለ... ወይም መጥቶ ለወንድሙ ነገረው፡ “በለምጽ፡ እየሞተች ነው፡” አለው።

148 ስለዚህ ሙሴ በመሠዊያው አጠገብ፡ ሰለ እርሷ ሊማልድ ሮጦ ገባ። ያንንም ባደረገ ጊዜ፡ የእሳት ዓምድ ወረደ፡ እግዚአብሔር። እርሱም፡ “ሂድና እርሷንና አሮንን ጥራ፡ ወደዚህም አምጣቸው።” ለካ አሮንም፡ በጉዳዩ ውስጥ ነበረበት። ስለዚህ፡ “ጥራቸውና ወደዚህ ና” አለው።

149 እርሱም፡ “በመካከላችሁ ማንም ቢኖር፡” እግዚአብሔር አሁን ለእነርሱ እየተናገረ ነው፡ “መንፈሳዊ፡ ወይም ነቢይ የሆነ፡ እኔ እግዚአብሔር ራሴን ለእርሱ እገልጣለሁ። በራእዮች እናገረዋለሁ፡ በህልሞችም ራሴን ለእርሱ እገልጣለሁ፡ ደ—ደግሞም ህልሞችን እፈታለሁ፡ ወዘተ” አለ። እርሱም፡ “ነገር ግን ባሪያዬ፡ ሙሴ፡ በምድሪቱ ላይ እንደ እርሱ ያለ ማንም የለም” አለ። እንዲህም አለ፡ “ከእርሱ ጋር አፍ ለአፍ እናገራለሁ” አለ። እርሱም፡ “እግዚአብሔርን አልፈራችሁምን” አለ? አያችሁ፡ እግዚአብሔር ያንን አልወደደውም።

150 መልካም፡ ያንን ባየሁ ጊዜ፡ ሮጬ ገባሁ። እሷም በሌላኛው ክፍል ውስጥ ነበረች። በሩን አንኳኳሁ። በራሷ ላይ ቆልፋ ነበር። ላነጋግራት እንደምፈልግም ነገርኳት። ወደዚያም ገብቼ አነጋገርኳት፡ ምን እንደሆነ ልነግራትም ሞከርኩ። እኔም፡ “የኔ ውድ፡ እንዴት እንደምወድሽ ታውቂያለሽ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ያንን አልወደደውም። ያንን መናገር አልነበረብሽም” አልኳት። ከዚያም ወዲያው፡ ጎኗ ላይ ህመም ጀመራት።

151 እዚህ ሉዊስቪል ወደሚገኝ፡ ዶክተር አርተር ሾን ወደተባለ ሐኪም ወሰድናት፡ እርሱም ከአሥራ አምስት ወይም አሥራ ስድስት ዓመታት በፊት እኔ አግኝቼው የነበረውን እብጠት፡ በግራ ኦቫሪዋ ላይ አገኘባት። “በግራ ኦቫሪዋ ላይ ያለው እብጠት፡ ልክ የገውዝ ፍሬ ያክላል።”

እኔም፡ “ታዲያ ምን ይሻላል፡ ዶክተር” አልኩት?

152 እርሱም፡ “ምን እንደሚፈጠር እንይ። ከጥቂት ወራት በኋላ፡ ምናልባትም ከሁለት ወር ገደማ በኋላ ይዘሃት ተመለስ” አለኝ።

153 መልሰን ወሰድናት። እብጠቱ ከገውዝ ፍሬነት አድጎ፡ ሎሚ የሚያክል ሆኖ ነበር። እርሱም፡ “ይህ ነገር ቢወጣ ይሻላል፥ ከላላና ወደ አደገኛነት ከተቀየረ” አለ።

154 እኔም፡ “እሺ፡ ማይ” አልኩ፡ እንዲህ አልኩ፡ “ወ—ወደ ቱሰን እንሄዳለን። ጌታ ወደ ቱሰን ልኮኛል” አልኩ።

155 ኃላፊነቱን መውሰድ ስላልፈለገ፥ ወደ የማህፀን ስፔሻሊስት ሐኪም ላካት። ስለ አገልግሎቴም ለዚያኛው ሐኪም ነግሮት መሆን አለበት፡ ምክንያቱም... የማህጸን ስፔሻሊስቱ፡ “ግዴታ መውጣት አለበት” አለ። ስለዚህ እንዲህ አለ... ወ—ወደ ቱክሰን እንደምንሄድ ነገርነው። እርሱም፡ “መልካም፡ እዚያ በጣም የቅርብ ጓደኛዬ የሆነ፡ አንድ ስፔሻሊስት አለኝ። እኔ ቀደም ሲል ቱክሰን እኖር ነበር” አለ። “ወደ እርሱ እልካችኋለሁ፡” አለን።

156 ስለዚህ ደብዳቤ ጽፎ ላከለትና፡ “ወይዘሮ ብራንሃም ግሩም ሴት ናት፡” እያለ፡ እንዲሁ ቀጠለ። እንዲህ አለ... የእብጠቱን መጠን የሚያሳይ ዲያግራምና፡ የመሳሰሉትን ላከለት። በዚያን ጊዜ ወደ እብጠትነት ተቀይሮ ነበር፥ መጠኑም ምን ያህል እንደሆነ ገልጿል። እንዲህም አለ፡ “እውቃለሁ... ” ታውቃላችሁ፡ እርሱ ያውቅ ነበር... እኔን “መለኮታዊ ፈዋሽ” ብሎ፡ እንደጠራኝ አስባለሁ። መግለጽ የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነበር። ነገር ግን፡ “ሊወጣ እንደሚችልና፡ መሆንም እንዳለበት ተ—ተስማምቻለሁ። መውጣት ካለበት፡ አውጣው” አለ።

157 ነገር ግን እምነታችንን የሚፈትን ነበር። እኛም ያለማቋረጥ ጸለይን። በጸለይን ቁጥርም፡ እብጠቱ ይበልጥ እያደገ ሄደ፡ በመጨረሻም በጎንዋ በኩል ብቅ ብሎ እስከሚታይ ድረስ ደረሰ። ምን እንደሚፈጠር ለማየት ስንል፡ ምስጢር አድርገነው ነበር፥ እዚህ ካሉት ሰዎች ጥቂቶች ያውቁ ነበር። ሁኔታውም እንደዚሁ ቀጠለ።

በመጨረሻም፡ ሄጄበት ከነበረው፡ ከካናዳ ስመለስ...

158 ጌታ ያንን የሕንዶች ነገድ ወደ ክርስቶስ እንድመራ ረዳኝ። ጌታ ቢፈቅድ፡ በዚህ የጸደይ ወራት፡ በጌታ በኢየሱስ ስም ላጠምቃቸው፡ ወደዚያው እመለሳለሁ።

159 አሁን፡ ወደ ታች ስንወርድ፡ ኒው ዮርክ ሳለሁ፡ እሷ... ወይም እዚህ ቀዶ ጥግ-... ቀዶ ጥገና ልታደርግ፡ ወይም ደግሞ ለመጨረሻ ጊዜ ልትመረመር የምትሄድበት ጊዜ ደረሰ። ወደ ኒው ዮርክ ሄድኩ። ስመለስም፡ እዚህ አረፍ አልኩና፡ ወደ ላይ ወጣሁ... እዚህ የመጨረሻውን ስብሰባ፡ ካደረግሁ በኋላ፡ ወደዚያ ሄጄ ከወንድም ውድ ቤት ሆኜ ደወልኩላት።

160 እርሷም፡ “ቢል፡ ልብሴ እንኳ ሲነካኝ መቋቋም አልቻልኩም” አለችኝ። በዚያን ጊዜ በጎንዋ በኩል ልክ **እንደዚህ** ወጥቶ ይታይ ነበር። በዚያ በኩል ያለው እግሯም፡ እየጎተተችው ታነክስ ነበር፡ ከዚያም በላይ በሕይወቷ አሳልፋው የማታውቀው እጅግ የከፋ ሳምንት ነበር። አሁን እዚያ ተቀምጣ፡ እያደመጠችኝ ነው። በሕይወቷ አሳልፋው የማታውቀው እጅግ የከፋ ሳምንት ነበር። እንዲህም አለች፡ “ለዚያ ምርመራ፡ ከነገ ወዲያ፡ መሄድ አለብኝ።”

161 እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “ኦ አምላኬ፡ በቀዶ ጥገና ካወጡት፡ በገና በዓል ወደ ቤታችን እንዳንሄድ ያግደናል፡ ለሕዝቡም እዚያ እንደምገኝ ነግሬያቸዋለሁ።” እኔም፡ “ምን ዓይነት ጊዜ ነው! ኦህ፡ ማይ!” ብዬ አሰብኩ።

162 “ቀዶ ጥገና ሊያደርግ ከሆነ፡ እንግዲህ፡ ‘ከገና በዓል በኋላ እስኪሆን ድረስ፡ ትንሽ ጊዜ ይሰጠኝ፡’ ብለሽ ንገሪው።”

163 ከዚያም፡ “ወደ ካንሰርነት ሊቀየር ይችላል” ብዬ ማሰብ ጀመርኩ። **ወደዚህኛው** በኩል ደግሞ፡ ታውቃላችሁ፡ መጥፎ ነገር ነው፡ ወደ ኩላሊቶች ይዛመታል። ቀጥታ፡ ወደ ካንሰርነት ከተቀየረ፡ ይገድላል። ስለዚህም፡ “ምን ላድርግ” ብዬ አሰብኩ?

ሜዳም፡ “እንግዲህ፡ አሁን፡ በቃ ደውልልኝ፡” አለችኝ።

164 ሽሬቭፖርት በደረስኩበት ዕለት፡ ማለትም ከዚያ ቀጥሎ ባለው ቀን፡ ወደ ሽሬቭፖርት ሰገባ፡ እሷ ለምርመራ መሄድ ነበረባት። ስለዚህም ወደ... ወይዘሮ ኖርማን አብራዋት ትሄድ ነበር፡ እህት ኖርማን፥ ወደዚህ ተብርናክል የምትመጡ፡ ሁላችሁም ታውቋታላችሁ። አብራዋት ወደዚህ ስፔሻሊስት፡ ሐኪም ትሄድ ነበር። እሷም እንዲህ አለችኝ፡ “በ—በ... የመጀመሪያውን ምሽት አገልግሎትህን እስክታደርግ ድረስ ጠብቅና፡ ከዚያም ተመለስ” አለች። ምክንያቱም፡ የሁለት ሰዓታት፡ የጊዜ ልዩነት ነበረ። “ከዚያም ከስብሰባው በኋላ፡ ስትመለስ ደውልልኝና፡ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እነግርሃለሁ።”

እኔም፡ “እሺ” አልኳት። ስለዚህ፡ መንገዴን ቀጠልኩ።

165 በማግሥቱም ጠዋት፡ ከመሄዴ በፊት፡ ቢሊንና ሎይስን ልወስዳቸው ነበር። ሁለቱም አሁን በዚህ ሰዓት እዚህ ተቀምጠዋል። ሁልጊዜም ቢሆን...

166 በቅርቡ ወንድም ፓልመር የሸፈነልን፡ አንድ ያረጀ መቀመጫ እዚያ አለን፡ ሁልጊዜም በዚያ መቀመጫ ዙሪያ ተሰብሰበን እንጸልያለን፡ ይህም የሆነ ነገር... ኦህ፡ ኦቶማን፡ ታውቃላችሁ፡ እግር ማሳረፊያ፡ የሚመስል ነው። ወደ አገልግሎት በምሄድበት ጊዜ ሁሉ፡ በዚያ ዙሪያ ተሰብሰበን ስንጸልይ፡ እግዚአብሔር እንዲረዳን እንጠይቀዋለን።

167 እዚያ ለጥቂት ቀናት፡ ቆይቼ ነበር፡ ብ—ብቸኝነትም ተሰምቶኝ ነበር። ቤቱ፥ ልጆቹ ሄደዋል፡ እርሷም ሄዳለች። ታውቃላችሁ፡ ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት በአንድ ወቅት ይህንን ማለፍ ነበረብኝ፡ ወደ ባዶ ቤት መመለስ፥ በዚያን ጊዜ ግን፡ ሚሰቴን ሆፐን፡ ቀብሬ ነበር። አሁንም ደግሞ ያው ነገር ተደገመ። ተንበርክኬም፡ እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “መልካም፡ ልጸልይና ከዚያም ሄጄ ቢሊንና ሎይስን ይዤ፡ መንገዴን እቀጥላለሁ።”

168 ስለዚህ ለመጸለይ ሰንበረከክ፡ “ጌታ ሆይ፡ በዚህ ጧት እዚህ አካባቢ፡ ናፍቀውኛል፡” አልኩ። እንዲህም አልኩ፡ “እንድትረዳቸውና እንድትባርካቸው

እጸልያለሁ። ዳግመኛ ወደዚህ ሰፍራ እንድንመለስ እርዳን። አሁንም፡” እንዲህ አልኩ፡ “እነርሱ እዚያ ያሉት አንተ በራእይ ወደዚያ ስለላክኸኝ ነው፡ አንተም ፈጽመኸዋል። አሁን ደግሞ ቀጥሎ ምን እንዳደርግ እንደምትነግረኝ ለማየት፡ መጠበቅ እፈልጋለሁ።” እንዲህም አልኩ፡ “እጸልያለሁ... ራራላት።” እንዲህም አልኩ፡ “እዚያ በሚኖረው አገልግሎት እርዳኝ” አልኩ። ከዚያም ቀጠልኩና... እንዲህ አልኩ፡ “ጌታ ሆይ፡ ወደ ካንሰርነት እንዳይቀየር አድርግ። ያ ሐኪምም እብጠቱን ለማውጣት፡ ከአዲሱ ዓመት መጀመሪያ በኋላ እስኪሆን ድረስ እንዲጠብቅ አድርግ። እ—እኔ እርሷን እንደዚያ ማየት አልፈልግም... ”

169 እንዲህም አልኩ፡ “ጌታ ሆይ፡ በዚያች ጧት ያደረገችውን አስባበት አይደለም። ያንን ማለቷ አልነበረም።” አክዬም፡ “ጌታ ሆይ፥ እኔ ወደ አገልግሎቶች ስለመሄዴ አንድም ቀን አንዳች ትንፍሽ ብላ አታውቅም፡ ለወራት ብቆይ፡ ወይም ምንም ቢሆን። ስለዚህ ጉዳይ አንድም ቀን አፏን ከፍታ አታውቅም። ሁልጊዜም ልብሶቼን ወደ አጣቢዎች ትልካለች፡ ሸሚዞቼን ታጥባለች፡ እንዲሁም ወደ አገልግሎት ለመሄድ ሁሉንም ነገር አዘጋጅታ ትጠብቃለች። ከዚያም፡ እግዚአብሔርን እንዴት ማገልገል እንደምትችል ታስባለች” አልኩ።

170 እናንተ ሴቶች፡ ባሎቻችሁን ስታገለግሉ፡ እርግጥ ነው፡ እግዚአብሔርን ታገለግላላችሁ።

171 “አሁንም፡ ደግሞ ደክሞኛና ዝዬ፡ ሰመለሰ፡ ሰዎች ከየቦታው ይመጣሉ። አሳ ለማጥመድ፡ ወይም አደን ለመሄድ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ ይኖርብኛል። እያችሁ፡ ብዙ ሴቶች በዚህ የተነሳ ይበሳጩ ነበር። እርሷ ግን ምን ታደርጋለች? እንድሄድ የአደን ልብሶቼን አዘጋጀችልኝ፥ እንድሄድ ታደርገኛለች።” እኔም፡ “ጌታ ሆይ፡ ያንን ለማለት ፈልጋ አልነበረም” አልኩት። “ልጆቿን የወለደችው በቀዶ ጥገና ስለነበረ፡ ሦስት ጊዜ ሆዷን መቀደድ ነበረባት፡” አልኩ። እንዲህም አልኩ... “ጌታ ሆይ፡ ይ—ይህንን እንደገና ስታደርገው ማየት አልፈልግም።”

172 ልክ በዚያን ጊዜ በክፍሉ ውስጥ አንድ ድምፅ ሰማሁ። ቀና ብዬም አየሁ። ድምፁም፡ “ተነሰ” አለኝ። እንዲህም አለ፡ “አሁን የምትለውን ማንኛውንም ነገር፡ ልክ እንደዚያው ይሆናል” አለኝ።

173 ለአንድ ደቂቃ ያህል ጠበቅሁ። እንዲህም አልኩ፡ “የሐኪሙ እጅ እርሷን ከመንካቱ በፊት፡ የእግዚአብሔር እጅ እብጠቱን ያሰወግደው፡ ፈጽሞም አይገኝ” አልኩ።

174 ለእኔ፡ ያ እልባት ሰጠው። አልደወልኩላትም። ቀጥታ መንገዳችንን ቀጠልን፡ ሄደን ቢሊንና ሎይስን ወሰድን፡ ወደ ሽሪቭፖርትም ሄድን።

175 በማግሥቱ ምሽት ደወልኩላት። በጣም ደስተኛ ነበረች። እንዲህም አለችኝ፡ “ቢል፡ ልነግርህ እፈልጋለሁ!”

176 አሁን እዚህ ነች፡ ይህንም ማረጋገጥ ትችላለች። ወደዚያ የሄደችው እያነከሰች ነበር፥ ከነርሷና ከወይዘሮ ኖርማን ጋር ወደ ክፍሉ ገብታ፡ ለ... ለምርመራ የሚሆነውን፡ ቀሚስ ለበሰች። ሐኪሙ ሲወጣ፡ ወደ ጠረጴዛው ላይ ለመውጣት እንኳ ተቸግራ ነበር፥ እብጠቱ በጣም ትልቅ ስለነበር፡ ወጥቶ ይታይ ነበር። እርሷም... ሐኪሙ ገብቶ ያነጋግራት ነበር። እናም ሊነካት፡ አንሶላውን ሊያነሳ መጣ፡ ከዚያም፡ ልክ ሊነካት ሲል፡ እብጠቱ ጠፋ።

177 ሐኪሙም በየትኛው ጎን እንደነበረ አላወቀም። እርሱም እንዲህ አለ፡ “ቆይ!” ከተሳሉት ዲያግራሞችና ከፎቶግራፎቹና፡ ከሌሎችም ነገሮች ሁሉ ጋር አመሳክሮ፡ ምንም ዓይነት ምልክት ሊያገኝ አልቻለም። ደጋግሞ፡ መረመራት። እንዲህም አለ፡ “ላብራራው አልችል ይሆናል፡ ነገር ግን፡ ወይዘሮ ብራንሃም፡ ያ እብጠት እዚያ የለም፡” አላት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም፡ አንድም ምልክት ታይቶባት አያውቅም።

178 ይህ ምን ነበር? አስተውሉ፡ ልክ፡ “የሐኪሙ እጅ እርሷን ከመንካቱ በፊት” እንደተባለው ነው። በቅጽበተ ዓይን ልዩነት፡ እጁ ሊነካው ነበር። የጌታ ቃል እንዴት ፍጹም ነው!

179 አሁን፡ ባለቤቴ እዚያ አለች፡ ሁለታችንም በእግዚአብሔር ፊት ነን። ነገር ግን የሐኪሙ እጅ ገና ገላዋን ከመንካቱ በፊት፡ ልክ እንደዚያ ወደ እርሷ እየመጣ ሳለ፡ አንድ ነገር ሆነ፡ እብጠቱ ጠፋ። እነርሱም፡ እ—እርሱ እንዲህ አለ... እንደዚያ ነበር ብዬ አምናለሁ፡ አይደለም እንዴ፡ ውዴ? “ወይዘሮ ብራንሃም፡ ላረጋግጥልሽ እፈልጋለሁ፡” (እርሱ ያለው ልክ እንደዚህ ነው? በትክክል።) “ያ እብጠት እዚያ የለም። ምንም ዓይነት እብጠት የለብሽም።”

180 ይህ ምን ነበር? በትክክል እንደ ጌታ ቃል፡ ያ የሆነው... ? ... አሜን። ያ አምስተኛው ጊዜ ነው። አምስት የጸጋ ቁጥር ነው፡ የ እ-ም-ነ-ት-ም ቁጥር ነው።

181 በአእምሮዬ ውስጥ ከእንግዲህ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ የለም። ሦስተኛው ስህበት፡ ምን እንደሆነና ምን እንደሚያደርግ አውቃለሁ። አሁን አክብሮት ይኑራችሁ፡ ጸጥ በሉ፡ እግዚአብሔር ለእኛ ታላላቅ ነገሮችን የሚያደርግበት ሰዓት በቅርቡ ይደርሳል።

አሁን ለጸሎት ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

182 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ይህንን በሌሎች ሰዎች ላይ አይቼው ነበር፡ ነገር ግን በገዛ ውድ ባለቤቴ ላይ ሲደርስ፡ ከዚያም፡ ጌታ ሆይ፡ ቤቴ ውስጥ ነበር። በገዛ ዓይኖቼ አየሁት፡ በገዛ እጆቼም ዳሰስኩት። ይህም ደግሞ፡ እ... ከዚያ ከአሥራ-... ከአሥራ ስድስት ዓመታት በፊት፡ ጌታ ሆይ፡ በአንተ ዘንድ የታወቀና የተገለጠ ነበር። ማንኛውም ነገር ሲነገር፡ መፈጸም አለበት። ጌታ ሆይ፡ በዚያን ጊዜ፡ ታሳየኝ የነበረው፡ አንተ ለሕዝቡ ባደረግኸው ነገር ላይ፡ ያለኝን መተማመንና፡ እነርሱን ልረዳቸው እችል ዘንድ፡ እንደምታሳውቀኝ ነበር። በገዛ ቤቴም ውስጥ እንዲፈጸም አደረግህ። ያ የመጀመሪያው ስህበት ነበር። አሁንም ሦስተኛው ስህበት የመጀመሪያውን ስህበት አረጋገጠው።

183 አባት ሆይ፡ ለዚህም አመስጋኞች ነን። ድክመቶቻችንን ይቅር በለን። እኛ ትንሽ ሰዎች ነን። ያልተማርን፡ በመጠኑም ቢሆን፡ መሃይም ሰዎች ነን። ነገር ግን ራሳችንን እንዴት እንደምንጠብቅ ስለማናውቅ የሚጠብቀንና የሚንከባከበን ታላቅና ሁሉን ቻይ የሆነ፡ አምላክ ስላለን እጅግ አመስጋኞች ነን። ራሳችንን ለአንተ አሳልፈን እንሰጣለን።

184 አሁን፡ አባት ሆይ፡ እንድትረዳኝ እጸልያለሁ። በዚህ ሦስተኛው ስህበትም፡ ጌታ ሆይ፡ እንዲሁ ይሁን፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ስለዚህ ነገር ስትናገር፡ በተራሮች ላይ... ምልክት በማድረግና፡ በመሳሰሉት በማሳየት፡ እያሳደግኸው እንዳመጣኸው ነው። አሁን፡ ሙሉ በሙሉ እስኪረጋገጥ ድረስ ምን እንደሆነ ለማየት እጠባበቅ ነበር። አሁንም አባት ሆይ፡ ከበፊቱ በበለጠ ሁኔታ፡ ለዚህ፡

ታላቅ አክብሮት እንዲኖረኝ እንድትረዳኝ፡ እጸልያለሁ፡ ክብርንም ለራስህ ውሰድ። የመጀመሪያው በተነገረበት፡ በዚህው፡ መድረክ ላይ፡ ሁለተኛውም፡ አሁን ደግሞ ሦስተኛው ተነግሯል፡ የተናገርከውም ነገር ልክ እንዳልከው በትክክል ተፈጽሟል። ጌታ አምላክ ሆይ፡ እናምንሃለን።

185 እያንዳንዳችን አለማመናችንንና አጉል እምነታችንን አውጥተን እንድንጥል እርዳን፡ በዚህም በሕያው እግዚአብሔር ፊት መቆም እንችል ዘንድ፡ አሁን እዚህ ተቀምጣ ካለችው ባለቤቴ ላይ ያንን እብጠት ያስወገደው ያው አምላክ መሆኑን፡ እያወቅን፥ ይህም በአገራችን ባሉ አንዳንድ ከፍተኛ የሕክምና ሳይንስ ባለሙያዎች የተረጋገጠውን፡ እነርሱም የመረመሩት፡ የተመለከቱትና፡ ፎቶ ያነሱት ሲሆን፥ አሁንም እርሱ ጠፍቷል። አንተ አምላክ ነህ ከአንተም በቀር ሌላ ማንም የለም።

186 አገልጋዮችህ እንድንሆን ስ—ስለፈቀድህልን እንወድሃለን። በሕይወታችንም ዘመን ሁሉ፡ በአክብሮትና በክብር አንተን ማገልገል ይሁንልን። ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን። እኔና ቤተሰቤ፡ እንዲሁም፡ እነዚህ ሰዎች ሁሉ፡ ለእኛ ይህን ያህል ታላቅ ነገር ያደረገልንን፡ ኢየሱስን እንዲወዱ በሌሎች ላይ-... ጥማትን የሚፈጥር የሚያበራ ብርሃንና፡ ጣዕም ያለው ጨው መሆን ይሁንልን።

187 አሁንም ለአጭር መልእክት ለማንበብ፡ ቃሉን ስከፍት፡ ከዚያም ለታመሙት ስጸልይ፡ ጌታ ሆይ፡ እርዳኝ። ተናገረን፡ የታመሙትንም ፈውስ፡ በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አሜን።

188 ለመሆኑ፡ ለዚህ... ጊዜ ይኖረኝ ይሆን? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።— አርታዒ።] እዚህ ባሉት... አንዳንድ ጥቅሶች ላይ በፍጥነት ካፋጠንኩኝ፡ አሁን እንድታነቡት፡ ወይም እንድታሰምሩበት፡ ወይም ማድረግ የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር እንድታደርጉ እፈልጋለሁ። የመጀመሪያው በዘኊልቊ መጽሐፍ፡ 21፥5 እስከ 19 ላይ ይገኛል፡ ይ—ይህንን ማንበብ እንፈልጋለን፥

> **ሕዝቡም በእግዚአብሔርና፡ በሙሴ ላይ፡ በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ ከግብፅ ለምን አወጣችሁን? እንጀራ የለም፡ ውኃ የለም፥ ሰውነታችንም ይህን ቀላል እንጀራ፡** የመላእክት እንጀራ **ተጸየፈ ብለው ተናገሩ።**
>
> **እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ፡ ሕዝቡንም ነደፉ፥ ከእስራኤልም ብዙ ሰዎች ሞቱ። ከዚያም** ጌታ...
>
> **ሕዝቡም ወደ ሙሴ መጥተው፡ እንዲህ አሉ፡...**

189 መናዘዝ! ተመልከቱ፡ "ኃጢአት ሠርተናል!" አያችሁ፡ ለፈውስ የመጀመሪያው ነገር ያ ነው፡ በመጀመሪያ መናዘዝ።

> **... በእግዚአብሔርና፡ በአንተ ላይ ስለ ተናገርን፡ በድለናል፥ እባቦችን ከእኛ ያርቅልን ዘንድ፡ ወደ እግዚአብሔር ጸልይልን አሉት። ሙሴም ስለ ሕዝቡ ጸለየ።**
>
> **እግዚአብሔርም ሙሴን፡ እባብን ሠርተህ፡ በዓላማ ላይ ሰቀል፥ እንዲህም ይሆናል፡ የ—የተነደፈውም ሁሉ፡ ሲያየት፡ በሕይወት ይኖራል፡ አለው።**

**ሙሴም የናሱን እባብ ሠርቶ፡ በዓላማ ላይ ሰቀለ፡ እንዲህም ሆነ፡ እባብም የነደፈችው ሰው ሁሉ፡ የናሱን እባብ ባየ፡ ጊዜ ዳነ።**

190 አሁን፡ ደግሞ፡ ከዘካርያስ ምዕራፍ 12፡ ቁጥር 10 ላይ አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ ላነብ እወዳለሁ።

**በዳዊትም ቤት ላይ፡ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ፡ የሞገሰንና የልመናን መንፈስ አፈስሳለሁ፥ ወደ ወጉት ወደ እኔ ይመለከታሉ፡ ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ፡ ያለቅሱለታል፡ ሰውም ለበኩር ልጁ እንደሚያዝን፡ በመራራ ኀዘን ያዝኑለታል።**

191 አሁን ለርዕስ፡ ይህንን እወስዳለሁ፡ **ወደ ኢየሱስ ተመልከቱ።** ከዓለም ዘወር ብላችሁ፡ ኢየሱስን ተመልከቱ። ሙሴ እባብን ሠራ፥ እዚህ ጋር ነቢዩ፡ በኋላ፡ ስለሚሆነው ነገር፡ ወ—ወደ ኢየሱስ ስለመመልከት፡ ይናገር ነበር።

192 መጽሐፍ ቅዱስ፡ በኢሳይያስ 45፥22 ላይ እንዲህ ይላል። እግዚአብሔር፡ "የምድር ዳርቻዎች ሁሉ፡ ወደ እኔ ተመልከቱ" እንዳለ እናገኛለን። አሁንም ምድር ወደ መጨረሻዋ ስትደርስ፡ ወይም የምድር መዋቅር ወደ መጨረሻው ሲደርስ፡ ሰዎች ወደ እርሱ ይመልከቱ።

193 አሁን፡ "ይህንን ከትውልድ ወደ ትውልድ፡ ሰንሰማው ኖረናል። ይህንን ለረዥም ጊዜ ሰምተነዋል" ትሉ ይሆናል። ይህም እውነት ነው፡ ለረዥም ጊዜም ሲሰበክ ቆይቷል። በሺዎች የሚቆጠሩ ብዙ አገልጋዮች፡ ይህንኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ወሰደውታል።

194 ነገር ግን ዛሬ ማታ፡ በቀጣዮቹ ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ ልጠይቃችሁ የምፈልገው ነገር ይህ ነው። ዳሩ ግን ስትመለከቱ፡ ጥ—ጥያቄው፡ ስትመለከቱ ምን ታያላችሁ? ስትመለከቱ ምን ታያላችሁ? ያ የሚወሰነው በምትፈልጉት ነገር ላይ ብቻ ነው። አያችሁ? አሁን እርሱ፡ "የምድር ዳርቻዎች ሁሉ፡ ወደ እኔ ተመልከቱ" አለ። ሙሴ እባቡን ከፍ አደረገ፡ እና፡ እርሱን ትኩር ብሎ ያየ ሁሉ፡ ተፈወሰ። አሁንም፡ ነገሩ የሚወሰነው እናንተ በምትፈልጉት ነገር ላይ ነው።

195 በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ ሰዎች ወደ ሰብሰባዎች መጥተው፡ በሰብሰባው ውስጥ መቆየት የሚችሉት ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃዎች ያህል ብቻ ሆኖ አይቻለሁ። መቋቋም የሚችሉት ያንን ያህል ብቻ ነው። አያችሁ፡ መቋቋም አልቻሉም ነበር።

196 በወተርሉ ውስጥ ሰብሰባ ባደረግሁበት ጊዜ የነበረውን፡ መቼም አልረሳውም፡ ይህም አዮዋ ካለ ከማንም ሰው ጋር እንደማይጋጭ ተስፋ አደርጋለሁ።

197 ወንድም ሊ ቬይል፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ ነበር። ዛሬ ማታ እዚህ ይኑር አይኑር አላውቅም። ሊ፡ እዚህ ነህ? ዛሬ ጠዋት እዚህ ነበር። አዎን፡ እዚያ ድምጽ መቅረጫው ጋር፡ እዚህ ከኋላ አለ። መልካም።

198 ከወንድም ሊ ጋር ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አደረግን። መጥተን እንድናነጋግራቸው ብቻ በማሰብም፡ ለአገልጋዮች ህብረት፡ ነጻ ቁርስ አቀረብንላቸው። ወንድም ሊ ቬይል፡ እርግጥ ነው፡ እሱ ምሁር እ—እንዲሁም ዲግሪውን በትክክል ያገኘ፡ የስነ መለኮት ዶክተር ነው። ስለዚህም በእነዚህ

ሉተራውያን፡ ፕሪስቢቴሪያውያን፡ እንዲሁም በመሳሰሉት ፊት እንዲናገር ለማድረግ ሞክርኩ፡ ነገር ግን እርሱ፡ “አይሆንም፡ ይሄን እንድታደርግ የሚጠብቁት ከአንተ ነው” አለኝ።

199 መልካም፡ ሁሉም በልተው ከጨረሱ በኋላ፡ በእነዚያ አገልጋዮች ፊት ሄጄ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሌን ወሰድኩ። የወሰድኩትም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡ **ለሰማያዊው ራእይ እምቢ አላልሁም** የሚል ነበር። መጽሐፍ ቅዱሱን አነብቤ እንዳበቃሁ ወዲያው፡ ወደ ሁለት የሚሆኑት ተያዩና፡ በሩን አልፈው ወጡ። ስለዚህ፡ “ጳውሎስ በዘመኑ፡ ልዩ በሆነ አገልግሎት፡ አሁን በአግሪጳ ፊት ቆሞ ለዚያ እምቢተኛ እንዳልነበረ እንደተናገረው፡” ብዬ መናገር ስጀምር ሁለት ወይም ሦስት የሚሆኑ ሌሎች ሰዎች ተነሱ። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉም አንድ ነገር መናገር ወደምችልበት ደረጃ ስደርስ፡ እዚያ ተቀምጠው የነበሩት ሦስት ወይም አራት የሚያህሉ ብቻ ነበሩ። ሁሉም ተነስተው ሄደው ነበር።

200 ለዚህም ምክንያቱ፡ ይኸውላችሁ፡ ይሄ ነው። አንዳንዶች ስለ ወንጌላዊ ሲሰሙ፡ ወደ ስብሰባ ይመጣሉ፡ እርሱ የሚለብሰበት መንገድም ከሰዎቹ ጋር ግንኙነት አለው። ትክክለኛውን ዓይነት ልብስ ካልለበሰ፡ ከእነርሱ አንዳንዶቹ...

201 በቀደም፡ አንድ የ——የሥነ ልቦና ባለሙያ ሲናገር ሰማሁ፥ ዶክተር ናራሞር፡ ግሩም ሰው፡ ክርስቲያን ሰው ነው፡ ፕሮግራሙ ሁልጊዜ፡ እዚያ **ኬያር** ላይ ይተላለፋል። እርሱም፡ “አንድ ሰው አእምሮውን እየሳተ መሆኑን የሚታወቅበት መንገድ፡ ለማንነቱ በሚመጥን ሁኔታ ሳይለብስ ሲቀር ነው” አለ። ታውቃላችሁ፡ በህዝብ ፊት እንዴት መቅረብ እንዳለበት የሚያሳየው ሁኔታ፡ ያ አእምሮውን እያጣ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነበር።

202 መልካም፡ እንግዲያውስ፡ በህይወት ዘመኔ ሁሉ እብድ ነበርኩ ማለት ነው፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም ኦቨርኦልና የመሳሰሉትን ልብሶች ስለብስ ነበር፡ አያችሁ። ስለዚህ፡ ለቦታዬ በሚመጥን መልኩ፡ እንደ ቀሳውስት መልበስ አለብኝ፡ በሌላ አነጋገር፡ ቀሳውስት ለ——ለመሆን።

203 ኢየሱስ እንደ ቀሳውስት የለበሰ አይመስለኝም። እርሱ እንደ ተራ ሰው ነበር የለበሰው። በሰዎች መካከል ተመላለሰ፡ በአለባበሱም ምንም የተለየ ነገር አልነበረም።

204 ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ያ የሰው ሀሳብ ብቻ ነው። ይህም... በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ አንድ ነቢይ፡ ልብሱን አውልቆ በህዝቡ ፊት ራቁቱን እንዲራመድ በታዘዘ ጊዜ፡ ይህ ሰው ምን ይል ይሆን ወይም ዶክተሩ ስለዚህ ጉዳይ ምን ያስብ ይሆን ብዬ አስባለሁ? በእርግጥም እብድ ይለው ነበር፡ አይደል እንዴ? ነገር ግን ያንን እንዲያደርግ የነገረው እግዚአብሔር ነበር።

205 ሌላኛው ደግሞ ለሦስት መቶ አርባ ወራት ያህል፡ ይመስለኛል፡ በአንድ ጎኑ መተኛት ነበረበት፥ በአንድ ጎኑ ተኝቶ፡ ከዚያም ወደ ሌላኛው ጎኑ ተገለበጠ። እዚያም ያዘጋጀውን አንድ ድስት ምስር መብላት ነበረበት፥ ሄዶም እነዚህን ነገሮች፡ በመቀቀል በአንድ ላይ በማዘጋጀት፡ በዚያም ጊዜ ሁሉ ያንን መብላት ነበረበት፥ እንደ ምልክት ሆኖ፡ በጎኑ ተኝቶ ሳለ፡ እጁን ዘርግቶ አንድ እፍኝ እየወሰደ መብላት ነበረበት። አያችሁ?

206 ኦህ፡ ሰዎች በእውነት፡ ከእግዚአብሔር ቃል፡ ምን ያህል ሊርቁ ይችላሉ። ራሳቸውን በትምህርት ከእግዚአብሔር እስኪያርቁ ድረስ እጅግ በጣም ይማራሉ። አንድ ሰው ትምህርት፡ የዶክትሬት ዲግሪ አለኝ ብሎ ሲናገር፥ በዚህ ከእግዚአብሔር ምን ያህል እንደራቀ አውቃለሁ፡ እያችሁ። ይህንን በዶክተር ቬይል ላይ እየተናገርኩ አይደለም፡ ምክንያቱም እርሱ እንደዚያ ዓይነት ሰው አይደለምና። ነገር ግን፡ አብዛኛውን ጊዜ፡ አንድ ሰው የዶክትሬት ዲግሪ ሲያገኝ፡ ራሱን ከቃሉና ከእግዚአብሔር ጋር ካላጣበቀ በቀር፡ ያ ለእኔ፡ የሚያሳየው፡ እያችሁ፡ ያን ያህል ከእግዚአብሔር መራቁን ነው።

207 አሁን፡ አንዳንዶች ለመመልከት ሲመጡ፡ የምትናገሩበትን መንገድ ለመስማት እንደሚመጡ እንረዳለን። ስለ መለኮታዊ ፈውስና ስለ ጌታ ትናገራላችሁ፥ አንድ ሰው የተለመደ፡ የተማረ አዋቂ ካልሆነ፡ ሰዎች እንደ “ተእርሱ፡ ተእዚያ፡” ያሉትን ቃላትና የ—የመሳሰሉትን ቃላት ሲጠቀም ለመስማት ፈጽሞ አይታገሱም… በቃ… አይችሉም። ያም ከእግዚአብሔር ፈጽሞ የራቀ እንደሆነ ያሰባሉ።

208 ኢየሱስም በጣም ቀላል ቋንቋ ስለተናገረ፡ እስከ፡ ዛሬዋ ዕለት ድረስ፡ ፕሮፌሰሮችን ግራ አጋብቷቸዋል፡ ምክንያቱም በትምህርታቸውና በዚያ ዘመን በነበረው ቋንቋ ሊተረጉሙት ስለሚሞክሩ ነው፡ እርሱም የጎዳና ቋንቋ ነበር። ስለዚህ…

209 እያችሁ፡ እዚህ በዩናይትድ ስቴትስ ሀገራችን እንኳ በጣም ብዙ ልዩነት አለ! ከፍሎሪዳ፡ ወደ ኒው ዮርክ ደወልኩ፡ በዚህች የደቡቧና በሰሜኗ ሴት መካከል እንድትተረጉም፡ በዚህች የደቡብ እና የሰሜን ሴት መካከል እንድትተረጉም፡ ሴንት ሉዊስ ውስጥም፡ ሌላ ሴት መፈለግ ነበረብኝ። ያን ያህል ልዩነት ነበር። እያችሁ? እርግጥ ነው።

210 አሁን ዋናው ነገር፡ ሰዎች ከቃሉ ይልቅ፡ እነዚያን ነገሮች፡ ንግግሮችን መፈለጋቸው ነው። ቃሉ መገለጡ ትክክል ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው። እያችሁ፡ ቃሉ መገለጡ! ያንን ከቶ አይመለከቱም። እውቀት ላይ የተመሰረተ ግንዛቤ ሊኖራችሁ ይገባል፡ ይህን ለማወቅ፡ ወደ ሴሚናሪ ሄዳችሁ እንዴት አጎንብሳችሁ እጅ መንሳት እንዳለባችሁ፡ በአንድ ቦታ ላይ እንዴት መቆም እንዳለባችሁ፡ ሌላውንም ሁሉ መማር አለባችሁ። ኦህ፡ ይህ በእውነት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላን አገልጋይ፡ እስከ ሞት ድረስ፡ ያንቀው ነበር። እያችሁ? አሁን፡ ያ በአእምሮ እውቀት ላይ የተመሰረተ ነው።

211 ይህችም መላዋ ሀገር የደረሰችበት መንገድ ይኸው ነው። ስለ ክርስቶስ በአእምሮ እውቀት ላይ የተመሰረተ ግንዛቤ አላት። የሚፈልጉትም ያንን ነው። “ክርስቶስም በውስጣችሁ ካለ፡ ምሁር መሆን ይገባችኋል፡ በአእምሮ እውቀት የበሰላችሁ መሆን አለባችሁ፡” ምክንያቱም ክርስቶስ ያ እንደሆነ ነው የሚያስቡት።

212 በሌላ ጊዜም፡ ሌላው ነገር፡ ቃሉ የተናገረውን ከመውሰድ ይልቅ፡ እርሱ ምን መሆን እንዳለበት የራሳቸውን አመለካከት፡ የራሳቸውን ሃሳብ ይቀርጻሉ። ሲመለከቱም፡ ኢየሱስንም ራሱን እንኳ ሲያዩት፡ ሊያሰተውሉት ያልቻሉትም በዚህ ምክንያት ነው። በጴንጤቆስጤ ቀንም ያንኑ አድርገዋል። በስጋ በነበረበት ጊዜም ያንኑ አድርገዋል። በግርግም ውስጥ በነበረበት ጊዜም ያንኑ

አድርገዋል። በኢየሩሳሌም ጎዳናዎች ላይ በነበረበት ጊዜም ያንኑ አድርገዋል። በመስቀል ላይ በነበረበት ጊዜም ያንኑ አድርገዋል። እርሱም የዚያ ቃል ፍጻሜ ነበረ። ሆኖም፡ ግን፡ መሢሑ ከሰማይ በመተላለፊያ ላይ እንደሚወርድና፡ ሌላውንም ሁሉ አድርገው አሰበው ነበር፡ ነገር ግን ስህተት ነበር፡ ምክንያቱም ይህ የእነርሱ አእምሯዊ አስተሳሰብ ነበር። ፊት ለፊታቸው እያዩትም እንኳ፡ እርሱን፡ ማየት ተሳናቸው። ዛሬም እንደዚሁ ነው!

213 ስትመለከቱ ምን ታያላችሁ? አንዳንዶች ለማየት ሲመለከቱ፡ እርሱን ሲመለከቱት፡ በአእምሮ እውቀት የበሰለ ታላቅ የቤተክርስቲያን መሰራች የሆነን ሰው፡ ሰዎች ሁሉ ለዚህ የሐይማኖት መግለጫ አሜን ብለው እንዲገዙ የሚያደርግ የሐይማኖት መግለጫን በእርግጥ ማውጣት የሚችል ሰውን፡ ወይም ሌላ ነገርን ለማየት ይመለከታሉ። እርሱን ሲያዩት የሚመለከቱት ያንን ነው።

214 አንዳንዶች ሲመለከቱ፡ ልክ እንደ ሳንታ ክላውስ ያለ፡ የፈጠራ ተረት ለማየት ይመለከታሉ። መጽሐፍ ቅዱስን ያነባሉ፡ እንዲህም ይላሉ፡ “እህ፡ ያ የፈጠራ ተረት ነው። ሰው የጻፈው ተራ ነገር ነው። ያ ነው፡ እነርሱ፡ ምክንያቱም እነርሱ… ” ለመጽሐፍ ቅዱስ ያላችሁ አመለካከት፡ ለእርሱም ያላችሁ አመለካከት ነው። አያችሁ?

215 አንዳንዶች ህፃን ልጅ ለማየት ይመለከታሉ። አንዳንዶችም ተመልክተው አንዲትን ጥ—ጥንቸል ወይም ሳንታ ክላውስን ያያሉ። አንዳንዶች ዛሬ ሳይሆን በትናንትና የነበረን የታሪክ መጽሐፍ ለማየት ይመለከታሉ።

ነገር ግን፡ ጥያቄው፡ ስትመለከቱ ምን ታያላችሁ?

216 ከእናንተ መንፈስ ቅዱስ አለን ብላችሁ የምትናገሩ፡ ብዙዎቻችሁ፡ ስትመለከቱ የሥላሴን ሁለተኛ አካል ታያላችሁ። እሱም፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንኳ አልተጠቀሰም። እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ የለም። ሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ውስጥ እንኳ አይገኝም። ነገር ግን፡ አሁንም፡ ኢየሱስን ስትመለከቱት፡ እንደ ሥላሴ ሦስተኛ አካል ወይም ሁለተኛ አካል አድርጋችሁ ትቆጥሩታላችሁ፡ የትም የማትደርሱበት ምክንያት ይህ ነው።

217 እርሱ ምን እንዳለ ታውቃላችሁን? “እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡ ከእኔም በቀር ሌላ ማንም የለም” አለ። አያችሁ?

218 ይሄ የሚወሰነው በምትመለከቱት ነገር ላይ ነው። አንድ ትንሽ የማሰኮት ልጅ፡ ጢም ያለው ሽማግሌና፡ የመሳሰሉትን አድርጋችሁ ልታስቀምጡት ከፈለጋችሁ፥ ኢየሱስን ከእግዚአብሔር የተለየ ሌላ ሰው አድርጋችሁ የምትመለከቱት በዚህ መንገድ ከሆነ፡ አመለካከታችሁ የተሳሳተ ነው። አታዩትም።

219 እዚህ በቅርብ ጊዜ፡ አንድ አጉሊ መነጽር ነበረኝ። እዚያ ሜዳ ላይ የተወሰኑ ሚዳቆዎችን፡ ወይም አንድ ሚዳቋ ለመመልከት እየሞከርኩ ነበር። ልጄም ሊያሳየኝ እየሞከረ ነበር፡ እርሱም በዕድሜ ትንሽ ነው። ስለዚህ እንዲህ አለኝ፡ “አባዬ፡ ይሄን መነጽር ያዝ! ሚዳቋው፡ ልክ እዚያ ውጭ ቆሟል!”

እኔም፡ “በተፈጥሮ ዓይኔ ላየው እችላለሁ” አልኩት።

እርሱም፡ “ይህን መነጽር ያዝ” አለኝ።

220 ስመለከት፡ ወደ አሰር የሚሆኑ ሚዳቆዎችን አየሁ፡ ነገር ግን የመነጽሩ የዕይታ ማስተካከያ አልተስተካከለም ነበር። ትኩረቱን ለማስተካከል ሰሞክርም፡ አሥሩም አንድ ሆኑ።

221 አእምሯችሁንም በእግዚአብሔር ቃል ላይ ብታተኩሩ፡ ሦስቱ አንድ ይሆናሉ። አያችሁ? ነገር ግን እርሱን ሦስት ለማድረግ ስትሞክሩ የሃይማኖት ተቋም መነጽራችሁ ዕይታ ይዛባባችኋል። እርሱ አንድ ነውና። አያችሁ?

222 ነገር ግን ይሄ የሚወሰነው በምትመለከቱት ነገር ላይ ነው። ስትመለከቱ ምን ታያላችሁ? አስታውሱ፡ እርሱን ማየት የምትችሉት በቃሉ በኩል ስትመለከቱት ብቻ ነው። በመማሪያ መጽሐፍ በኩል እርሱን መመልከት አትችሉም። በአንድ የሐይማኖት መግለጫ በኩል እርሱን መመልከት አትችሉም። በእነዚያ የሐይማኖት መግለጫዎች ውስጥ፡ ሁለት ወይም ሦስት አማልክትን፡ እንዲሁም ሌላውንም ሁሉ ታያላችሁ። ነገር ግን በቃሉ በኩል እርሱን ተመልከቱት፡ እርሱም "**አማኑኤል፡** 'በመካከላችን ሰጋ የሆነ አምላክ'" መሆኑን ታያላችሁ። እርሱም፡ "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡ ከእኔም በቀር ሌላ ማንም የለም" አለ። እርሱ እግዚአብሔር ነው።

223 ነቢዩ፡ ኢሳይያስ አንድ ጊዜ ተመለከተ፡ ኢየሱስንም ባየ ጊዜ... የስብከቴ ርዕስ፡ "ኢየሱስን መመልከት" የሚል ነው። **ወደ ኢየሱስ ተመልከቱ።** ኢሳይያስ እርሱን ለማየት፡ ከዓለም ላይ ዓይኑን ባነሳ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ "ድንቅ መካርን፡ የሰላም አለቃን፡ ኃያል አምላክን፡ የዘላለም አባትን አያለሁ" አለ። ኢሳይያስ ዓይኑን አንስቶ ያየው ያንን ነበር።

224 ዳንኤልም፡ አንድ ጊዜ፡ የ—የአሕዛብን መንግስታት ፍጻሜ ባየ ጊዜ ቆሞ ነበር። ናቡከደነፆር በህልሙ ያየውን ምስል አየ። ወደ ታች ሲወርዱ፡ እያንዳንዳቸው አንዱ ሌላውን እንዴት እንደሚተኩ አየ። በመጨረሻም ምን ሊሆን እንደሆነ ለማየት በተመለከተ ጊዜ፡ ኢየሱስን ባየ ጊዜ፡ እርሱ የአሕዛብን መንግስታት ያደቀቀ፡ "እጅ ሳይነካው፡ ከተራራ የተፈነቀለ ድንጋይ" ነበር።

225 ናቡከደነፆር በእግዚአብሔር ያመኑትንና በቃሉ ላይ የቆሙትን ሦስት የዕብራውያን ልጆች፡ ወደ እቶን እሳት ወረወራቸው። ለቃሉ ሲሉ መሞት ቢኖርባቸውም እንኳ፡ እንዴትም፡ ጸንተው ሊቆሙ ቆርጠው ነበር፡ ጉልበታቸውን በሌላ መንገድ ማንበርከክ፡ ምንም እንኳ ለሌሎች ትንሽ ነገር ቢመስልም አላደረጉትም። ዳሩ ግን ዓይኑን አንስቶ ኢየሱስን ባየ ጊዜ፡ እርሱ በእቶን እሳቱ ውስጥ የነበረው "አራተኛው ሰው" ነበረ፡ ያም የእሳቱን ሀይል ከታዛዥ አገልጋዮቹ ላይ አርቆት ነበር። ናቡከደነፆር ያየው ያንን ነው።

226 ሕዝቅኤል አንድ ቀን እርሱን ለማየት አሻግሮ በተመለከተ ጊዜ፡ "በመንኮራኩር መካከል እንዳለ መንኮራኩር" ነበረ፡ በአየር መካከል ወደ ላይ ከፍ ብሎ ነበር። እርሱ እያንዳንዱ ዘንግ የተያያዘበት፡ የመንኮራኩሩ እምብርት ነበረ። አሜን! ትልቁ መንኮራኩር በእምነት ይሽከረከራል፡ ነገር ግን ትንሹ መንኮራኩር በጌታ ኃይል ይሽከረከራል። ህዝቅኤል ዓይኑን ባነሳ ጊዜ ያየው ያንን ነበረ።

227 መጥምቁ ዮሐንስ አንድ ቀን ዓይኑን አነሳ፡ እናም፡ አነሳና፡ እርግብን አየ፥ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡" የሚልንም፡ ድምጽ ሰማ። ያየውም ያንን ነበር። ከዚያም፡ ኢየሱስና እግዚአብሔር ያው አንድ አካል

መሆናቸውን አየ፡ ምክንያቱም መንፈስ ከሰማይ እንደ እርግብ ወርዶ፡ “በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፡” እያለ ነበር። ያየውም ያንን ነበር። እስተውሉ፡ ራሱን በዚህ መንገድ ነው የሚገልጠው።

228 ኖኅ፡ እርሱን ለማየት ዓይኑን ባነሳ ጊዜ፡ ኖኅ ቃሉን ባልተቀበሉት በዚህ ዓለም ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር የጽድቅ ፍርድ ሲመጣ አየ። ኖኅ ዓይኑን ባነሳ ጊዜ የተናገረው ያንን ነበር።

229 ሙሴ፡ ዓይኑን ባነሳ ጊዜ፡ በእሳት የምትነድ ቁጥቋጦን አየ። የዕሳት ዓምድ ራሱን በቁጥቋጦው ውስጥ አድርጎ ነበር፡ ሙሴም ወደዚያ በቀረበ ጊዜ፡ እርሱም፡ “ጫማህን አውልቅ፡ ምክንያቱም፡ ‘**እኔ ነኝ**’” አለው። አሁን፡ “**እኔ ነኝ**” የሚለውን ቃል፡ ብትመረምሩት፡ ያለፈ ጊዜ፡ አሁናዊ ጊዜና፡ የወደፊት ጊዜ ነው። “**እኔ ነኝ**፡” ዘላለማዊ! እያችሁ? “**እኔ ነኝ**፡” እርሱም “**እኔ ነኝ**”ን አየ። በሚነድደው ቁጥቋጦ ውስጥ ያየው ያንን ነበር።

230 እስራኤል ሙሴ የሰራውን የናስ እባብ ተመለከተ፡ ስለ በሽተኞችም ፍርድ የተቀበለውን የክርስቶስን መከራ አየ፡ ምክንያቱም እባቡ ስለ ሰርየት እንደሚናገር እናውቃለንና።

231 ኢየሱስ ያ ሰርየት ነበረ። “ሙሴ በምድረ በዳ የናሱን እባብ ከፍ ከፍ እንዳደረገ፡ የሰው ልጅም እንዲሁ ከፍ ከፍ ሊል ይገባዋል፡” ይህም ለዚያው ዓላማ ነበረ። እያችሁ? ለምን? ኃጢአት ሰርተው ነበር፡ ደግሞም ታመው ነበር፥ ያም ኃጢአታቸውንና ህመማቸውን ለማስወገድ ነበረ። “ኢየሱስ ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፥ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወሰን፡” የሚለውም ለዚህ ነው። መለኮታዊ ፈውስን ከክርስቶስ ላይ ብታነሱ፡ የሰርየቱን ግማሽ፡ ለሁለት ትቆርጣላችሁ። እያችሁ?

232 ስትመለከቱ በእርሱ ውስጥ ምን ታያላችሁ? ያንን ታያላችሁን? “ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፥ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወሰን፡” የሚለውን ታያላችሁን? ዓይናችሁን አንስታችሁ ስትመለከቱ፡ ያንን ማየት ትችላላችሁ፡ ወይስ የሰርየቱን አንድ ጎን ብቻ ነው የምታዩት? ስትመለከቱ ሁለቱንም ጎኖች ማየት ትችላላችሁን?

በሐይማኖት መግለጫው በኩል ብትመለከቱት፡ “የፈውስ ቀናት አልፈዋል፡” ብለው ይነግሯችኋል።

ነገር ግን በቃሉ በኩል ብትመለከቱት፡ “እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡” የሚለውን ታያላችሁ። እያችሁ?

233 ደቀመዛሙርቱ በማዕበል በሚናወጥ ባህር ውስጥ በነበሩ ጊዜ እርሱን ተመለከቱ፡ ሊረዳቸው የሚችለውን ብቸኛውንም እርዳታ፡ ሲመጣ አዩ።

234 ማርታ በሞት ጊዜ እርሱን ተመለከተች፡ እርሱም “ትንሣኤና ህይወት” መሆኑን አየች። አሜን! በሞት ጊዜ፡ ማርታ አየች፡ እርሱን በተመለከተች ጊዜ... በህዝቦቿ ተጠልቶ ነበረ፥ ተገፍቶ ነበረ፥ እንዲያውም፡ ወደ እርሱ ልካ ነበረ፡ እርሱም ወደ ወንድሟ አልመጣም ነበረ። ዳሩ ግን በመጨረሻ በመጣ ጊዜ፡ እርሱንም መመልከት ትችል ዘንድ ሄዳ በፊቱ በወደቀች ጊዜ፡ እርሱ “ትንሣኤም ህይወትም” መሆኑን አወቀች። አሜን!

235 ኢያኢሮስም ያንኑ አደረገ፡ በድብቅ የሚያምን ሰው ነበር፥ በእርግጥም የሚያምን፡ ፕሪስቢቴሪያን፡ ሜቶዲስት፡ ወይም ባፕቲስት ነበር፡ ነገር ግን ይወገድ ስለነበር፡ የሐይማኖት ተቋሙ ስለማይፈቅድለት፡ በግልጽ መውጣት አልቻለም። ነገር ግን ብቸኛዋ ትንሽ ልጁ በሞት አፋፍ ላይ ተኝታ ነበር፡ እርሱም መሄድ ነበረበት። ነገር ግን እርሱን ባገኘው ጊዜ፡ እርሱ ትንሣኤና ህይወት መሆኑን ተረዳ።

236 ወደ እርሱ በላከ ጊዜ፡ አንድ ሰው እየሮጠ መጣና፡ “ልጅቷ አስቀድማ ሞታለችና፡ መምህሩን አታድክመው” አለው። እርሱም… ትንሿ ልቡ ልትቆም ምንም አልቀራትም ነበር።

237 ነገር ግን እርሱ እንዲህ አለው፡ “‘ብታምን ብቻ፡ የእግዚአብሔርን ክብር ታያለህ’ ብዬ፡ አልነገርሁህምን? ” ያኢሮስ ኢየሱስን በተመለከተ ጊዜ፡ እርሱ ሙታንን ማስነሳት እንደሚችል አወቀ።

238 የተራቡት እርሱን ተመለከቱ፡ ለህይወት የሚያቆይ ምግብንም አገኙ። ያም ተፈጥሯዊ ነበር። በመንፈስ፡ የተራቡትም፡ እርሱን ሊመለከቱ እርሱ የህይወት እንጀራ መሆኑን ሊረዱ ይችላሉ።

239 የሚሞተው ሌባ ምን ሊያይ እንደሚችል ለማየት ተመለከተ፡ በኢየሱስም ውስጥ፡ ይቅርታውን፡ አገኘ። “ጌታ ሆይ፡ በመንግስትህ በመጣህ ጊዜ፡ አስበኝ” አለው። ኢየሱስም፡ “ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ” አለው። በሞቱ ሰዓት ያየው ያንን ነበር።

240 በሽተኞች እርሱን ተመለከቱ፡ ፈዋሹንም አዩ። ዕውሮች ተመለከቱ፡ ማየትም ቻሉ።

ይሄ የሚወሰነው አሁን በምትመለከቱት ነገር ላይ ነው። ምን እየተመለከታችሁ ነው?

241 ጴጥሮስና ናትናኤል ተመለከቱ፡ የነቢያቸው፡ የሙሴ፡ የተሰፋ ቃል በተግባር ሲገለጥም አዩ። “ጌታ አምላካችሁ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል፡ ህዝቡም በእርሱ ይጣበቃል። በእርሱ የማያምንና፡ ያንን ነቢይ የማይሰማ ሁሉ፡ ከህዝቡ መካከል ተለይቶ ይጠፋል።”

242 ጴጥሮስ ወደ እርሱ ፊት በቀረበ ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ “ስምህ ስምዖን ነው፡ አንተም የዮናስ ልጅ ነህ” አለው። ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ኢየሱስን በተመለከተበት በዚያች ቅጽበት፡ የእግዚአብሔር ቃል እርሱ ይሆናል ብሎ የተናገረው ነገር ፍጻሜውን እንዳገኘ ያን ጊዜውኑ አወቀ። አሜን።

243 እናንተስ እርሱን ለመጀመሪያ ጊዜ በተመለከታችሁት ጊዜ ያንኑ ነገር አግኝታችሁ ይሆን ብዬ እሰባለሁ? እርሱን በተመለከታችሁ ጊዜ የተሰፋው ቃል ለእናንተ ተገልጦላችሁ ይሆን?

244 ናትናኤል፡ ወደ ኢየሱስ ፊት እንደ ቀረበ ወዲያው፡ በውስጡ ትንሽ ጥርጣሬ አድሮበት ነበር… ፊልጶስ ሄዶ፡ “ማንን እንዳገኘን፡ መጥተህ እይ” ብሎ ነግሮት እንደነበር እናገኛለን።

ናትናኤልም መጣና፡ “የትኛው ነው እርሱ፡” አለው?

እርሱም፡ “ምናልባት እዚያ ቆሞ ለበሽተኞች የሚጸልየው እርሱ ይሆናል” አለው።

245 እርሱን መመልከት እስኪችል ድረስም በህዝቡ መካከል እየተጋፋ ጥሶ አለፈ። በተመለከተውም ጊዜ፡ ኢየሱስ፡ “እነሆ ተንኰል የሌለበት እውነተኛ እስራኤላዊ” አለው።

እርሱም፡ “ረቢ፡ ከየት ታውቀኛለህ” አለው?

246 እርሱም፡ “ፊልጶስ ሳይጠራህ፡ ከዛፉ በታች ሳለህ፡ አየሁህ” አለው።

247 ታዲያ ናትናኤል ምን አገኘ? የእስራኤል ንጉሥ እዚያ እንደነበረ አወቀ። እርሱም፡ “አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ። አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ” አለው። በተመለከተ ጊዜ ያየው ያንን ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ፡ ከፊቱ ብርሃን ሆኖ ሲበራ አየው። ያ የተቀባው ነቢይ ሙሴ፡ “እንደ እኔ ያለ ነቢይ ይሆናል” ብሎ የተናገረውን ያንኑን ቃል፡ ያንን አየው።

248 በውሃው ጉድጓድ አጠገብ የነበረችው ሴትም፡ አንድ ጊዜ ተመለከተች፡ ምን አየች? ያንን በከተማይቱ ውስጥ ገለጠችው። እሷም፡ “ኑ፡ መጥታችሁ ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው እዩ። ይህ በእርግጥ መሢሑ አይደለምን? ” ለመጀመሪያ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን በተመለከተች ጊዜ፡ መሢሑን አየች።

249 ሰዎች ዛሬም ያንኑ ነገር ሊመለከቱት ይችላሉ፡ ደግሞም “የአእምሮ ቴሌፓቲ” ብለው ይጠሩታል። “መንፈሳዊነት” ብለው ይጠሩታል። ሊጠሩት በሚችሉት በማንኛውም የሰይጣን ስም ይጠሩታል፡ ምክንያቱም ምን እንደሚፈልጉ አያውቁምና። አሜን። አያስተውሉም። የሐይማኖት መግለጫን ይፈልጋሉ። ቤተክርስቲያንን በሰርዓት የሚያስይዝ ሊቅን ይፈልጋሉ። ተጨማሪ አባላትን ይፈልጋሉ፡ በተገለጠው ቃሉም ውስጥ የተባረከውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማየት ይሳናቸዋል። በትክክል።

250 ይሄም የሚወስነው በምትፈልጉት ነገር ላይ ነው። የዛሬውን የተሰፋ ቃል መፈጸም የምትፈልጉ ከሆነ፡ ያንን ታያላችሁ። ነገር ግን፡ በአእምሮ እውቀት የበሰለን ሰው፡ ወይም እነርሱ ሁልጊዜ ሲፈልጉት የነበረውን ነገር፡ አንድ ታላቅ መሰራችን፡ አንድ ታሪክ ጸሐፊን፡ ሌላ ሰውን፡ ወይም ሌላ ነገርን የምትፈልጉ ከሆነ፡ ማየት አትችሉም። ነገር ግን በቃሉ በኩል እርሱን ሰትመለከቱት፡ ቃሉ እርሱ ማን እንደሆነ ይገልጣል።

251 በዘመኑ የነበሩትን ሰዎችም እንዲሁ እንዲያደርጉ ተገዳደራቸው። ሊያዩት አልቻሉም። እርሱም፡ “እናንተ ዕውሮችን የምትመሩ ዕውሮች። ሙሴ ነቢያችን ነው ትላላችሁ። ሙሴን ብታውቁት ኖሮ፡ እኔንም ባወቃችሁኝ ነበር። ሙሴ ስለ እኔ ጽፏልና” አላቸው። ሆኖም ይህንን ለማየት በጣም ታውረው ነበር። አፍጠው እያዩት፡ ለማየት ግን እጅግ ታውረው ነበር።

252 ዛሬ ጠዋት፡ ለጥቂት ደቂቃዎች፡ አያችሁ፡ ያንን “እንጸባራቂ ብርሃን፡” እያያያዝኩት-ነው። እየተመለከቱ ነው፡ ነገር ግን ምን እንደሚፈልጉ አያውቁም፡ ምክንያቱም ሊያገኙት ስለሚሞክሩት ነገር የተሳሳተ አመለካከት ስላላቸው ነው። ምን እንደምትፈልጉ ካላወቃችሁ፡ ማግኘት የምትፈልጉትን ነገር እንዴት ልታውቁ ትችላላችሁ?

253 ዱባ አይታችሁም ሆነ ሰምታችሁ የማታውቁ ከሆነ፡ ዱባን ለመፈለግ እንዴት ትሄዳላችሁ? ሀብሐብ የሚባል ነገር መኖሩንና፡ ምን እንደሚመስል ሳታውቁ፡ ሀብሐብን እንዴት ልታገኙ ትችላላችሁ? አያችሁ፡ ገንዳን አግኝታችሁ፡ ሀብሐብ

እንደሆነ ልታስቡ ትችላላችሁ። ሌላም ነገር አግኝታችሁ፡ ምናልባትም ጉቶ አግኝታችሁ፡ ሀብሐብ መስሎአችሁ ሊሆን ይችላል።

254 ነገር ግን ምን እንደምትፈልጉ ማወቅ አለባችሁ። ወዴት እንደምትሄዱና፡ ምን እንደምትፈልጉ ማወቅ የምትችሉበት ብቸኛው መንገድ፥ ኢየሱስን የምትፈልጉ ከሆነ፡ ወደ ቃሉ ትመለከታላችሁ፡ እርሱ ቃሉ ነውና። "መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ። እነርሱ ስለ እኔ ይመሰክራሉና።"

255 "እናንተ በነቢያት... እንደምታምኑ ትናገራላችሁ፡ ዳሩ ግን ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ። ነቢያትን እናምናለን የሚሉት፡ አባቶቻችሁ፥ እግዚአብሔር ነቢያትን ወደ እነርሱ ሲልክ፡ በመቃብር ውስጥ ከተቷቸው። እ—እነርሱ ነቢያትን ይገድላሉ። ከመጡት ሁሉ፡" ኢየሱስም እንዲህ አለ፡ "አባቶቻችሁ ያልወገሩት ከእነርሱ መካከል ማንኛውን ነው? እናንተም የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ" አለ። አሜን! ጻድቃን ሰዎች፡ ቅዱሳን ሰዎች፡ ጣት ልትቀስሩባቸው የማትችሉ ሰዎች ነበሩ፡ ዳሩ ግን እርሱ "እባቦችና እጋንንት" ብሎ ጠራቸው። አያችሁ?

256 ምን እየፈለጋችሁ ነው? የሆነ ሃይማኖተኛ ሰው እየፈለጋችሁ ነውን? አንዳንዶች መንፈስ ቅዱስ በእናንተ በኩል ስለሠራ፡ ትልቅና፡ ሃይማኖተኛ ሰው መሆን እንዳለባችሁ አድርገው ያስባሉ፡ በዚያ አካባቢ ሰትራመዱ እንኳ... ያ መንፈስ ቅዱስ አይደለም። እግዚአብሔር እንደዚህ ባሉ፡ ወይም እንዲህ ይመስላሉ ተብሎ በሚታሰቡ መላእክት በኩል አይሠራም። እግዚአብሔር በሰዎች በኩል ይሠራል። መጽሐፍ ቅዱስ፡ "ኤልያስ እንደ እኛ የተፈጠረ ሰው ነበረ" ይላል፡ ነገር ግን ኢየሱስን እስካላያችሁ ድረስ ከእርሱ ጋር ልትሆኑ አትችሉም ነበር።

257 ጴጥሮስና ዮሐንስ፡ መልካም በተባለችው መቅደስ ደጃፍ ነበሩ። ያንን ሰው ስለመፈወሳቸውም ወደ ሸንጎ ባቀረቧቸው ጊዜ፡ "መጽሐፍን የማያውቁና፡ ያልተማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ አስተውለው አደነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ አወቁላቸው፡" አያችሁ፡ ምክንያቱም የእርሱ ሕይወት በእነርሱ በኩል ይንጸባረቅ ነበር።

አሁን፡ ይህ የምወሰነው በምትፈልጉት ነገር ላይ ነው።

258 ሴቲቱ መጽሐፍ ቅዱስን አንብባ ነበር። የሚመጣ መሲሕ እንዳለ ታውቅ ነበር፡ ያ መሲሕም ምን እንደሚያደርግ ታውቅ ነበር። ኢየሱስም፡ "የምጠጣውን ስጪኝ" እንዳላት ወዲያውኑ።

እርሷም፡ "ያልተለመደ ነው" አለችው። እርሱ ተራ ሰው ነበር።

259 አሁን፡ እርሱ የአንድን ቅዱስ ሰው፡ በጣም ትልቅ ጥምጣም አድርጎ፡ ሁሉንም ዓይነት ጌጣጌጦች በላዩ ላይ አድርጎ፡ እዚያ ተቀምጦ ቢሆን ኖሮ፡ ሴትዮዋ፡ "እንግዲህ፡ አንድ ካህን እዚያ አለ" ብላ፡ መንገዷን በቀጠለች ነበር። ወይም፡ "የሆነ ዓይነት ረቢ አለ" ብላ፡ በሄደች ነበር።

260 አገልጋይ፡ የሆነ ነገር፥ ዛሬ፡ እኔ ልበላ ወደሄድኩበት ስፍራ፡ አንድ ሰው ለመብላት ሲመጣ አየሁ። ያም ሰው ሲገባ፡ በ—በላዩ ላይ ብዙ መስቀሎችና የመሳሰሉ ነገሮች ነበሩት፥ አንዳንድ ጊዜ እነዚያ ሰዎች ይህንን ማድረጋቸው ጥሩ ነገር ነው። ኑሮአችሁን መኖር እንዳለባችሁ አስባለሁ። ምን እንደሆናችሁ

ለማሳየት፡ ብዙ የክህነት ልብሶችን መልበስ አያስፈልጋችሁም። አንዳንድ ጊዜ ይጠጣሉ፡ በጣም ይረበሻሉ፡ሲጋራ ያጨሳሉ፡ ሁሉንም ነገሮች ያደርጋሉ፡ በዚህ የተነሳ አገልጋዮች መሆናቸውንና አለመሆናቸውን እንኳ ለማወቅ የክህነት ልብሶችን መልበስ ይኖርባቸዋል። ልክ ነው።

261 እላችኋለሁ፡ አንድ ሰው ሊለብሰው የሚገባው የክህነት ልብሰ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። ያ ከኢየሱስ ጋር መሆናችሁን ያረጋግጥላችኋል! በትክክል።

262 አሁን፡ ይህ የምወስነው በምትፈልጉት ነገር ላይ እንደሆነ፡ እናገኛለን። እርሱ ተራ ሰው ሰለነበረ፡ በሚገባ-የለበሰ፡ በደንብ-የተሽሞነሞነ፡ የሆነ ጥምጣም ያደረገ ሰው የምትፈልጉ ከሆነ፥ ፈጽሞ አታዩትም። እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ይሠራል። ኢየሱስ ሰው ነበር፥ እግዚአብሔር በሰው ውስጥ ነበረ፡ እርሱም እግዚአብሔር ነበር።

263 አሁን፡ ይህች ሴት፡ ይህንን ምስጢራዊ ምልክት ባየች ጊዜ፡ ያደረገችውን ስህተት፡ ወይም ደግሞ በልብዋ ውስጥ የነበረውን ሊነግራት ሲችል፡ መሲሑ እርሱ መሆኑን በዚያኑ ሰዓት አወቀች። ስለዚህም፡ ወደ ኢየሱስ በተመለከተች ጊዜ፡ መሲሑን አየችው።

264 መሲሑ፡ የመሲሑ ሥራ ምን ነበር? የልብን ምስጢር ማወቅ ነበረ። ይህ ገብቷችኋልን? ትረዱት ይሆን ብዬ እሰባለሁ። ዛሬ ማታ፡ እርሱን ብትፈልጉት፡ ምን ትፈልጉ ነበር? እርሱ ያው ነው። መሲሑ ቃሉ ነው፡ ቃሉ! መጽሐፍ ቅዱስም፡ በዕብራውያን 4ኛው ምዕራፍ ላይ እንዲህ ይላል፡ ማለት፡ "የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና የሚሠራም፡ ሁለትም-አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፡ ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፡ የልብንም አሳብ ይመረምራል።"

265 መሲሑ ያ የተገለጠው ቃል መሆን እንዳለበት ባወቀች ጊዜ፡ ችግሯም ምን እንደሆነ ሊነግራት ሲችል፡ መሲሑ እርሱ መሆኑን አወቀች። አለባበሱ ምን እንደሚመስል፡ ምን ያህል ትምህርት እንዳለው አይደለም፥ ነገር ግን፡ ባሳያት ምልክት፡ እርሱ መሲሑ ነበር። ኢየሱስን ባየች ጊዜ፡ መሲሑን አየች፥ ለዚያ ለተቀባው ዘመን በተሰፋ እንደተሰጠው፡ እግዚአብሔር በሰው ውስጥ ነበር።

266 ነገር ግን ታውቃላችሁ? እኔ ከተናገርኳቸው ዘመናት መካከል፡ ብዙዎቹ፡ ያንን ነገር ፈጽሞ አላዩትም። ከእነርሱ ውስጥ ብዙዎቹ አላዩትም። ዛሬም ያው ነው። ብዙዎች ሙሴን አላስተዋሉትም። ብዙዎች ኤልያስን አላስተዋሉትም። ብዙዎች አላሰ-... እስኪያልፉ ድረስ ፈጽሞ አያስተውሏቸውም፡ ከዚያ በኋላ ያስተውሏቸዋል።

267 በኖኅ ዘመን፡ የማያምኑት ያዩት፡ ያ አለማመናቸው የተመለከተው ምን ነበር? አማኞቹ ያዩትን ነግሬያችኋለሁ፡ ደግሞ የማያምኑት ያዩትን እንመልከት። በኖኅ ዘመን፡ የማያምኑት ያዩት ወ—ወደ ኋላ ተመልሰው ሲመለከቱ ያዩት ምንድን ነው? ያዩት "ጀልባ-በሚባለው ነገር ዙሪያ የሚዋከብን፡ አንድ አክራሪ" ነበር። ያዩት ያንን ብቻ ነው። "እእምሮውን የሳተ፡ ረዥም ነጭ ጢም ያለው አንድ እብድ አዛውንት፡ ሳይንሳዊ ጥናትና፡ ምርምርን በመቃወም፡ 'እዚያ ላይ ውኃ አለ፡' ይላል። እንዴ፡ ምስኪን አዛውንት!" አዘኑለት። "ተውት፥ እርሱ፡ በቅርቡ አእምሮውን እንደሳተ ይገለጻል። አእምሮውን ስቷል።"

268 እርሱ ግን የጌታ ቃል ነበረው። በዚያ ላይ፡ መሥራቱን ቀጠለ፡ እግዚአብሔርም የጥፋት ውኃ እንደሚመጣ ማስረጃ እያሳየ ነበር። ያም ለእነርሱ ምልክት ነበር። በኖኅ ታሪክ ያላመኑት በጨለማ ውስጥ ተቅበዘበዙ፡ መጨረሻቸውም ሞት ሆነ፡ በውኃ ውስጥም አለቁ፡ ወደ ገሃነም መቃብርም ወረዱ።

269 ፈርዖን፡ በአንድ ወቅት ተመለከተ። እርሱ ያየው ምንድን ነው፡ ፈርዖን ምን አየ? እርሱ ያየው "ባለ ብዙ የነጻ-አውጪ ሰያሜዋ፡ ራሱን ነቢይ-ነኝ ባይ፡ አንድ አክራሪ" ነበር። እርሱ ያየው ይህንን ብቻ ነው፥ የጭቃ-አቡኪ፡ አንድ ባሪያ በሕዝቡ መካከል ተነስቶ፡ ተአምራትን እንዲያደርግ ከእግዚአብሔር እንደተላከ ሲናገር ነው ያየው። ለምን፡ ያ ሰው አእምሮውን እንደሳተ አሰቡ… እንዲህም አሉ፡ "ተዉት፡ መዘላበዱን ይቀጥል። እርሱ… ከጥቂት ጊዜ በኋላ 'እብድ፡' መሆኑን ይገልጻሉ" አሉ።

270 እርሱ ግን **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል** ነበረው። አማኞቹ፡ አሮን፡ ኢያሱና፡ ሌሎች ብዙዎቹ፡ በሙሴ ውስጥ እግዚአብሔርን አዩ። ሙሴም፡ የእግዚአብሔርን ሥራ ሠራ፡ እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ መሆኑን ያወቁትም ለዚህ ነው። ተመልክተውም እግዚአብሔርን በሙሴ ውስጥ አዩት።

271 ባለጠጋው ሰው ተመልክቶ ማን እንደነበረ በትክክል አወቀ። አያችሁ? ነገር ግን የዓለምን ነገሮች፡ አብዝቶ ሰለወደደ፡ ኢየሱስን ከመከተል ይልቅ፡ እምቢ አለ።

272 የዚያ ዓይነት፡ ስንት ባለጠጋ ሰው ይህንን ካሴት ያዳምጥ ይሆን! ሁልጊዜም በገንዘብ ባለጠጋ መሆን አይጠበቅባችሁም፥ አይደለም፡ ምናልባትም በፍትወት ባለጠጋ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ በዚህ ሕይወት ተድላዎች ባለጠጋ ልትሆኑ ትችላላችሁ። ስንት ወንዶች፡ ስንት ወጣት ሴቶችና፡ ስንት ወጣት ወንዶች ናቸው፡ አንዲት የፍትወት ንግሥት፡ ወይም ባንጆ ወይም ጊታር ይዞ ወጥቶ፡ በሆነ ሮክ-ኤንድ-ሮል ለሚያዝናና ለሆነ ሪኪ፡ ወይም ሊደንሰው ለሚችለው ለሆነ ዳንስ ታዋቂነት ሲሉ ራሳቸውን አሳልፈው የማይሰጡት! እዚያው ስብሰባዎቹ ውስጥ ተቀምጠው፡ የእግዚአብሔር እጅ ሲንቀሳቀስና፡ ቃሉን ሲያውጅ እየተመለከቱ ስንቶቹ ናቸው የታዋቂነት ሀብታቸውን መርጠው እምቢ የሚሉት! ይህንን የሚያደርጉት ስንቶቹ ናቸው!

273 የሐይማኖት ተቋሙን መረጠ። በዚያ መኖር ይችላል። ለሐይማኖት ተቋሙ፡ "ኢየሱስ አክራሪ" ነበር። ስለዚህም ኢየሱስ ያለውን መቀበል ነበረበት፡ አለዚያ ደግሞ…

274 ለምን ወደ ካህኑ ሄዶ፡ "የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ምን ላድርግ፡" አላለውም? ካህኑ ስለዚያ ምንም እንደማያውቅ እርሱ ያውቅ ነበር።

ስለዚህም ወደ ኢየሱስ መጣና፡ እንዲህ አለ፡ "ምን ላድርግ? "

275 ኢየሱስም፡ "ትእዛዛትን ጠብቅ" አለው። ቀጥታ ወደ እርሱ መለሰበት።

እርሱም፡ "ይህንን አድርጌአለሁ" አለው።

276 እርሱም፡ "ትእዛዛትን ጠብቅ" አለ። ከዚያም፡ አሁንም ቢሆን የዘላለም ሕይወት አልነበረውም፡ እንደሌለውም ያውቅ ነበር። ትእዛዛትን ሁሉ ልትጠብቁ ትችላላችሁ፡ ሆኖም ገና፡ የዘላለም ሕይወት አላገኛችሁም።

277 ስለዚህ ኢየሱስም፡ “አሁን ትክክል የሆነውን ማድረግ ከፈለግህ፡ ሄደህ ያለህን ሸጥ፡ ለድሆችም ስጥ። መጥተህም፡ ተከተለኝ” አለው።

278 ይህ ግን ለእርሱ እጅግ ከባድ ነበር። አያችሁ? እርሱ ተመልክቶ ማን እንደነበረ እንዳወቀ እናገኛለን፡ ቢሆንም ግን እምቢ አለ። ቀጣዩም እይታው በገሃነም ውስጥ ነበር፡ ወደ ላይ ተመልክቶም አልዓዛርን በአብርሃም እቅፍ ውስጥ አየው።

279 በአንድ ወቅት፡ አምጥተውት በነበረ ጊዜ፡ ጵላጦስ ተመለከተው። ከዚህ በፊት አይቶት አያውቅም ነበር። እጆቹ ታስረው፥ ደም ከጀርባው እየፈሰሰ፥ የእሾህ አክሊል በራሱ ላይ ተደፍቶ ነበር። ጲላጦስም ተመልክቶ፡ እርግጠኛ ሆነ።

280 ምክንያቱም፡ ፈረስ እየጋለበ በመንገዱ ላይ መጣ፡ ፈረሰኛውም ዘሎ በመውረድ፡ ሮጦ መጣና፡ “ይኸውልህ፡ ሚስትህ ደብዳቤ ልካልሃለች” አለው።

281 እርሱም ሲመለከተው፡ እንዲህ አለች፡ “የተወደድክ ባለቤቴ፡ ጲላጦስ ሆይ፡ በዚያ ጻድቅ ሰው ላይ ምንም አታድርግ፡ በእርሱ ምክንያት ዛሬ በሕልም ብዙ መከራ ተቀብያለሁና” አለች።

282 እርሱም ተንቀጠቀጠ። ጉልበቶቹም እርስ በርስ ተላተሙ። እርሱም፡ “አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ፡ አንተ ንጉሥ ከሆንክ፡ ለምን አትናገርም? አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህን” አለ?

እርሱም፡ “አንተ አልህ” አለው።

“እውነቱን ንገረን፡” አለው።

283 እርሱም፡ “እኔ ለዚህ ተወልጃለሁ” አለው። ጲላጦስም ተደነቀ። እርሱ...

284 ሁሉም፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በእግሮቹ ሥር እየለመነና እያለቀሰ ነበር። እርሱም፡ “ልገድልህ ሥልጣን አለኝ፡ ወይም ደግሞ ልፈታህ ሥልጣን አለኝ” አለው።

285 እርሱም፡ “ከአባቴ ካልተሰጠህ በቀር፡ ምንም ዓይነት ሥልጣን የለህም” አለው። በለው!

286 ወዳጄ፡ እርሱ ከሰው በላይ እንደሆነ አምኖ ነበር። እርሱ ከሰው በላይ እንደሆነ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆኖ ነበር። በእርግጥም፡ አዎ ነበር። ነገር ግን (ምን? ) ፖለቲካውና ታዋቂነቱ እጅግ ትልቅ ነበር። አያችሁ፡ እርሱን እምቢ አለው። ታዋቂነቱ እጅግ ትልቅ ነበር። ይህንን አክራሪ ለመቀበል፡ ፖለቲካውና፡ በሕይወት ያለው ሥልጣን፡ እጅግ ትልቅ ነበር።

287 እውነተኛው ጌታ ኢየሱስ ዛሬ ባለበት ሁኔታ ለመቀበል፡ በሆነ የሐይማኖት ተቋም ውስጥ ያላችሁ ሥልጣን እጅግ ትልቅ የሆነባቸው፡ ስንት ጲላጦሶች ይህንን ያዳምጡ ይሆን ብዬ አስባለሁ።

በመስቀል፡ አጠገብ የነበረው ሮማዊ ወታደር፡ ወደ ኢየሱስ ተመለከተ።

288 ምድር በድንጋጤ ከራደች በኋላ፡ አለቶች ከተራሮች ላይ እስኪገነጠሉ ድረስ ተናወጠች። ፀሐይም በቀትር ጠለቀች፡ ጨለመችም። ከዋክብትም ብርሃናቸውን ለመስጠት አልወጡም። ምድርም በአለቶችና በመሬት መናወጥ ተሰነጠቀች። ዚግ-ዛግ መብረቅም ሰማያትን እናወጠው፥ የቤት መቅደሱንም

መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ቀደደው። ሕዝቡም፡ እየሮጡና እየጮሁ ነበር፡ ምን እንደተፈጠረ አላወቁም ነበር።

289 በዚያም እርሱን በመቸንከር የረዳው፡ ሰይፉን በልቡ ውስጥ የወጋው ያ ሮማዊ ወታደር፡ ተመለከተው፡ ነገር ግን በጣም ረፍዶ ነበር። ተመልክቶም አመነ፡ ነገር ግን ለማመን ለእርሱ በጣም ረፍዶ ነበር። ያደረገው ነገር ፍርዱን አትሞት ነበር፥ የአዳኙን ልብ በጦር ወግቶት ነበርና። በጣም ረፍዶ ነበር።

290 ዛሬ ሰንት ሮማውያን ያንኑ ነገር እንዳደረጉ፡ እንዲሁም ያንኑ ነገር እንደሚያደርጉ እሰባለሁ። አንድ ቀን፡ ትመለከቱ ይሆናል፡ ነገር ግን በጣም ረፍዶ ሊሆን ይችላል። በዛሬው ዘመን ያሉ ብዙዎች በዚያ ቀን ይመጣሉ በተመሳሳይ ሁኔታም ውስጥ ይሆናሉ። አውቀዋልና።

291 ወንድም ውድ እዚህ አለ፥ ትናንትና። ይህንን የምናገረው በዚህ መልእክት ውስጥ ስላለ ብቻ ነው። እዚህ ታች ስላይደር ካምፓኒ ውስጥ፡ አንድ የሮማ ካቶሊክ ሰው ተቀምጦ ነበር። እዚህ ላለው ቤተክርስቲያን የተወሰነ ሲሚንቶ ለመግዛት፡ ወደ ታች ወረደ፡ በዚያን ጊዜም፡ ለምን እንደፈለገው ነገረው። የሮማ ካቶሊኩም፡ “ወንድም ብራንሃም ነው እንዴ” አለ?

“አዎን።”

292 እርሱም፡ “አንድ ነገር ልናገር እወዳለሁ፡ እርሱ ሲጸልይ፡ እግዚአብሔር ይመልሳል” አለ። አያችሁ?

293 እንግዲህ ይህንን እያወቁ፡ በእርግጥ የሚሰራው ወንጌሉ፡ እንጂ እኔ፥ ወይም ክርስቶስን የሚወክል ማንም ሰው እንዳልሆነ ማረጋገጫውን እያዩ፡ ያሰገርማል። እየተነጋገርን ያለነው ሰለ ቃሉ እንጂ፡ ሰለ ሰው አይደለም።

294 ምን ለማለት እየሞከርኩ ነው? ይህ ነው፡ ይህም፡ እንደ ጲላጦሰና እንደ ሌሎቹም፡ እንደ ሮማዊው ወታደር ያሉት፡ የተረጋገጠውን ቃል በግልጽ ያዩታል፡ ነገር ግን ሰለዚህ ነገር አንድ ነገር ለማድረግ በጣም እስኪረፍድ ድረሰ ትጠብቃላችሁን? ጦሩን በሌላ መንገድ ሊጠቀምበት በተገባው ነበር። ልክ በኖኅ ዘመን እንደነበረው፡ በሮቹ ይዘጋሉ፡ በዚያን ጊዜ በጣም ረፍዷል። ምናልባትም አንድ ጧት ከእንቅልፋችሁ ነቅታችሁ፡ “ከዚህ ውጥንቅጥ ለመውጣት እሰባለሁ፡” ትሉ ይሆናል። ብዙ አትጠብቁ። አሁን ብትመለከቱና በሕይወት ብትኖሩ ይሻላችኋል።

295 ሉተር ከካቶሊክ የሐይማኖት ተቋም ዘወር ብሎ ተመለከተ። ምን አየ? የእሳት ዓምድ። ራሷን የቻለች ቤተክርሰቲያንን አየ።

296 ዌሰሊም ከአንግሊካን የሐይማኖት ተቋም ዘወር ብሎ ተመለከተ። እርሱም ያንኑ ነገር አየ።

297 ጴንጤቆሰጤዎች ከሐይማኖት ተቋማት ሁሉ ዘወር ብለው ተመለከቱ። ምንሰ ሆኑ? ታላቅና፡ ኃያል ሕዝብ።

298 እያንዳንዳቸው ምን አደረጉ? መሥራቾቹ፡ ሉተርና፡ ዌሰሊ፡ እንዲሁም እነርሱ፡ ዘወር ብለው ሲመለከቱና ያዩትን ነገር አድርገው ሲጀምሩ፥ ከኋላቸው የሚመጡት፡ ልጆቻቸው ግን፡ ከመጡበት ወደ ኋላ፡ ወደ ሐይማኖት ተቋሙ ተመለከቱ፡ ከዚያም ያንን ሕዝብ ይዘውት ከወጡበት ወደዚያው ውጥንቅጥ መለሱት።

299 ምን እየተመለከታችሁ ነው? መሥራቾቹ በትክክል ተመልክተዋል። ነገር ግን እነርሱን የተከተሉት፡ ሰዎች፡ መሥራቾቹ ወደ ወጡበት ወደ ኋላ ተመለከቱ፡ በእግዚአብሔር የተቀባው፥ መሥራቹ የተቃወመውን ያንኑ ነገር በትክክል አደረጉ።

300 ታውቃላችሁ፡ የጸሎት መስመር ስለሚጠብቀኝ፡ መቸኮል አለብኝ፡ ብዙዎቻችሁም መጓዝ እንዳለባችሁ አውቃለሁ።

301 አንድ ቀን ተመለከትኩ። ቃሉ ሥጋ ሆኖ አየሁ። አልፋና ኦሜጋን አየሁ። ፈጽሞ ሦስት፡ አራት፡ ወይም አምስት አላየሁም፥ አንድ አየሁት። እርሱን እንደ አዳኜ አየሁት። እርሱን አየሁት፡ ቃሉን። እርሱን አየሁት፡ ብርሃኑን። እርሱን አየሁት፡ ኃያሉን አምላክ። በውስጡ እግዚአብሔርን አየሁ። የእሳት ዓምድን አየሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ የተናገረውን፡ በትክክል፡ በእርሱ ውስጥ አየሁ። እርሱ አልፋና ኦሜጋ እንደሆነ፡ እርሱ የእሳት ዓምድ እንደሆነ አየሁ። ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው። የእሳት ዓምድ፡ ለዮሐንስ ሲናገር አየሁ፡ "ፍጹም-የማይለየው ሕልውናው።" በዚያ፡ በዮሐንስ ላይ እንደተናገረው፡ "ፍጹም-የማይለየው ሕልውናው ከቶ አይተዋችሁም።" ወንድሜ፡ ዛሬ ማታ ሀሳቤ ይህ ነው፡ ያንን መዝሙር ዘምሩ፥

> ተመልከትና ኑር፡ ወንድሜ ሆይ፡ በህይወት ኑር!
> ወደ ኢየሱስ ተመልከትና በሕይወት ኑር፥
> በቃሉ ተመዝግቧልና፡ ሃሌሉያ!
> የሚጠበቅብህ "ተመልክተህ በሕይወት መኖር" ነው።

302 ተመልከቱ! ምን ታያላችሁ? ነጻ መውጣትን ታያላችሁን? ምን እንደሆነ ታያላችሁን? በቃሉ ውስጥ ተመልክታችሁ በዚያን ጊዜ ምን እንደነበረ እዩ፡ ከዚያም በዚያው ቃል ውስጥ ተመልክታችሁ ዛሬም እንደዚያው መሆኑን እዩ። በምድረ በዳ ለነበረው የናስ እባብ እርሱ እውነተኛው ምሳሌ ነው፡ ለዚያው ለኃጢአትና ለበሽታ፡ ምክንያት የተሰጠ ነው።

303 ይሁዳም አንድ ቀን፡ ተመለከተ። ከተመለከተም በኋላ፡ እርሱን በሚገባ ካየው በኋላ... ከዚያ በፊት ይመለከት የነበረው፡ እነርሱ የነበራቸውን የገንዘብ ቋት፡ ግምጃውን ብቻ ነበር። አንድ ቀን ግን ተመልክቶ ኢየሱስን ባየው ጊዜ፡ ምን እንዳየ ታውቃላችሁ? ጥፋተኛ እንደሆነ አየ። በሕይወት ለመኖር እንደማይገባው አየ፡ ታንቆም ሞተ።

304 አንድ ጧት፡ በታሪክ ዘመናት ሁሉ ከነበሩት ታላላቅ ጧቶች አንዱ ነበር። በመደምደሚያዬ ላይ፡ ይህንን እናገራለሁ። በኢየሩሳሌም አንድ ነገር እየሆነ ነበር፡ በድንገትም አንድ የጦር ሠራዊት ቡድን ወ—ወደ ወህኒ ቤቱ ወረደ። የ—የሰንሰለቶች ጩኸት ይሰማኛል፥ ጦር በመንገዱ ላይ ሲጎተት እሰማለሁ።

305 እዚያ ውስጥ ያለው ማነው? በርባን። ለመሞት ተዘጋጅቷል። ሌባ ነው። እርባና ቢስ ነው። ወንበዴ ነው። ነፍስ ገዳይ ነው። ሊሞት ነው።

306 በመጀመሪያ ደረጃ፡ እንዲህ አለ፡ "እንግዲህ፡ ይህ ሁሉ ለእኔ ነው። ዛሬ ጧት እገደላለሁ" አለ።

307 በመጀመሪያ ደረጃ ይኸውላችሁ፡ ዘበኛው በሩን ከፈተና፡ "ውጣ፡ በርባን" አለው።

እርሱም ወጣና፡ “እንግዲህ፡ መጨረሻው ይህ ይመስለኛል” አለ።

እርሱም፡ “በርባን፡ አንተ ሙሉ በሙሉ ነጻ ነህ” አለው።

“ምን? እኔ ምን? እኔ... ”

“ሙሉ በሙሉ ነጻ! ነጻ ነህ፡” አለው።

እርሱም፡ “እንዴት ነጻ ልሆን እችላለሁ” አለ?

308 እርሱም እንዲህ አለው፡ “እንግዲህ፡ ወደዚህ ና፡ በርባን፡ **እዚያ** ወደ ላይ ተመልከት። እዚያ ላይ እየሞተ ያለውን ያንን ሰው እየኸው? እርሱ የአንተን ቦታ ተክቷል።”

309 ዛሬ ማታ፡ ሁላችንም ተመልክተን፡ በርባን ያየውን ማየት እንችል ይሆን እላለሁ፡ የሆነ ሰው የእኛን ስፍራ ሲወስድ? “እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፡ ስለ በደላችንም ደቀቀ። የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል፡” እኔ ተፈወስኩ፡ እናንተ ተፈወሳችሁ። እንግዲህ እኛ፡ መታመም የነበረብን፡ ጥፋተኞች ሆነን ሳለን፡ ነጻ መውጣታችንን በእርሱ ውስጥ ማየት እንችል ይሆን? ወደ ገሃነም መውረድ የነበረባችሁ እናንተ፥ ነጻነታችሁንና፡ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግቢያችሁን በእርሱ ውስጥ ተመልከቱ። በርባን በዚያ ቀን ያየውን እናንተም ማየት ትችሉ ይሆን እላለሁ?

310 እርሱም፡ “ጥቂት ዘመን አልፎ ዓለም ከእንግዲህ ወዲህ አያየኝም፡ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ” አለ። ኦህ፡ ቤተክርስቲያን! ታዲያ፡ “ታዩኛላችሁ፡” ካለ፡ ይህ ዳግመኛ መመልከት እንደምትችሉ ማረጋገጫ ነው። “እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር፡ እንዲያውም በእናንተ ውስጥ ስለምሆን፡ ታዩኛላችሁ።” መቼ? እንዴት ነው የምታዩት? በቃሉ ውስጥ። እርሱ ቃሉ ነው። ተስፋው ምን እንደሆነ ለማየት ወደ ቃሉ ተመልከቱ፡ እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነውና።

311 በገሊላ ሲመላለስ ምን እንደነበረ፡ ዛሬ ማታም በጀፈርሰንቪል ያው ነው፡ በብራንሃም ተብርናክልም ያው ነው። ለማየት የምትመለከቱት ምንድን ነው፡ መሥራችን፡ የሐይማኖት ተቋም ሰውን ነው? ያንን በኢየሱስ ውስጥ ፈጽሞ አታዩም። ታላቅ ካህን የሆነ ሰውን ለማየት ትመለከታላችሁን? ያንን በኢየሱስ ውስጥ ፈጽሞ አታዩም። አይ። ኢየሱስን የምታዩት እንዴት ነው? የእግዚአብሔር ቃል ሲገለጥ ነው፡ ምክንያቱም እርሱ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል ነበርና። በዚያን ጊዜ ምን እንደነበረ፡ ዛሬ ማታም ያው ነው፡ ለዘላለምም ያው ይሆናል።

312 ለአፍታ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። ይህንን በመጠኑ አሳጥረዋለሁ።

313 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ከሕይወት ጭንቀቶች ዘወር ብዬ እንድመለከት፡ ጸሎቴ ነው። ጌታ ሆይ፡ እ—እኛ ተራ ሰዎች፡ ያልተማርን መሆናችንን አውቃለሁ። የዚህ ዓለም ንብረት ብዙም የለንም፡ ነገር ግን እንወድሃለን፡ ጌታ ሆይ።

314 ለዚህም ሕዝብ እናገራለሁ። ከአንተ ውጪ ሌላ ማናቸውንም ነገር ለማየት ወደዚህ የመጡ ቢሆን ኖሮ፡ እንደዚህ ባለ ስፍራ፡ ተቀምጠው፥ በሕዝቡ መሃል እየተጋፉና እየተጨናነቁ፥ በ—በሙቀት እየተቃጠሉ፡ ወይም በብርድ እየተንቀጠቀጡ፡ አይቀመጡም ነበር፡ በዚህ ቆመው... እንዲሁም ልጆቻቸውን፡ የታመሙትንና የተሰቃዩትን፡ ይዘው በመምጣት፡ በዚህ ዙሪያ አይገኙም ነበር።

ጌታ ሆይ፡ እነዚህ ሰዎች፡ ሰውን ለማየት ፈጽሞ አይመጡም። በመንገድ ላይ ብዙ ሰዎች አሉ፥ ሁሉም ይመሳሰላሉ።

315 ዳሩ ግን ያንን ሰው ለማየት መጥተዋል፡ ያንን የእግዚአብሔር ሰው፡ በሥጋ የመጣውን የናዝሬቱን ኢየሱስን፡ እግዚአብሔር የሆነውን። አሁን፡ አባት ሆይ፡ “ጥቂት ጊዜ አለ፡ ዓለም ከእንግዲህ ወዲህ አያየኝም፡” ብለህ ነግረኸናል፡ ምንም ያህል ቢመለከቱ፡ ፈጽሞ አያዩትም። ነገር ግን አንተ፡ “እናንተ ታዩኛላችሁ” አልህ፡ እውነተኛው አማኝ ማለቴ ነው፡ “እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር፡ በውስጣችሁም እሆናለሁና” ብለሃል። ብንመለከት፡ እንደምናይህ፡ ተስፋ ሰጥተኸናል። ዛሬ ማታም፡ ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፡ እንደገና በእኛ ላይ እንድትፈጽመው እጸልያለሁ፡ ከእንግዲህ ወዲህ ጌታ ሆይ፡ ዘወትር ያደርግ እንደነበረው፡ ቃሉን እየፈጸመ፡ ኢየሱስ ራሱን ለእኛ ሲገልጥ፡ ተመልክተን ማየት እንችል ዘንድ እጸልያለሁ።

316 ከዚህ በፊት፡ አንድ ቃል ተናግሬ ነበር፡ ስለ ስህበቶቹም፡ እነዚህን ነገሮች በእውነት ከልቤ ተናግሬአለሁ፡ አንተም ነግረኸኛል። አሁንም፡ ምንም እንኳ ምስጢራዊ ቢመስልም፡ የውስጥ ሕሊናችንን ቀስቅሰን ማስተዋል ብንችል፡ ከእግዚአብሔር ካልመጣ በቀር፡ እነዚህ ነገሮች በትክክል እንዳሉት ሆነው፡ አስቀድመው ሊነገሩ እንደማይችሉ እናይ ነበር።

317 ያ የመጀመሪያው ነገር ሲፈጸም እንዴት ልናይ እንችል ነበር? ሁለተኛውስ እንዴት ሊፈጸም ይችል ነበር? ሦስተኛውስ እንዴት ሊፈጸም ይችል ነበር? ከመፈጸሙ ከወራት በፊት እዚህ ቆመን፡ በቱክሰን ምን እንደሚፈጠር፡ እንዴት ልንናገር እንችል ነበር? እንዲሁም ሰባቱን ማኅተሞች የሚፈታ፡ ምስጢሩንም የሚመልስ፡ ከዘመን መጀመሪያ ጀምሮ ተሰውረው የነበሩትን፡ የእግዚአብሔርን የተሰወሩ ነገሮች የሚገልጥ መሆኑን እንዴት እናውቃለን። ይህንንም ሰናይ፡ ተመስክሮለታል፡ አማኝ ቆሞለታል፡ በሳይንስም ተረጋግጧል!

318 ጌታ ሆይ፡ አንተ መሸሸጊያችንና ኃይላችን ነህ። ያለን ሁሉ አንተ ነህ። ስለዚህም፡ ጌታ ሆይ፡ የዚህ ታላቅ አሠራርህ አካል ስለሆንኩ፡ አመሰግንሃለሁ። እዚህ ካሉት፡ የዚያ አካል ብልቶች ከሆኑ ብዙዎች ጋር፡ እንዲሁም በዓለም ዙሪያ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከሚገኙ፡ የክርስቶስ ምስጢራዊ አካል ብልቶች ከሆኑ ብዙዎች ጋር፡ እኔም የአካልህ ብልት በመሆኔ አመሰግንሃለሁ።

319 በተመለከትን ቁጥር፡ እርሱን እናየዋለን! ወፎች ሲዘምሩ እናየዋለን። ፀሐይ ስትወጣ፡ ወይም ስትጠልቅ እናየዋለን። በመዝሙራት ውስጥ እንሰማዋለን። በሕዝቡ ውስጥ እንመለከተዋለን። ቃሉን ሲያጸና እናየዋለን።

320 ጌታ ሆይ፡ አንተ አምላካችን ነህ። ማልደን እንጠራሃለን። አንተ መሐሪ አባታችን ነህ። ስህተቶቻችንን ይቅር በለን።

321 ጌታ ሆይ፡ በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። በሮቹ በቅርቡ እንደሚዘጉ አይቻለሁ፡ የእድል በሮቹ። ጌታ ሆይ፡ ገና ቀን ሳለና ወደ አንዳንድ ስፍራዎች መግባት ስችል፡ እንድሄድ እርዳኝ። እያረጀሁ ነው፡ ብርታት ስጠኝ። ጌታ ሆይ፡ ወጣትነቴን አድስ። አሁን፡ ይህ ታላቅ ጊዜ እዚህ እስከሚሆን ድረስ፡ እየጠበቅሁ ሳለሁ፡ እዚያ ውጭ አንድ ነገር ማድረግ እንድችል፡ እርዳኝ። ጌታ ሆይ፡ እኔ ሰወጣ፡ ያ የጌታን የኢየሱስን መመለስ የሚያመጣውን፡ አስቀድሞ

የተወሰነው፡ የመጨረሻው ዘር፡ በሆነ ዘዴ፡ ማጥመድ እንድችል አቤቱ እርዳኝ። አምላክ ሆይ፡ እርዳኝ!

322 እንዲሁም ሌላው ሰው የሚቆምበትን መሠረት እየጣልኩ ከሆነ፡ ቃሉ ይፈጸም ዘንድ፡ ጌታ ሆይ፡ ቶሎ እንዲሆን፡ ይሁንልን።

323 የልባችን መሻት ቃልህ ሲፈጸም ማየት ነው። እንወድሃለን። እናምንሃለን። በማያምኑና፡ በሚጠራጠሩ ሰዎች መካከል፡ ጌታ አምላክ ሆይ ዛሬ ባ—ባ—ባለን ትውልድ መካከል፡ ቃልህ ፈጽሞ እንደማይወድቅ፡ አሁንም እናምናለን። "ሰማይና ምድር ያልፋሉ፡ እርሱ ግን ፈጽሞ አያልፍም፡" ብለን፡ እናምናለን። ለዚህም በድፍረት እንቆማለን።

324 አሁን፡ አባት ሆይ፡ ለጠበቁት ለዚህ አነስተኛ ቡድን። እዚህ ውስጥ ብዙ የታመሙ አሉ። እንዲሁም እዚህ ውስጥ ያልዳኑ ሊኖሩ ይችላሉ። የዳኑ፡ ሆኖም ግን ገና በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞሉ ሰዎች አሉ። ጌታ አምላክ ሆይ፡ ሕዝቡ ተመልክቶ ኢየሱስን ያይ ዘንድ፡ ከዚያም ተደፍቶ፡ ልቡን ለእርሱ ይሰጥ ዘንድ፡ በተሰፋ ቃልህ መሠረት ወደ ሰፍራው እንድትመጣ እጸልያለሁ። የታመሙትም ተመልክተው ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ማንም ይህንን ሊያደርግ እንደማይችል ይረዱ፡ ምክንያቱም፡ ይህ የቃሉ ተሰፋ ነውና።

325 ዛሬ የተናገርነው፡ ሁለቱም መልእክቶች፡ አሁንም ይረጋገጡ። ጌታ ሆይ፡ ሁሉም ነገር በእጅህ ውስጥ ነው። እኔም በእጅህ ውስጥ ነኝ። ጉ—ጉባኤውም በእጅህ ውስጥ ነው። ታላቁን ሰምህን ታከብር ዘንድ፡ ጌታ ሆይ፡ በእኛ በኩል ሥራ። ዘላለማዊ አምላክ ሆይ፡ ይህን ለእግዚአብሔር ክብር ይሁንልን። አሜን።

326 ሙቀት እንደሆነ አውቃለሁ፡ አሁንም ለታመሙት ለመጸለይ መሞከር እፈልጋለሁ። አሥራ አምሰት፡ ወይም ሃያ ደቂቃ ያህል ብትሰጡኝ፡ ስንት ካርዶችን እንዳደሉ አላውቅም፡ ዳሩ ግን ለታመሙት መጸለይ ልንጀምር ነው።

327 አሁን፡ ቢሊ እንዳደለ ነግሮኛል፡ ስንት ነበር? [አንድ ሰው፡ "ከአንድ እስከ መቶ" አለ።—እርታዒ።] መቶ-... ምን፡ ምን? [አንድ ሰው መለሰ።] መልካም። በሉ፡ እንጀምር። ከአንድ እስከ መቶ እንዳደለ ነግሮኛል። እዚህ የጸሎት ካርድ ያላችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? እጆቻችሁን አንሱ፥ የጸሎት ካርዶች ያሏችሁ። እንግዲህ፡ ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። ከቻልን፡ እስከቻልን ድረስ ወደ ሁሉም ለመድረስ እንሞክራለን። አሁን፡ በሁሉም ላይ የመንፈስ መለየት ሊኖረን አይችልም፡ ታውቃላችሁ፡ ስለዚህ እንዲሁ እንጸልያለን። እንዲሁም፡ ሁላችሁም፡ እዚህ የጸሎት ካርድ የሌላችሁ፡ ሆኖም የታመማችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? እጃችሁን አንሱ። ብዙዎች ናቸው።

328 አሁን፡ ተመልከቱ። ምንድን ነው? አሁን፡ ከፕሮግራማችን በጥቂቱ በ—በጣም ጥቂት፡ አሥራ አምስት ደቂቃ ያህል ዘግይተን ሊሆን እንደሚችል አውቃለሁ፡ ዳሩ ግን ይህንን አንድ ነገር መናገር እፈልጋለሁ። ይህ ነገር እዚህ፡ ዘላለምን በመንግሥተ ሰማያት ወይም በገሃነም የማሳለፍ ያህል፡ ልዩነት ሊያመጣ ይችላል። አያችሁ? ተመልከቱ፡ አክብሮት ይኑራችሁና፡ ለአንድ ደቂቃ ያህል ተመልከቱ፡ ቃሉን አዳምጡ፡ አሁንም ክርስቶስ ሆኖ መቀጠሉን ተመልከቱ።

329 አሁን፡ እዚህ ያለ እያንዳንዱ ሰው ምናልባትም ያውቀኛል። እኔ ግን ብዙዎቻችሁን አላውቃችሁም፡ ምክንያቱም እናንተን ለማወቅ የሚያስችል በቂ

ጊዜ እዚህ አላሳልፍም። ደግሞም ብዙዎቻችሁ ከከተማ ውጪ የመጣችሁ ናችሁ። ከከተማ-ውጪ-የመጣችሁ ሰዎች ስንቶቻችሁ ናችሁ? እጆቻችሁን አንሱ። አያችሁ?

330 አሁን፡ በቀደም፡ እዚያ ታች ከተማ ውስጥ ለአንድ ሰው ጥያቄ አቅርቤ፡ እንዲህ አልኩት፡ “ወደዚህ መጥተህ ታውቃለህን? ”

331 እንዲህ አለ፡ “እኛ ብንመጣም ምንም ፋይዳ የለውም።” እንዲህ አለ፡ “ከከተማ ውጪ የሚመጡ፡ በጣም ብዙ ሰዎች እዚያ ስለሚገኙ፡ ልንገባ አንችልም” አለ። አያችሁ?

332 ነገር ግን ያ—ያ ምንም አይደለም። የሚገቡበትን መንገድ እናመቻቻለን። በማንኛውም ሁኔታ፡ እናንተ ብቻ ኑ። አስተውሉ፡ ከእናንተ በፊት እነርሱ ዕድል ነበራቸው። አዎ።

333 አሁን አስታውሱ፡ አሁን፡ እኔ ወንድማችሁ ብቻ ነኝ። ይህንን እንደምትረዱት እርግጠኛ ነኝ። እኔ ሰው ነኝ፥ እርሱ እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር መሥራት የሚችለው፡ ሁልጊዜም ሲሠራ የኖረው፡ እንዲሁም የሚሠራው፡ በሰው በኩል ብቻ ነው። አሁን ዛሬ ማታ፡ ወደ እኔ ወይም ወደ ሌላ ማናቸውም ሰው ሳይሆን፡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ።

334 አሁን ዛሬ ማታ ተስፋ ወደሰጠው፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተመልከቱ። ከእናንተ ስንቶቻችሁ… ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ልሰጣችሁ እችላለሁ፡ ነገር ግን በዕብራውያን 13፥8 ላይ ያለውን፡ ይህም፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና… ”? እንዲሁም በዮሐንስ 14፥12 ላይ ያለውን፡ “እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ” የሚለውን ስንቶቻችሁ ታምናላችሁ? አያችሁ? እርሱ ያደረጋቸው እነዚያው ነገሮች፡ “የልብን አሳብ በመመርመር” መንገድ፡ ከመምጣቱ በፊት ልክ በመጨረሻው ዘመን ዳግመኛ እንደሚመለሱ ተስፋ እንደሰጠ ስንቶቻችሁ ታምናላችሁ? ኧ-ሀ። እርግጥ ነው። ሁላችንም እናውቀዋለን። መልካም። ኦህ፡ ሌሎች ስንት፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ፡ ነገር ግን እኛ እናውቀዋለን!

335 አሁን ተመልከቱ። አገልጋይን ለማየት አትመልከቱ። ፓስተርን ለማየት አትመልከቱ። ኢየሱስን ለማየት ተመልከቱ። ሰውን አታዩ፥ ኢየሱስን እዩ። ስትመለከቱ፡ እርሱን እዩት። ልረዳችሁ ብችል ኖሮ፡ አደርገው ነበር፡ ነገር ግን አልችልም። ልረዳችሁ አልችልም፥ እኔ ወንድማችሁ ብቻ ነኝ። እርሱ ግን፡ ጌታችሁ ነው፡ ወደ እርሱ ተመልክታችሁ እመኑ። መልካም።

336 እንግዲህ በጸሎት ካርድ ቁጥር እንጀምር… መልካም፡ ከቁጥር አንድ እንጀምራለን። ስንት… ቁጥር አንድ፡ የጸሎት ካርድ ቁጥር አንድ ያለው ማነው? እጃችሁን አንሱ። የት ነው ያለው? [አንድ ወንድም፡ “ልክ እዚያ ኋላ ነው” አለ።—አርታዒ።] ማለት… [“እየቆመች ነው።”] እሷ ነበረች እንዴ? ኦህ፡ ይቅርታ። መልካም። ቁጥር አንድ፡ ወደዚህ ነይ፡ እመቤት፡ እ… በየት በኩል ብታመጧቸው ይሻላችኋል፡ **በዚህ** በኩል? መልካም፡ መራመድ ከ—ከቻላችሁ፡ ልክ **ወደዚህ** ኑ። አሁን ከተጠሩት ውስጥ፡ ማንም አካለ ስንኩል ቢኖር፡ ወደዚህ እንድትመጡ አንዳንዶቻችን እንረዳችኋለን። ቁጥር አንድ።

337 ቁጥር ሁለት፡ የጸሎት ካርድ ቁጥር ሁለት ያለው ማነው? በተቻላችሁ ፍጥነት፡ እጃችሁን አንሱ። ቁጥር ሁለት፡ የት ነው ያለው? አላየሁትም። የት? ይቅርታ፡ ለ—ለማየት አልቻልኩም... ልክ እዚህ ጋር ናት፡ እመቤት።

338 ቁጥር ሦስት፡ ልትቆሙ ትችላላችሁን፡ ወይም አንዳች ምልክት ታሳያላችሁን? ልክ ነው፡ ቁጥር ሦስት።

339 ቁጥር አራት። የጸሎት ካርድ ቁጥር አራት፡ እጅህን ታነሳለህ? የት ነው ያለው? አላየሁትም። የጸሎት ካርድ ቁጥር አራት። ምን? ቁጥር አራት።

340 ቁጥር አምስት። ቁጥር አምስት ያለው ማነው፡ እጃችሁን ታነሳላችሁን? አላየሁትም። ቁጥር አምስት።

341 ቁጥር ስድስት። ቁጥር ስድስት። በፍጥነት፡ በጣም በፍጥነት፡ ቁጥር ስድስት። መልካም።

ሰባት። አንተ፡ ሰባት ነህ? መልካም። ልክ ነው።

342 ስምንት። ስምንት፡ አሁን በጣም በፍጥነት። ተነሱ፡ በጣም በፍጥነት። መልካም፡ ስምንት። በጣም ጥሩ፡ ጌታዬ።

ዘጠኝ። ዘጠኝ፡ የት ነው ያለው? ቁጥር ዘጠኝ። መልካም።

ቁጥር አሰር። አሰር፡ መልካም፡ አሰር፡ ልክ እዚህ ጋር። አሰር።

አስራ አንድ፡ አስራ ሁለት፡ አስራ ሦስት፡ አስራ አራት፡ አስራ አምስት።

343 በጣም ብዙ አንጠራም፡ ስለዚህ እንድት... አያችሁ፡ ይህን የምናደርግበት ምክንያት... ቁጥር የተጻፈበት ካርድ ብቻ ነው፡' አያችሁ፡ በዚሁ ቁጥርም መሠረት ትመጣላችሁ። ያም በሰልፍ እንዲቆሙ ያደርጋቸዋል።

አስራ አምስት። የጸሎት ካርድ አስራ አምስት። መልካም።

344 አስራ ስድስት፡ አስራ ሰባት፡ አስራ ስምንት፡ አስራ ዘጠኝ፡ ሃያ፡ ሃያ-አንድ፡ ሃያ-ሁለት፡ ሃያ-ሦስት፡ ሃያ-አራት፡ ሃያ-አምስት።

345 ሰልፋችሁ፡ እስኪስተካከል ድረስ፡ ሃያ-አምስት ያላችሁ፡ አሁን መጥታችሁ ሰልፍ ያዙ። አሁን በቁጥሮቻችሁ መሰረት ብቻ ተነሱ። ልክ ነው። ሁላችሁም በአንድ ጊዜ አትምጡ። እዚያ ማዶ ከሆናችሁ፡ ከቻላችሁ፡ በሌላኛው አቅጣጫ ዙራችሁ፡ ኑ። አሁን ሃያ-...

346 ስንት ነው የጠራነው፡ ሃያ-አምስት? [አንድ ወንድም፡ "ሃያ-አምስት" አለ።—አርታዒ።] መልካም፡ ለአንድ ደቂቃ ያህል ብቻ በሃያ-አምስት ላይ እናቁም። መልካም።

347 አሁንም የምለው፡ ለረጅም ጊዜ መቆም ካልፈለጋችሁ፡ ሰልፉ አጠር እያለ ሲመጣ ስታዩ፡ ከዚያም ከእነርሱ ጋር ትቀላቀላላችሁ፥ ሃያ-አምስት፡ ሃያ-ስድስት፡ ሃያ-ሰባት ኑ። ብቻ፡ መልካም፡ ጠብቁ፡ ሰልፉ ትንሽ አጠር ይበል፡ በጣም ለረጅም ጊዜ መቆም፡ አይኖርባችሁም።

አሁን ራሶቻችንን እናዘንብል።

348 ኦህ፡ ወዳጆች ሆይ፡ አሁንስ ምን ይሆን? አሁን የት ላይ ነን? አሁን በ—በመጨረሻው ላይ ነን። አንድ ነገር መደረግ ባለበት፡ "አዎ" ወይም "አይ"

በሚባልበት ጊዜ ላይ ነን። እግዚአብሔር ትክክል ወይም ስህተት ሆኖ መገኘት አለበት።

349 አሁን፡ ዛሬ እርሱ ምን እንደሆነ ልነግራችሁ እየሞከርኩ፡ ጊዜው እያለቀ እንደሆነ ልነግራችሁ፡ እርሱ ምን እንደሆነ፥ ምን እንደነበረ ለማሳየት፡ ሁለት ስብከቶችን አጥብቄ ሰብኬያለሁ። አሁንም ዛሬ ማታ፡ ስንመለከት፡ እርሱን እንመልከተው።

350 አሁን፡ እያንዳንዱ ሰው፡ በጌታ በኢየሱስ ስም፡ አሁን ቦታችሁ ላይ ተቀመጡ። አትዘዋወሩ። እስክትጠሩ ድረስ በጸጥታ ተቀመጡ። ትንንሾቹ ልጆች...

351 አሁን፡ "ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፡" ብዬ ብናገር፡ ወገኖቼ፡ በፍጥነት አድርጉት፡ ምክንያቱም እንደ ካንሰርና በሽታዎች ያሉ ክፉ ነገሮች፡ ከሰው ሲወጡ፡ በሕዝቡ መካከል ያልፉና፡ ወደ ሌሎች ሰዎች ይገባሉ። ይህንን የምታምኑ ሁሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስም መሆኑን የምታውቁ፡ "አሜን፡" በሉ። [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ክፉ መናፍስት በወጡ ጊዜ፡ ከአንዱ ወደ ሌላው ይሄዱ እንደነበረ፡ እናገኛለን። የሚገቡበትንም ስፍራ ለማግኘት ይሞክራሉ።

352 በስብሰባውም ውስጥ ይህንን ስንት ጊዜ አይተነዋል! ሰዎች ፈጽሞ ጤነኛና ደህና ሆነው፡ ወደ ስብሰባው ይመጣሉ፡ እዚያ ተቀምጠውም ይነቅፋሉ፥ ከአንድ፡ ወይም ከሁለት ቀን በኋላም፡ ሙሉ በሙሉ ታውረው፡ ወይም በካንሰር ተመትተው፡ አለዚያም ሽባ ሆነው ይገኛሉ። አያችሁ፡ ምክንያቱም እነርሱ የማያምኑ ነበሩና። እኔ ኃላፊነት የምወስደው ለአማኞች እንጂ፥ ለእነርሱ አይደለም። ከብዙ ዓመታት በፊት ከእነርሱ መካከል፡ ብዙዎቹ ወደ ተቋም ውስጥ ገብተዋል፡ አሁንም እዚያው ይገኛሉ፡ አንዳንዶቹም ትዕቢተኞችና፡ የማያምኑ በመሆናቸው ብቻ፡ ወደ መቃብራቸው ወርደዋል።

353 አሁን ለማያምን ሰው የሚሆን ስፍራ የለም። ይህ ስፍራ ለአማኞች ነው። በእግዚአብሔር እመኑ!

354 በሰማይ የምትኖር አባት ሆይ፡ አሁን ስብሰባው ያንተ ነው፥ ሁልጊዜም ቢሆን፡ ያንተው ነበረ። አሁን፡ ስለ ቃልህ ልናገር እችላለሁ፥ አሁን ግን፡ ከእንግዲህ ወዲህ፡ መናገር አልችልም። ጌታ ሆይ፡ አሁን የምትናገረው አንተ ነህ። አገልጋይህ እውነትን እንደነገራቸው ይታወቅ ዘንድ ይሁን። እዚህ ያሉ ሰዎች፡ ምናልባትም ብዙዎች እዚህ ታመው ይገኛሉ፡ በጸሎት መስመር ውስጥም አልገቡ ይሆናል፡ ዳሩ ግን ጌታ ሆይ፡ አንተ አሁንም እዚህ አለህ። በየትኛውም ስፍራ መፈወስ እንደምትችል ሁሉ፡ እዚያ ውጭም መፈወስ ትችላለህ። ቃልህ ይታወቅ ዘንድ ይሁን፡ በኢየሱስ ስም፡ እጸልያለሁ። አሜን።

355 አሁንም ለአንድ አፍታ ሙሉ ትኩረታችሁን ብታደርጉልኝ። በዚህ የጸሎት መስመር ውስጥ ያሉትን ልመለከት እወዳለሁ። በእውነት አንድም ሰው የማውቅ አይመስለኝም። በዚህ የጸሎት መስመር ውስጥ ያላችሁ፡ እናንተ፡ ሁላችሁም ለእኔ እንግዶች ናችሁ፡ እንደማላውቃችሁ ታውቃላችሁን? እንደዚያ ከሆነ እጆቻችሁን አንሱ። እንግዶች ናቸው። እዚያ ያላችሁ ስለ እናንተ ምንም እንደማላውቅ የምታውቁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? እዚያ ያላችሁ፡ እጆቻችሁን አንሱ፡

እያችሁ። በእርግጥ፡ እዚህ ካሉት ሰዎች ዘጠና-አምስት በመቶ የሚሆኑትን፡ አላውቃቸውም። ይህ እውነት ነው።

356 አሁን እዚህ አንዲት ምስኪን ሴት አለች፡ በሕይወቴ አይቻት አላውቅም። ለእኔ ሙሉ በሙሉ እንግዳ ናት። አሁን፡ እዚህ የመጣችው ስለ ሕመም ሊሆን ይችላል። እዚህ የመጣችው... ምናልባት ያደረገችው ነገር ሊኖር ይችላል። ምናልባት ለገንዘብ ችግር መጥታ ይሆናል። ምናልባት የቤተሰብ ችግር ሊሆን ይችላል። ምናልባት ደግሞ ስለ ሌላ ሰው መጥታ ይሆናል። አላውቅም። ምንም የማውቀው ነገር የለም።

357 ዳሩ ግን በዮሐንስ ወንጌል 4ኛው ምዕራፍ ላይ እንዳለው፡ በትክክል ያው ትዕይንት እዚህ አለ፡ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኝተዋል። ያለምንም ጥርጥር፡ ከኢየሱስ ጋር የተገናኘችው ያቺ ወጣት ሴት፡ እርሱ ከእርሷ በጣም በዕድሜ ይበልጣት ነበር፡ ምክንያቱም፡ "እርሱ፡" እንዳሉት፡ "አምሳ ዓመት፡ ወይም ከአምሳ ዓመት በላይ የሞላው ይመስል ነበር፡" እዚያ የውኃ ጉድጓድ አጠገብ የነበረችው ያቺ ወጣት ቆንጆ ሴት ደግሞ፡ ምናልባት ገና ወጣት ልጃገረድ ነበረች። አሁንም እዚህ ዛሬ ማታ፡ ሁለት ሰዎች፡ እንደገና ተገናኝተዋል፡ ወጣትና አዛውንት፡ አንዱ ሌላውን ሳያውቅ።

358 አሁንም እዚያ ቆማለች። እዚያ የቆመችበት የሆነ ምክንያት አለ። አላውቅም። አታላይ ሆና፡ እዚያ ቆማ ሊሆን ይችላል። ምንም ነገር ሳይኖር፡ ምን እንደሚፈጠር ለማየት ብቻ፡ የሆነ ነገር እየተናገረች፡ እዚያ ቆማ ሊሆን ይችላል። እንደዚያ ከሆነ፡ ምን እንደሚፈጠር ትመለከታላችሁ። እያችሁ? እያችሁ?

359 አሁን፡ ይህችን ሴት አላውቃትም፡ ፈጽሞ አይቻት አላውቅም። ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ለእርሷ እንግዳ መሆኔን ለማሳየት፡ እጅዋን አንስታ ነበር። እጄን አነሳለሁ፡ እርሷም ለእኔ እንግዳ ናት። ፈጽሞ አይቻት አላውቅም። እንግዲህ፡ አሁን እኔ ብ...

360 እንደ ተራ ሰው ሆኜ፡ እንዲህ ማለት ይኖርብኛል፡ "እመቤቴ፡ ችግርሽ ምንድን ነው? እዚህ ምን እየሠራሽ ነው? ምን ትፈልጊያለሽ?"

361 እርሷም፡ "አቶ ብራንሃም፡ እ—እኔ እዚህ የመጣሁት በ—በካንሰር ሰ—ሰለምሰቃይ ነው። የቲቢ በሽታ አለብኝ። እብጠት አለብኝ" ትል ይሆናል። ወይም፡ "ገንዘብ አልቆብኛል። እኔ... ባለቤቴ ትቶኝ ሄዷል።" ወይም፡ "እኔ አላገባሁም፡ ጓደኛዬም እንዲህ አድርጎኛል" ልትለኝ ትችላለች። መናገር ይኖርባታል።

362 "እንግዲህ፡" እኔ ደግሞ፡ "መልካም፡ እ—እ—እኔ እጸልይልሻለሁ፥ እጆቼንም እጭንብሻለሁና፡ እንዲህ እላለሁ፡ 'ጌታ አምላክ ሆይ ይህች ሴት የምትፈልገውን ስጣት። አሜን። ኢየሱስ ሆይ፡ አድርገው!'" እንድትሄድ አደርጋለሁ። እንግዲህ፡ ያንን ካመነች፡ እንደምትፈወስ አስባለሁ። ያ ምንም አይደለም። ያ ለብዙ፡ ብዙ ዓመታት የቆየ አገልግሎት ነበር።

363 ነገር ግን፡ ሰዶም ከመቃጠሏ ጥቂት ቀደም ብሎ፡ መጥቶ በሰው አካል ውስጥ አድሮ እንደነበረውና፡ ሣራ ወደነበረችበት ድንኳን ጀርባውን አዙሮ ተቀምጦ ሳለ፡ በድንኳኑ ውስጥ ምን እያሰበች እንደነበር ለአብርሃም እንደነገረው፡ መልአክ፡ እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመንም እንዲሁ

እንደሚሆን ተስፋ ተሰጥቶ ነበር፥ እግዚአብሔር፡ በሰው ሥጋ ሆኖ፡ የሰውን ልብሰ ለብሶ።

364 ዛሬም እግዚአብሔር ሊያደርገው የሚችለው በዚያው መንገድ ብቻ ነው፡ ያም በእናንተ ሥጋ ውስጥ ሲገባ ነው፡ አያችሁ፡ እግዚአብሔር በሰው ሥጋ እንደሚገለጥ በማሳየት።

365 ኢየሱስም፡ “በሰዶም ዘመን እንደነበረ፡ በሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል” አለ። እዚያ ታች በሰዶም ቢሊ ግራሃምና ሌሎቹ፡ መልእክተኞች አሉን፡ ዳሩ ግን የተመረጠችው ቤተክርስቲያን መልእክትንና መልእክተኛን ተቀበለች።

366 አሁንም፡ ይህች ምስኪን ሴት... መንፈስ ቅዱስ... ያደርገዋል አትበሉ፡ ነገር ግን ቢመጣና እዚህ የቆምሽው ለምን እንደሆነ ቢነግረኝ፡ ወ—ወይም ምን እንደምትፈልጊ፡ ወይም ያደረግሽውን ነገር፡ ወይም ደግሞ ልታደርጊ ያሰብሽውን ነገር ቢነግረኝ። አየሽ፡ ይህ ነገር መምጣት ያለበት ከተፈጥሮ በላይ ከሆነ ምንጭ እንደሆነ ታውቂያለሽ፡ ምክንያቱም ዝም ብለን እዚህ ቆመናልና፡ አየሽ። ያ ትክክል ይሆናል፡ አይደለም እንዴ? ታዲያ ያ ከተፈጥሮ በላይ ከሆነ ኃይል መምጣት እንዳለበት ታውቂያለሽ። መጽሐፍ ቅዱስም ኢየሱስ ያንኑ ነገር እንዳደረገ፡ በመጨረሻውም ዘመን ዳግመኛ እንደሚያደርገው ተስፋ ከሰጠ፡ እርሱ እንደሆነ ታምኛለሽ። ያንኑ ነገር የምታምኑ ስንቶቻችሁ ናችሁ? በዚያን ጊዜ ኢየሱስን ታዩታላችሁ። ቃሉን ታያላችሁ።

አሁን፡ “እርሱ ቃሉ ነውን” ትላላችሁ?

367 መጽሐፍ ቅዱስ እርሱ ቃል እንደሆነ ይናገራል። ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የልብን ስሜትና አሳብ እንደሚመረምር ይናገራል። ልክ ነው? እንደዛ ከሆነ አሳብን የሚመረምረው፡ በሰው ከንፈር በኩል የተነገረው ቃል ይሆናል።

368 አሁን፡ እኔ አልችልም። ያንን የማደርግበት ምንም መንገድ የለኝም፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም እኔ አላውቃትምና፥ እርሱ ግን ያውቃል፡ እርሱም ቃል ነው።

369 የውኃ ጉድጓድ አጠገብ እንደነበረችው ሴትና እንደ እርሱ፡ የሁለታችንንም መንፈስ ወስዶ፡ ማዋሃድ የሚችል፡ እርሱ ነው፥ ከዚያም ሄዶ እዚህ የመጣችው ለምን እንደሆነ፡ ምን እንዳደረገች፡ ወይም ምን እንደምትፈልግ፡ ወይም ደግሞ የሆነ ነገር ያሳየኛል። ከዚያም እኔ ልናገረው እችላለሁ፡ ያኔ ውሳኔው የራሷ ይሆናል።

370 አሁን እናንተ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ልትፈውሳት ትችላለህን” ትላላችሁ? አይ፡ አይደለም። ያንን ላደርግ አልችልም። እርሱ አስቀድሞ አድርጎታል። በእርሱ ቍስል እኛ ተፈወስን።

371 ይህ ግን የሆነው እምነቷን ለማሳደግ ብቻ ነው፡ እርሷ ምን እንደነበረችና፡ ምን እንደምትፈልግ፡ የሚያውቅ ከሆነ፡ እ—እርሱ ያንን እንዴት እንደሚሰጣትና ከዚህ በኋላም ምን እንደምትሆን የሚያውቅ መሆኑን እንድታውቅ ለማድረግ ነው። ልክ ነው? አሁን፡ ሁላችሁም ያንን ታምናላችሁ?

372 አሁን ታላቅ አክብሮት ይኑራችሁ። ደግሞም እዚያ ያላችሁ፡ የጸሎት ካርድ የሌላችሁ፡ ጸልዩ።

373 አሁን፡ አስታውሱ፡ አንድ ቀን ኢየሱስ በሰዎች መሃል ሲያልፍ ሳለ፡ አንዲት ምስኪን ሴት ልብሱን ዳሰሰች። እርሱም ዞር ብሎ፡ “የዳሰሰኝ ማን ነው፡”

አለ? እስከሚያገኛትም ድረስ ጉባኤውን በሙሉ ቃኘ፡ ደም ይፈሳት እንደነበረም ነገራት። በዚያን ጊዜም ደሟ ቆመ። አያችሁ?

374 አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ እርሱ አሁን “በድካማችን ሊራራልን የሚችል ሊቀ ካህን” እንደሆነ ይናገራል። ልክ ነው?

375 እዚህ ከባለቤቱ አጠገብ ተቀምጦ የሚገኘውን፡ ወንድም ዌይን እያየሁት ነው። በቅርቡ እኔ እየሰበክሁ ሳለ ይህ ሰው እዚህ ቆሞ ነበር፡ ልክ ጳውሎስ በአንድ ወቅት ሌሊቱን ሙሉ ይሰብክ እንደነበረው፡ ይህ ሰውም እዚሁ አድማጮች መሃል ሞቶ ወደቀ። መንፈስ ቅዱስም ቀጥታ ዳግመኛ ወደ ሕይወት መለሰው። እርሱም፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡” ለሚለው ምስክር ነው፡ አያችሁ።

376 ወንድም ዌይን ፈጽሞ አይታችሁት የማታውቁና፡ ማየት የምትፈልጉ ስንቶቻችሁ ናችሁ፥ ፈጽሞ አይታችሁት የማታውቁ፡ እጆቻችሁን አንሱ። ወንድም ዌይ፡ ቆም ትል ይሆን? ሰውዬው ይኸውላችሁ፡ ልክ አሁን በተቀመጠበት አካባቢ ገደማ ሞቶ ወድቆ ነበር። ፈቃድ ያላት ነርስ የሆነችው፡ ባለቤቱም ይኸውና፡ ልክ እዚያ ቆማለች። የልብ ትርታ አልነበረውም፡ ሞቶ ነበር፥ ዓይኖቹ ወደ ኋላ ተገልብጠው ነበር፡ ፊቱም ጠቁሮ ነበር፡ በልብ ድካም በሽታ ነበር።

377 ሐኪሙ የልብ ሕመም እንዳለበት ነግሮት ነበር። ከዚያም በፊት፡ በቅርብ ጊዜ፡ በመንፈስ መለየት አግኝቼው፡ የልብ ሕመም እንዳለበት ነግሬው ነበር። ከዚያም፡ በድንገት፡ ልቡ ቆመ፡ ወደ ታችም ወደቀ። እዚያም ተዘርሮ ነበር፡ ሙሉ በሙሉ፡ ሞቶ ነበር።

378 ጌታ ኢየሱስ ሙታንን ወደ ሕይወት ሲመልስ ያየሁት ያ ሰድስት ወይም ሰምንት ጊዜ ያህል ነው። ሲያደርገው አይቼዋለሁ፡ ዛሬ ማታም ሊያደርገው ይችላል።

379 አሁን እዚህ ያለውን፡ መንፈስ ሁሉ፡ ለእግዚአብሔር ክብር፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ከቁጥጥሬ ሥር አደርገዋለሁ። ጨዋዎች ሁኑ። ጠብቁ።

380 እመቤት፡ ላነጋግርሽ እፈልጋለሁ። አየሽ፡ ስሰብክ ነበር። መንፈስሽን ለመያዝ ያህል ነው፡ እያደረግሁ ያለሁትም በትክክል ያንን ነው። አየሽ?

381 በአንቺ ውስጥ የሆነ ነገር አለ፡ ሕይወት፡ አለዚያማ እዚያ አትቆሚም ነበር፥ ሕይወት የሌለሽ፡ ቅርጽ ብቻ ሆነሽ፡ ሞተሽ ትዘረሪ ነበር። ነገር ግን፡ በዚያ ሥጋ ውስጥ ሕይወት ስለአለ፡ ይቆጣጠርሻል። አያችሁ? ደግሞም አሁን አሳቦችሽና የምታስቢው ነገር፡ የምትናገሪያቸው ቃላትና፡ ማንኛውም ነገር፡ የምትኖሪበት ነገር ነው። አየሽ? የምትናገሪያቸው ቃላት፡ አሳቦችሽና፡ ማናቸውም ነገሮችሽ አንቺነትሽን ይገልጻሉ።

አሁን፡ እኛ፡ አምነን፡ እዚህ እንገኛለን። አሁን መንፈስ ቅዱስ...

ኢየሱስ ለሴቲቱ፡ “የምጠጣውን ውሃ ስጪኝ” እንዳላት ነው።

382 እርሷም፡ ባመጣች ጊዜ፡ እንዲህ አለች፡ “እንዴ፡ አንተ፡ አንተ ይህንን ልትጠይቀኝ አይገባም። እኔ ሳ—ሳምራዊት ነኝ። አንተ ደግሞ... አይሁዳዊ ነህ። እርስ በእርሳችን ምንም ዓይነት ግንኙነት የለንም፡ ምንም—ምንም ዓይነት፡ በመካከላችን የቃላት ልውውጥ የለም።”

383 አሁን፡ ግን፡ እርግጥ ነው፡ ሁለታችንም አሕዛብ ነን። እንዲሁም እዚህ ቆመን በእግዚአብሔር እናምናለን። አሁን፡ መንፈሱ ለስጦታ በአጠገቤ ቢያልፍና፡ ምን እንደሆነ ሊነግርሽ ቢችል፥ ያንን የሕይወት ክፍል ኖርሽዋልና፡ ያ ነገር ልክ መሆኑንና አለመሆኑን ታውቂያለሽ። ከዚያም፡ ከዚያም ያንን ለማመን፡ ስጦታው አለሽ። ደግሞም ያንን ካመንሽ፡ እርሱም ስለዚያ ነገር ቢነግርሽ፡ ከዚያ በኋላ ሁሉም ነገር ያበቃል። እዚህ ባለ ሰው ሁሉ ላይ ይሠራል። አሁን፡ ሁላችሁም ታላቅ ትህትና ይኑራችሁ።

384 ይህች ሴት በጉሮሮዋ ላይ ባለ የሆነ ችግር ትሠቃያለች። የጉሮሮ ሕመም ነው። ልክ ከሆነ፡ እጅሽን አንሺ። አሁን፡ በሕይወቴ ፈጽሞ አይቻት አላውቅም። ልክ ነው። እዚህ የመጣችው ለዚህ ነው፡ ለጉሮሮዋ እንድጸልይላት።

385 አሁን፡ ልክ በዚያን ጊዜ፡ ያንን እንዳልኩ፡ ወይም ትንሽ ቀደም ብሎ፡ እርሷ... አጠገቧ የሆነ ነገር እንደነበረ ታውቅ ነበር። ልክ በዚያን ጊዜ፡ የሆነ ነገር ወደ እርሷ ቀረበ። በእርሷ ላይ ስሜትን ማየት ትችሉ ነበር፡ ልክ፡ እንደነካት፡ በጣም ደስ የሚል ስሜት።

386 በፎቶግራፉ ላይ የምታዩት ያ ብርሃን። ጆርጅ፡ የት ነህ? በፎቶግራፉ ውስጥ የነበረው ያ ብርሃን፡ ልክ አሁን፡ ከሴቲቱ በላይ ማንዣበቡን ቀጥሏል። አያችሁ፡ በሌላ ዳይመንሽን ላይ ነው። እርሷ አማኝ ናት፡ አስመሳይ-አማኝ አይደለችም። አማኝ ናት።

387 አሁን፡ አማኝ እንደመሆንሽ፡ እኔ የእርሱ አገልጋይና ነቢይ መሆኔን ታምኛለሽን? ያንን ለማወቅ፡ መሆን አለበት። [እህት፡ “አዎ ጌታዬ፡” አለች።—አርታዒ።] በልብሽ ውስጥ ያሉትን ሌሎች ነገሮች ሊነግርሽ እንደሚችል ታምኛለሽን? [“አዎ፡ ጌታዬ።”] መልካም።

388 በልብሽ ውስጥ ያለው ነገር ይኸውልሽ። የምትጸልዩለት ሰው አለ፥ ልጅ ነው። ምን እንደሆነ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምኛለሽን? ቫይረስ አለበት። ልክ ነው? [እህት፡ “ልክ ነው። አዎ” አለች።—አርታዒ።] ማን እንደሆንሽ እግዚአብሔር ሊነግረኝ እንደሚችል ታምኛለሽን? [“አዎ፡ ጌታዬ።”] ወይዘሮ ዋከር ነሽ። [“ልክ ነው።”] የዚህ አካባቢ ሰው አይደለሽም። [“አይደለሁም።”] ከደቡብ ነሽ። [“ልክ ነው።”] ጆርጂያ። [“ልክ ነው።”] ተፈውሰሽ፡ ወደ ቤትሽ ትሄጃለሽ። ኢየሱስ ክርስቶስ አንቺንም ልጅሽንም ፈውሷል። ስለዚህ ነገር አትጨነቂ። አብቅቶለታል። እህቴ፡ እግዚአብሔር ይባርክሽ።

389 ጤና ይሰጥልኝ? አሁን እዚህ ሌላ ሴት አለች። አላውቃትም፡ ፈጽሞ አይቻት አላውቅም። እዚያ የቆመች ሴት ብቻ ናት። አሁን ተመልከቱ፡ ከሰምንት ሰዓት ገደማ ጀምሮ፡ በአጠቃላይ፡ ስሰብክ ነበር፡ አሁንም አሥር ሰዓት ሆኗል። እዚህ የቆየሁት ለሁለት ሰዓታት ነው። ያ አንዱ የመንፈስ መለየት ከሁለት ሰዓቱ ስብከት ይልቅ በጣም አድክሞኛል። አያችሁ? ያ... አያችሁ?

“ያንን ለማለት ፈልገህ ነው፡” ትሉ ይሆናል፥ ኦህ፡ አዎን።

390 የልብሱን ጫፍ የዳሰሰችው ያቺ ሴት። እርሱም፡ “ኃይል ከእኔ እንደ ወጣ አውቃለሁና” አለ፡ ብርታት። ልክ ነው? የሚያደርገው ያንን ነው።

አሁን፡ ፈጽሞ አይቻት የማላውቃት አንዲት ሴት እዚህ አለች።

391 አንድ ነገር አስተውላችሁ ከሆነ፡ ቢሊ ወደዚያ ሄዶ፡ እዚህ ከእኛ ጋር ያለውን ያንን ልጅ ጆርጅን፡ አነሳው። ባፕቲስት የሆነ ልጅ ነው። የምንናገረው ስለ እግዚአብሔር እንደሆነ እንዲያይ እፈልጋለሁ። አባቱ፡ ቤተሰቡ፡ ግሩም ሰዎች ናቸው። እነርሱ ሜክሲኮ ውስጥ ናቸው፡ ሚሰዮናዊ፡ ጥሩ ሰው ነው። ደግሞም፡ አባቱም ታሟል። እርሱ እስኪመጣ እየጠበቅሁት ነው። አሁን ጆርጅ፡ በቅርበት ተመልከት።

392 አሁን፡ ይህችን እመቤት፡ እ—እ—እኔ አላውቃትም። እ—እኔ ፈጽሞ አይቻት አላውቅም። እርስ በርሳችን እንግዶች ነን ብዬ እሰባለሁ። [እህት፡ "ልክ ነው" አለች።—አርታዒ።] አንዳችን ሌላውን አናውቅም።

393 አሁን ግን፡ የመንፈስ ቅዱስ፡ የኢየሱስ ሕልውና ጣዕም፡ እዚህ መሆኑን ሁላችንም እየመሰከርን ነው። አሁን ጌታ ኢየሱስ ስለ አንቺ የሆነ ነገር ቢገልጥልኝ...

394 አሁን፡ ልፈውስሽ ብችል፡ አደርገው ነበር፡ ነገር ግን እርሱ አስቀድሞ ያደረገውን ላደርግ አልችልም። ብቸኛው ነገር፡ የሰጠኝን፡ ይህንን ልብስ ለብሶ ዛሬ ማታ እዚህ ቆሞ ቢሆን ኖሮ፡ እንግዲህ፡ አሁን፡ እ—እርሱ ሊፈውስሽ አይችልም፡ ምክንያቱም አስቀድሞ አድርጎታልና። "በእርሱ ቊስል እኛ ተፈወስን።" አያችሁ? ነገር ግን ብቸኛው ነገር፡ ተስፋ በሰጠው ቃል መሠረት ራሱን ይገልጻል፡ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው መሆኑንም እንድታዩ ያደርግሻል። እንደሚያደርገውም ተስፋ ሰጥቷል።

395 አሁን እዚህ የመጣሽው ለምን እንደሆነ ለመናገር ቢጠቀምብኝ፡ የመጣሽበትን ነገር... እንደምትቀበዪ ለማመን፡ በእርሱ ላይ ያለሽን እምነት፡ ትጠቀሚያለሽን? በሙሉ ልብሽ? [ያቺ እህት፦ "አዎ፡ እጠቀማለሁ" አለች።—አርታዒ።] መልካም፡ ጌታ ያድርግልሽ።

396 እመቤቲቱ የሆነ ችግር እንዳለባት አያለሁ። ምርመራው እንደሚያሳየው ከሆነ የ—የጨጓራ መሰንጠቅ ነው። ልክ ነው። ይህ እውነት ነው፡ አዎን፡ ወዳጄ፡ የጨጓራ መሰንጠቅ ነው። ያንን መሰንጠቅ እግዚአብሔር ሊፈውሰው እንደሚችል ታምኛለሽን? [ያቺ እህት፡ "አዎ፡ ጌታዬ። ላምነው በምችለው ሁሉ አምናለሁ" አለች።—አርታዒ።] አንቺ፡ በምትችይው ሁሉ—ሁሉ... ["ላምነው በምችለው ሁሉ አምናለሁ።"] እግዚአብሔር ይባርክሽ።

397 አሁን፡ የዚህ አካባቢ ሰው አይደለሽም። ወደዚህ ለመምጣት ከፍተኛ መሥዋዕትነት ከፍለሻል። [እህት፡ "አዎ፡ ከፍያለሁ" አለች።—አርታዒ።] ነበረ። አዎ። አዎ። ከቴነሲ ነሽ። ልክ ነው። ወይዘሮ ሃርት። ተመለሺ፥ አትጠራጠሪ። ብታምኚ፡ ትፈወሻለሽ።

398 ጤና ይስጥልኝ፡ እመቤት? እርስ በርሳችን እንግዶች ነን። እስከማውቀው ድረስ፡ በሕይወቴ ፈጽሞ አይቼሽ አላውቅም። ምናልባት በሆነ ስብሰባ ውስጥ፡ አይቼሽ ይሆናል፡ አንቺም አይተሽኝ ይሆናል፡ እኔ ግን አላውቅሽም። እግዚአብሔር ያውቅሻል። የእርሱ አገልጋይ መሆኔን፡ የሰበክሁትም ቃል እውነት መሆኑን ታምኛለሽን? እንግዲህ፡ ላንቺ እንግዳ በመሆኔ፥ እኔ የሰበክሁትንም፡ ቃል፡ ያንን አምነሻል።

399 ብቸኛው ነገር፡ ይህ ነው፡ የሆነ ሰው ካርድ ሰጥቶሻል፥ ከአስተናጋጆቹ አንዱ፡ ወይም ልጄ፡ ወይም ደግሞ ሌላ ሰው ካርድ ሰጥቶሻል። ቁጥርሽ ተጠራ፥ እዚህም መጣሽ። የማውቀው ያንን ብቻ ነው።

400 ነገር ግን እዚህ ያለሽው፡ በነርቭ ሕመም እየተሠቃየሽ ነው። በጣም ያስቸግርሻል። አብሮሽ ያለ ሰው አለ። የምትጸልዪለት ሰው አለ። እርሱ... ባለቤትሽ ነው። ሊያልፈው ያልቻለው መንፈሳዊ ችግር አለበት። ደግሞም፡ የታመመ ልጅ አለሽ። የዚህ አካባቢ ሰው አይደለሽም፡ የመጣሽው ከሰሜን ነው። ከካናዳ ነሽ፡ ከአልበርታ። ያ ልክ ነው። እኔ የእግዚአብሔር ነቢይ መሆኔን አምነሽ፡ የምነግርሽም እውነት መሆኑን ካመንሽ፡ ወደ ቤትሽ ሂጂ ያገኘሽውንም ትቀበያለሽ። አዎ። እመኚ። እመቤቴ፡ እግዚአብሔር ይባርክሽ።

401 እኔ ለአንቺ እንግዳ ነኝ። አንቺ ለእኔ እንግዳ ነሽ። አላውቅሽም። እግዚአብሔር ግን ያውቅሻል። የእርሱ አገልጋይ መሆኔን ታምኛለሽን? [እህት፡ "አዎ፡ አምናለሁ" አለች።—አርታዒ።] በሙሉ ልብሽ? አላውቅሽም፡ ስለ አንቺ ምንም አላውቅም። ልፈውስሽ ብችል ኖሮ፡ አደርገው ነበር፡ እ—እኔ ግን አልችልም። እኔ ፈዋሽ አይደለሁም። እኔ ተራ ሰው ነኝ። እርሱ ግን እግዚአብሔር ነው። በእኔና በአንቺ መካከል አንዲት አዛውንት ስለቆመች፡ ትንሽ ግራ ተጋብቻለሁ። የምትጸልዪላት ሰው ናት። አዎ። እናትሽ ናት። በ—በከፍተኛ የደም ግፊት ትሠቃያለች። አንቺ ደግሞ የ—የኩላሊት ኢንፌክሽን አለብሽ። ያ ልክ ነው። ያንን ታምኛለሽን? ["አዎ፡ አምናለሁ።"]

402 እናትሽ እዚህ የለችም። ነገር ግን ወደ እርሷ ስትሄጂ፡ በአንገትሽ ላይ ያለውን ያንን ሻርፕ ወስደሽ፡ እናትሽ ላይ አድርጊው፡ አትጠራጠሪም፡ የደም ግፊቱም ከእርሷ ይለቃል፡ ያንቺም ኢንፌክሽን ይጠፋል። አሁንም ሂጂ፡ እመኚ።

403 አሁን ታምናላችሁ? በሙሉ ልባችሁ? አሁን፡ አያችሁ፡ ወደ ጉባኤው ስመለከት፡ ልክ የ—የሆነ ጉም ነገር፡ እዚያ የሚታይ፡ ይመስላል።

404 "እኔ የማደርገውን እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።" በምድራዊ ሕይወት በዘመኑ ሙሉ ካደረገው ይልቅ... ከዚህ ዓይነቱ፡ ዛሬ ማታ፡ እዚሁ፡ ብዙ አድርጓል። ልክ ነው።

አሁን፡ እዚህ ያለችው ይህች አንዲት ሴት፡ ወጣት ሴት ናት። አላውቃትም፡ ለእኔ እንግዳ ናት። የእርሱ አገልጋይ መሆኔን ታምኛለሽን? [እህት፡ "አዎ" አለች።—አርታዒ።] አሁን አንድ ደቂቃ ጠብቁ።

405 አንድ ሰው ከፊቴ መጣ፡ በጉባኤ መሃል ያለ አንድ ሰው። አሁን አንድ ደቂቃ ጠብቁ። በአድማጮቹ መሃል ያለ የሆነ ሰው። ልክ አሁን ከዚህ ሄዷል፥ ያ ብርሃን ከዚህ ሄዷል። ከእርሱም አጠገብ አንድ ሰው ቆሞ ነበር፡ በሆነ ሰፍራ በጉባኤ መሃል። አትጨነቁ፥ አይዞአችሁ በርቱ።

406 እንደገና ወደ ኋላ እንመለስና ሴቲቱን እንያት። አሁን ጌታ አምላክ... ይህ በመንፈስ መለየት፡ መሰመሩን ያለፈ፡ ስድስት ወይም ሰባት፡ ወይም የሆነ ሌላ ነው። ጌታ ኢየሱስም፡ ለዚህች ሴት፡ ችግሯ ምንም ይሁን ምን ቢገልጥልኝ፡ ሌሎቻችሁ በሙሉ ልባችሁ እንድታምኑ ያደርጋችኋልን? በእነዚህ መሠረቶች ላይ ክርስቶስን ልትቀበሉ ትችላላችሁን? አያችሁ? አንድ ጊዜ ማረጋገጥ ይገባው ነበር። ሦስት ጊዜ ደግሞ ማረጋገጫ ነው። ይህ ደግሞ ለአሥር ሺዎች ጊዜ ያህል፡ አንድም ጊዜ ሳይሳሳት ነው።

407 እዚህ የመጣሽው ለራስሽ አይደለም። የመጣሽው ለአንድ ሰው ነው። ራሱን ደፍቶ ተቀምጦ እየዋለሁ። ሲጋራ እያጨሰ ነው፡ እናም ሲጋራውን እንዲተውለት እየጸለይሽ ነው። ያ... እህቴ፡ ጌታ አምላክ የልብሽን መሻት ይሰጥሽ። በሙሉ ልብሽ እያመንሽ፡ ሂጂ፡ በጌታ በኢየሱስ ስምም ያ የልማድ ጋኔን፡ ከባለቤትሽ ይውጣ።

408 ችግርሽ ያለው በጀርባሽ ላይ ነው። እግዚአብሔር እንደሚፈውሰው ታምኛለሽን? ታምኛለሽ? [እህት፡ "አዎ፡ አምናለሁ" አለች።—እርታዒ።] መልካም። ሂጂና፡ "ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ፡" በይ።

409 ይህችን ሴት አውቃታለሁ፡ የወይዘሮ ኒስ ልጅ እንደሆነች እሰባለሁ። አደለም እንዴ? [እህት፡ "አዎ" አለች።—እርታዒ።] እንደዚያ መስሎኝ ነበር። እግዚአብሔር ይባርክሽ። ያ የቆየው የጀርባ ሕመም አሁን ይለቅሻል ሂጂ ደህና ትሆኛለሽ።

410 ያንን የአጥንት መገጣጠሚያ ሕመም እግዚአብሔር ፈውሶ ሊያድንሽ እንደሚችል ታምኛለሽን? ሂጂና እንደምታምኚው ንገሪው። በሙሉ ልብሽ እመኚ።

411 እንደምን ነህ፡ ጌታዬ? ያንን የጨጓራ ሕመም እግዚአብሔር ፈውሶ ሊያድንህ እንደሚችል ታምናለህን? [ወንድም፡ "አሜን" አለ።—እርታዒ።] መልካም፡ እንደዛ ከሆነ ሂድና፡ "ጌታ ሆይ አመሰግንሃለሁ፡ እ—እኔ አሁን እፈወሳለሁ፡" በል። እ—እናም ት—ትፈወሳለህ።

412 ሌላ የአጥንት መገጣጠሚያ ሕመም፡ ደግሞም እርጅናም ጭምር። እጆቼን ብጭንብሽ፡ እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽን? [እህት፡ "ወንድሜ ሆይ፡ እጆችህን በላዬ በመጫን፡ ብዙ ጊዜ አድርጎታል፡" አለች።—እርታዒ።] ያንን ሰማችሁ? ጌታ እህቴን ይባርካት፡ ዛሬ ማታም ዳግመኛ መፈወስን ይሰጣት። አሜን። እርሱን እመኚው።

413 የልብ ሕመም፡ የጨጓራ ሕመም። እግዚአብሔር ሊፈውሰው እንደሚችል ታምኛለሽን? መልካም። ሂጂ፡ በጌታ በኢየሱስ ስም፡ እርሱ ይፈውስሽ።

414 እንዴት ነህ፡ ወጣት? የአስም ሕመም። እግዚአብሔር አስምን ሊፈውስ እንደሚችል ታምናለህን? [ወንድም፡ "አዎ" አለ።—እርታዒ።] ሂድ፡ እመነው፥ ያደርገዋል። መልካም።

415 የስኳር ሕመም። እግዚአብሔር ደምህን ፈውሶ ሊያድንህ እንደሚችል ታምናለህን? ሂድ፡ እመን፡ እርሱም ይፈውስሃል። በሙሉ ልብህ ታምናለህን?

416 ምንም ነገር ባልነግርህ፥ ዝም ብዬ እጆቼን ብጭንብህ፥ ፈውሶ ሊያድንህ መንፈስ ቅዱስ እዚህ እንዳለ ታምናለህ? መንገዱ ያ ነው። ወደዚህ ና። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ይሂድና ይፈወስ። አሜን።

417 ነይ እመቤት። ምንም ነገር ባልነግርሽ፡ ከዚያ ከሴቶች ሕመምሽ እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽን-... አይ፡ ይቅርታ፡ አስቀድሞ ተናግሮታል። ሂጂ። እግዚአብሔር ይባርክሽ። ሂጂ፡ እያመንሽ፡ ሂጂ፡ ከዚያም፡ ተፈወሺ።

418 ጌታዬ፡ በሙሉ ልብህ ታምናለህን? እግዚአብሔር የልብ ሕመምን ይፈውሳል፡ አይደለም እንዴ? [ወንድም፡ "አዎ፡ ጌታዬ" አለ።—አርታዒ።] ሰውን ይፈውሳል። እንደሚያደርገው እርግጠኛ ነኝ።

419 እርሱ፡ እርሱ እግዚአብሔር ነው። ያንን ታምናላችሁ? በሙሉ ልባችሁ ታምኑታላችሁ? በእግዚአብሔር እመኑ!

420 እዚህ ውጭ አንድ ሰው አሁን ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ አንድ ነገር አድርጓል። ያንን ማግኘት እፈልጋለሁ። ደም ነበር። ልክ እንደ አደጋ፡ ወይም የሆነ የተፈጠረ ነገር ያለበት ሰው። እ—እየደማ ነበር። የሆነ ቦታ ላይ ነበር። ሰውዬው እዚህ ቆሞ ነበር። አሁን ዝም ብላችሁ ጸልዩ። አዎ፡ እርሱ ነው። ተቀምጦ ያለው ሰው-... አያችሁ፡ ጄ. ቲ. ፓርኔል ነው። ልጁን አውቀዋለሁ። ውስጥህ እየደማህ ነው፡ ጄ. ቲ. እግዚአብሔር እንደሚፈውስህ ታምናለህን? መልካም፡ እንደዛ ከሆነ ይቆማል፡ ጄ.ቲ. በሙሉ ልብህ እመን።

421 ልክ እዚህ ተቀምጣ ያለችው፡ አቋርጣ እያየች ያለችው፡ እዚያ በወንድም ግሪምስሊ አጠገብ ተቀምጣ ያለችው ምስኪን ሴት። አጠገቧ ብርሃን አለ። አንቺ፡ ትንሽ ነጭ ኮሌታ ያደረግሽው። ማርያም፡ አላውቅሽም፡ ሰምሽ ግን ያ ነው። በመንፈሳዊ ችግር ትሠቃያለሽ፡ እንዲሁም በጣም ትረበሻለሽ። እርሺው፥ ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል። በሙሉ ልብሽ እመኚ። በእግዚአብሔር እመኑ። ማመን ብቻ ቢቻላችሁ።

422 ልክ እዚያ ኋላ በመጨረሻው ረድፍ ላይ፡ እዚያ በጎን በኩል ተቀምጣ ያለችው ይህች ምስኪን ሴት፡ የመጣችው ከሚሺጋን ነው፡ በሴቶች በሽታ ትሠቃያለች። እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽን? የለመንሽውን ማግኘት፡ ትችያለሽ። ታምኚዋለሽን? አሜን። እጅሽን አንሺና፡ "እቀበለዋለሁ፡" በዪ። መልካም፡ ወደ ቤትሽ ሄደሽ ልትፈወሺ ትችያለሽ። እመቤቲቱን አላውቃትም፡ እግዚአብሔር ግን ያውቃታል።

423 እዚህ ቃሬዛ ላይ ያለኸውስ አንተ? ብቸኛው አካል ጉዳተኛ ሰው፡ ወይም አልጋ ላይ ያለህ ሰው አንተ ነህ። እኔ ለአንተ እንግዳ ነኝ። አላውቅህም። እግዚአብሔር ያውቅሃል። ዳሩ ግን፡ አሁን እልሃለሁ፡ የሞት ጥላ አጥልቶብሃል። ካንሰር አለብህ። የመጣኸው ከሩቅ መንገድ ነው። ወደዚህ፡ የመጣኸው ከሲንሲናቲ ነው። ሰምህ አቶ ሆክ ይባላል። በሙሉ ልብህ እመን። እዚያ ተቀምጠህ ከቀረህ፡ ትሞታለህ። ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀበልና ተፈወስ። ታምነዋለህን? ታዲያ ከዚያ አልጋ ላይ፡ በእግሮችህ ቁም፡ ኢየሱስ ክርስቶስንም ተቀበል።

424 በዚህ ደቂቃ እርሱን የሚያምን እዚህ ውስጥ ስንት ሰው አለ? በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ? እንደዛ ከሆነ፡ እያንዳንዳችሁ፡ ልክ አሁን ቁሙ። ቁሙ። አሁን በራሳችሁ መንገድ፡ በምትጸልዩበት መንገድ፡ ከአጠገባችሁ ባለው ሰው ላይ እጃችሁን ጫኑ።

425 እህት ብራውን የት አለች? በዚህ እየተሠቃየች፡ እዚህ ተቀምጣ ነበር። በቀደም በስልክ ደውላልኝ ነበር፡ እጇቿንም ከፍ ማድረግ አትችልም ነበር። በደሟ ውስጥ የሆነ ችግር እንዳለ አየሁ። በቀደም ሰገናኛት... የስኳር በሽታ አለባት። የት ናት? ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ ከወይዘሮ ዶክ ጋር እዚህ ነበረች። መልካም፡ እህት ብራውን። ዛሬ ማታ፡ በሙሉ ልብሽ እንድታምኚ እፈልጋለሁ።

ችግርሽ ምን እንደሆነ እንደምታውቂ አውቃለሁ፡ እንድታምኚ ግን እፈልጋለሁ። እዚህ ለመምጣት፡ ከሆስፒታል ወጥተሻል፡ አያችሁ፡ ጸሎት እንዲደረግልሽ። አሁን እጸልይልሻለሁ። እመኚ። ልትፈወሺ ነው።

426 ማርጂ፡ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ይኑርሽ። ሕመሙ አሁን ሊቆም ነው። ሊያበቃ ነው። የስኳር በሽታን ሊፈውስ ይችላል፡ በጨጓራሽ ካለው ከዚያ ሕመም ሊፈውስሽ ይችላል።

427 አሁን እያንዳንዳችሁ አንዱ በሌላው ላይ እጃችሁን ጫኑ፡ እጆቻችሁንም ለአንድ ደቂቃ ያህል ዝም ብላችሁ እዚያው አቆዩ። ዝም ብላችሁ አንዱ በሌላው ላይ እጃችሁን ጫኑ፡ አቆዩ... አያችሁ፡ አምስት ሰዓት ሊሆን ነው፡ ከእነዚህ ሰዎች መካከል ብዙዎቹ መኪና ነድተው ወደ ቴነሲና ወደ ተለያዩ ሰፍራዎች መሄድ አለባቸው።

428 በእርግጥ፡ ጌታ አምላክ አረጋግጧል። ዛሬ ማታ፡ ምን አያችሁ? ሰውን አያችሁ ወይስ ኢየሱስን አያችሁ፡ ኢየሱስ ቃሉን ሲያጸና?

429 እዚህ የተቀመጡት እነዚህ መሃረቦች፡ ይህ ቅባት በእኔ ላይ ሳለ፡ እጆቼንም በእነዚህ መሃረቦች ላይ አድርጌ፡ ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር... እንዲህ ብለዋል፡ "ከጳውሎስ መሃረብን፡ ወይም ጨርቅን ወሰዱ።"

430 ሞተው የነበሩት፡ ከሞት የተነሱት እዚህ አሉ። አደጋ ደርሶባቸው፡ ተሰባብረው የነበሩ፡ አሁን ግን የተፈወሱ እዚህ አሉ። እዚህ...

431 ከዓመታት በፊት፡ በቅርብ ጊዜ፡ በቲቢ፡ ደም ይፈሳትና፡ ልትሞት የነበረችው፡ ወይዘሮ ዊልሰን አሁን እዚህ ቆማ አያታለሁ። ዛሬ ማታ እዚህ አለች፡ ሐኪሞች በሕይወት ለመቆየት ጥቂት ሰዓታት ብቻ ነበር የሰጧት። ዛሬ ማታ እዚህ ቆማለች።

432 በዚሁ ሁሉ ዙሪያ፡ አንካሶች፡ ዕውሮች፡ አካል ጉዳተኞች፡ በዊልቼርና በሁሉም ነገር ላይ የነበሩና ሌሎችም፡ ዛሬ ማታ እንደ ሕያው የድል እርማዎች ቆመዋል። ለምንድን ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው ነው፡ እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።

433 ከጥቂት ጊዜ በፊት፡ የመሰከረው ያ ሰው፡ እዚያ ታች፡ እርሱ፡ የሚጥል በሽታ ነበረበት፡ ለነዚያ ሁሉ ዓመታት ነበረበት፡ ሌሎችም ነገሮች ነበሩበት፡ በስብሰባው ውስጥ ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ ነበር የተገኘው። ያ ከሆነ፡ ሃያ ዓመት ገደማ ሆኖታል፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አንድም ጊዜ ጥሎት አያውቅም። ያ ከአሥር ሺዎች መካከል አንዱ ነው።

434 እርሱ ፈዋሽ ነው። አሜን። እርሱ ይፈውሳል። አሁን፡ አትረበሹ። ዝም ብላችሁ፡ እንደ ሕፃን-ባለ እምነት፡ ዘወር ብላችሁ ወደ ቀራንዮ ተመልከቱ። ዓይኖቻችሁን ጨፍኑና በዚህ ተብርናክል ውስጥ መሆናችሁን እርሱ። ዓይኖቻችሁን ጨፍኑና በዙሪያችሁ ማንም እንዳለ እርሱ፡ ወደ ኢየሱስ ተመልከቱና እዩት።

ወደ ኢየሱስ ተመልከትና በሕይወት ኑር፥
በቃሉ ተመዝግቧልና፡ ሃሌሉያ!
የሚጠበቅብን "ተመልክተን በሕይወት መኖር" ብቻ ነው።

ኦህ፡ ተመልከትና በሕይወት ኑር፡ ወንድሜ፡ ኑር!
ወደ ኢየሱስ ተመልከትና በሕይወት ኑር፥
በቃሉ ተመዝግቧልና፡ ሃሌሉያ!
የሚጠበቅብህ “ተመልክተህ በሕይወት መኖር” ነው።

435 ሰውን ላለማየት ዓይናችሁን ጨፍኑ። በዙሪያችሁ ባሉ ነገሮች ላይ ዓይኖቻችሁን ጨፍኑ። በእምነታችሁም በኩል፡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልከቱ፡ “እርሱ ስለ መተላለፋችሁ ቈሰለ፡ በእርሱ ቍስል እናንተ ተፈወሳችሁ፡” የሚለውንም፡ እወቁ።

436 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እነዚህ ሰዎች እየጸለዩ ሳሉ፡ እርስ በርሳቸውም፡ እጆቻቸውን ጭነዋል። እኛም... የልባችንን ምስጢር በሚገልጥልን፡ መሻታችንን በሚያሳውቀን፡ እንዲሁም ማመን ብቻ ቢቻለን፡ መሻታችንን እንደሚሰጠን፡ ተስፋ በሚሰጠን፡ በመንፈስ ቅዱስ አምሳል በሆነው በሕያውና ከሞት በተነሳው በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እንደቆምን እንገነዘባለን።

437 ወንዶችና ሴቶች እርስ በርሳቸው እጆቻቸውን ጭነዋል። እየጸለዩም ነው፡ ምክንያቱም እኛ የእግዚአብሔር መንግሥት አብረን የምንወርስ ዜጎች ነንና። እኛ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድሞችና እህቶች ነን።

438 እናም፡ ሰይጣን፡ በጌታ በኢየሱስ ስም በመቃወም እንገጥምሃለን። እርሱ ሰይፍ ነው። እርሱ በሽታን ቆርጦ የሚያስወግድ ነው። እርሱ ጥርጣሬን ቆርጦ የሚያስወግድ ነው። እርሱ ድል ነሺው ነው። አሁንም ሰይጣን፡ ከዚህ ሕዝብ ውስጥ እንድትወጣ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እንገጥምሃለን!

439 የእግዚአብሔር ቃል ተገልጧል። እርሱም ይገርዛል፡ ጥርጣሬን ያስወግዳል፡ በሽታን ያስወግዳል፡ እንዲሁም ፍጹም የሆነ ነጻ መውጣትን ያመጣል። መንፈስ ቅዱስ በዚህ ሕዝብ ላይ እንዲወርድ፡ እንዲሁም ሁሉን ቻይ የሆነው ክርስቶስ ሕልውና አሁን እዚህ መሆኑን እንዲያምኑ የእምነትን ኃይል እንዲሰጣቸው እንጸልያለን። ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን።

440 እያንዳንዱን ሕመም እኮንናለሁ። በሽታዎችን ሁሉ እኮንናለሁ። አለማመንን ሁሉ እኮንናለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ መንፈስ ቅዱስ የተናገርኩትን ያክብር፡ በዚህም ሕንፃ ውስጥ አልፎ በመለኮታዊ ሕልውናው ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ሰው ነጻ ያውጣ።

441 አሁን እጆቻችሁን አንሱና እርሱን አመስግኑት። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ደህና እንደሆናችሁና እንደተፈወሳችሁ አውጃለሁ!

63-1229E ወደ ኢየሱስ ተመልከቱ
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤሰ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org